**DSpace Institution**

**DSpace Repository** **http://dspace.org**

Ethiopian Languages and Literature - Amharic Thesis and Dissertations

2020-11-11

# þÿè Í“Ê•u -e&} ` ò (s L Í5%

þÿ •`) -`- p 5 •

http://hdl.handle.net/123456789/11618

*Downloaded from DSpace Repository, DSpace Institution's institutional repository*

# ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

## ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል


# የህልውናዊነት ጭብጦች በአዳም ረታ ለፍ ውስጥ

በ


መንበሩ ክበር ተመስገን



የካቲት፣ 2012 ዓ.ም

ባሕር ዳር

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ- አማርኛ ትምህርት ክፍል

# የህልውናዊነት ጭብጦች በአዳም ረታ ለፍ ውስጥ

ለባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል

ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ

የአማርኛ ሥነጽሑፍ ድህረ ምረቃ ፕሮግራም

መንበሩ ክበር ተመስገን

አማካሪ ፡- አየነው ጓዴ (ዶ/ር)

የካቲት፣ 2012 ዓ.ም.

ባሕር ዳር

# ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

# ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ

# የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ- አማርኛ ትምህርት ክፍል

## የቴሲስ ፈተና ውጤት ማረጋገጫ

እኛ ስማችን ከታች የተዘረዘሩት የፈተና ቦርድ አባላት

"የህልውናዊነት ጭብጦች በአዳም ረታ ሰፍ ውስጥ"

የሚለውን የማስተር ቴሲስ ፈትነን ---------------- ውጤት በጋራ ተስማምተን አጽድቀናል፡፡.

## የፈተና ቦርድ አባላት

| የውጭ ፈታኝ ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|
| ________________________ | ____________________ | ________________ |
| የውስጥ ፈታኝ ስም | ፊርማ | ቀን |
| ------------------------------------ | ---------------------------- | ----------------------- |
| የፈተናው ሰብሳቢ ስም | ፊርማ | ቀን |
| -------------------------------------- | ------------------------------ | ------------------------- |

# ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሞ፣ ይህ ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ለወደደ ለሁሉ አለቃ፣ የሰላም አምላክ ለሆነ፣ **የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ልጅ፣ ቸሩ ልዑል እግዚአብሔር** ስሙ ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ ለዘለዓለሙ የተመሰገነ ይሁን!

ይህ ጥናት በዚህ መልኩ እንዲሰናዳ እና ይህን መስመር ይይዝ ዘንድ ከእኔ ከታናሽህ ጎን ቆመህ ያላሰለሰ ደጋፊ አስተያየትህን ለሰጠኸኝ መምህሬ እና አማካሪየ ዶ/ር አየነው ጓዱ ላቅ ያለ ምስጋናየ ይድረስልኝ፡፡

ጅማሮየን እንዳልዘነጋ እያባነንክ የሁልጊዜም ክትትል እና ድጋፍህን ላደረግህልኝ እንዲሁም ገንቢ አስተያየትህን ላልነፈግኸኝ መምህሬ ዶ/ር አንተነህ አወቀ አክብሮታዊ ምስጋናየ ይድረስልኝ፡፡

ከጅምሩ እስከ ፍጻሜው ድረስ የህይወት ስንቅ ይሆነኝ ዘንድ የዕውቀት ዘራችሁን በአዕምሮየ ላይ የዘራችሁልኝ መምህሮቼ ሁሉ ልባዊ ምስጋናየን እንኳችሁ፡፡

ከዚህ በመቀጠል፣ የእኔን ሀሴት እና ፍስሃ ለማየት እራስሽን ትተሽ ከእኔ በላይ ለእኔ ህላዌ ስትይ ብቻ ለምትኖሪው ውዷ ባለቤቴ ለምለም አረጋ፤ ስቸገር እየረዳሽ፣ ሲደክመኝ እያበረታሽ፣ ያላንዳች እረፍት እየደከምሽ እዚህ አድርሰሽኛል እና እጅጉን አመሰግንሻለሁ፡፡

በምክር፣ በገንዘብ እና በጸሎት ለደገፋችሁኝ ውድ ቤተሰቦቼ እንዲሁም በሃሳብ ላጠናከራችሁኝ ጓደኞቼ እና የሥራ አጋሮቼ ሁሉ ምስጋናየ ለእናንተም ይሁንልኝ፡፡

# ማውጫ

**ይዘት** **ገጽ**

ምስጋና ........ i
ማውጫ ........ ii
አጠቃሎ ........ iv
ምዕራፍ አንድ ........ 1
መግቢያ ........ 1
1.1. የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 6
1.3. ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች ........ 7
1.4. የጥናቱ ዓላማዎች ........ 8
1.5. የጥናቱ ፋይዳ ........ 8
1.6. የጥናቱ ገደብ እና ውስንነት ........ 9
1.7. የጥናቱ ሥነዘዴ ........ 12
1.7.1. ረጅም ልቦለዱ የተመረጠበት መመዘኛ ........ 12
1.7.2. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ........ 12
1.7.3. የጥናቱ ዘዴ (ስልት) ........ 13
1.7.4. የመረጃ አተናተን ስልት እና ሂደት ........ 13
1.8. የምዕራፍ አደረጃጀት ........ 14
ምዕራፍ ሁለት ........ 15
የተዛማጅ ጽሑፍ ክለሳ ........ 15
2.1 የንድፈ-ሃሳባዊ ጽሑፍ ክለሳ ........ 15
2.1.1. ነገረህላዌ ........ 15

2.1.2. የነገረህላዌ ፍልስፍና ታሪካዊ እድገት ........ 19

2.1.3. የነገረህላዌ ፍልስፍና እና ሥነጽሑፍ ........ 28

2.1.4. የህልውናዊነት ጭብጦች ........ 30

2.1.4.1. ነጻነት እና ኃላፊነት ........ 30

2.1.4.2. ኦናነት (Forlornness) ........ 34

2.1.4.3. ሁኔታዊነት (Situatedness) ........ 35

2.1.4.4. የርእይ መነጠቅ (Disillusionment) ........ 37

2.1.4.5. ቀቢጸ ተስፋ (Despair) ........ 39

2.2. የቀደምት ጥናቶች ክለሳ ........ 40

ምዕራፍ ሦስት ........ 47

የህልውናዊነት ጭብጦች ትንተና በሐፍ ረጅም ልቦለድ ውስጥ ........ 47

3.1. ነፃነት እና ኃላፊነት ........ 48

3.2. ኦናነት ........ 58

3.3. ሁኔታዊነት ........ 64

3.4. የርእይ መነጠቅ ........ 70

3.5. ቀቢጸ ተስፋ ........ 84

ምዕራፍ አራት ........ 90

ማጠቃለያ ........ 90

ዋቢ ጽሑፎች ........ 94

አባሪዎች ........ 99

አባሪ- ሀ፡- የረጅም ልቦለዱ አጽመ-ታሪክ ........ 99

አባሪ- ለ፡- የረጅም ልቦለዱ ቅርጽ ........ 101

መግለጫ ........ 103

# አጠቃሎ


ይህ ጥናት፣ ለምርምር በተመረጠው አፍ (2010) ረጅም ልቦለድ ውስጥ የቀረቡ የነገረህላዌ ጭብጦች ምን ምን እንደሆኑ በመለየት እና ተንትኖ በማሳየት ልቦለዱ ከነገረህላዌ ፍልስፍና ጋር ያለውን ግንኙነት ለመግለጥ የተደረገ ሙከራ ነው፡፡ ይህን ጉዳይ ለማጥናት ምክንያት የሆነው ደግሞ፣ ለምርምር በተመረጠው ረጅም ልቦለድ ናሙናነት የነገረህላዌ ፍልስፍና ከሥነጽሑፍ በተለይም ከአማርኛ ሥነጽሑፍ ጋር ያለውን ተዛምዶ አጉልቶ ለማሳየት አብዝቶ መሻት ነው፡፡ እነዚህ የህልውናዊነት ጭብጦች ከራሱ ከነገረህላዌ ፍልስፍና የሚመነጩ በመሆናቸው፣ ይህን ፍልስፍና በመተንተኛ ስልትነት ተጠቅሟል፡፡ በዚህ መሠረት ለምርምር በተመረጠው አፍ ረጅም ልቦለድ ውስጥ ባሉት ገፀ ባህርያት ህላዌ ወስጥ ተመላልሰው የተከሰቱ አምስት ዋና ዋና የህልውና ጭብጦች (ነጻነት እና ኃላፊነት፣ ኦናነት፣ ሁኔታዊነት፣ የርእይ መነጠቅ እና ቀቢጸተስፋ) ተለይተው እና በነገረህላዌ ፍልስፍና መተርጎሚያነት ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ፣ እነዚህ የነገረህላዌ ጭብጦች ያላቸው የእርስ በእርስ መስተጋብር ምን እንደሚመስል እና ከእንዴት አይነት ዓውድ እንደሚቀዱ እንደዚሁም የቀረቡበትን የትረካ መዋቅር ስልት ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ በዚህ መሠረት፣ በዚህ ልቦለድ ውስጥ ነጻነት ከነጻነት እጦት ትይዩ የቀረበ ሲሆን አንዳንዶቹ ገፀ ሰዎች እራሳቸውን ሲፈጥሩ ሌሎቹ ደግሞ በተቀደደላቸው ቦይ ብቻ እንዲፈሱ ተደርገው ቀርበዋል፡፡ በኋላም እነዚህ ነጻ ገፀ ባህርያት በህይወት ጉዟቸው ወቅት እራሳቸውን እንደተጣሉ አድርገው ይቆጥራሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ደግሞ ካላስፈላጊ ብቸኝነት ወይም ኦናነት ውስጥ ይገባሉ፡፡ እነዚህ ገፀ ባህርያት የቱንም ያህል ነጻ ቢሆኑ ከማህበረሰባቸው የሚቀዱት ኑባሬም አላቸው፤ በዚህ ምክንያትም ሁኔታዊ ይሆናሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በዚህ ልቦለድ ውስጥ የቀረቡት ገፀ ሰዎች ሙሉ ለሙሉ ሊባል በሚችል መልኩ ያሰቡት፣ የተመኙት፣ ያቀዱት አልሳካ ይላቸዋል፤ ወይም ርእያቸውን በተለያዩ ምክንያቶች ይነጠቃሉ፡፡ በመጨረሻም አንዳንዶቹ ከተስፋ መቁረጥ አዘቅት ውስጥ ይዘፈቃሉ፡፡

# ምዕራፍ አንድ
# መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

በየዘመናቱ እና በየወቅቱ ነባራዊ ሁኔታዎች መሠረትነት የሚቀነበቡ ልዩ ልዩ የሥነጽሑፍ ሥራዎች በውስጣቸው አምቀው የያዟቸው ይዘቶች እና የተቀናጁባቸው መንገዶች ጎልተው ይወጡ ዘንድ በተለያዩ የዘርፉ ባለሙያዎች ሂሳዊ ትንታኔ ታሽተው እና በውል ተፈትሸው ሲቀርቡ ማየት በተለይ ደግሞ ዛሬ ዛሬ የተለመደ ተግባር እየሆነ የመጣ ተግባር ነው፡፡ ይህ አንድን ሥነጽሑፋዊ ሥራ ሥርዓታዊ በሆነ መንገድ የመተርጎም፣ የመተንተን እና የመግለጥ ሂደት ደግሞ ሥነጽሑፋዊ ሂስ ወይም ሥነጽሑፋዊ ጥናት እንደሆነ Dr. Alex E. Blazer (2010) ያብራራሉ፡፡ በተመሳሳይ ዘሪሁን (2009፤ 353)፣ "ሥነ ጽሁፋዊ ሂስ ከዘመነ ግሪክ አንስቶ እስከ ዛሬ ድረስ የተለያዩ ፍልስፍናዎች እና አተያዮች ተንፀባርቀውበታል፡፡ [...] ከፕሌቶ እና ከአሪስቶትል ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የተለያዩ እሳቤዎች እየተንጸባረቁበት፣ የተለያዩ ፈለጎች እየታዩበት እያደገ እና እየሰፋ የመጣ የኪነጥበብ መስክ ነው" በማለት ወዲህ፣ የሥነጽሑፍ ሂስን ዘመን ተሻጋሪነት፤ ወዲህ ደግሞ ቀደም ሲል እንደተጠቆመው በጊዜ ልዩነት የሚያተኩርባቸው ጉዳዮችም እንዲሁ የተለያዩ መሆናቸውን ያስረዳሉ፡፡ በጥቅሉ ሥነጽሑፋዊ ጥናት ወይም ሥነጽሑፋዊ ሂስ፣ በየዘመናቱ ልዩነት በሁነኛ ንድፈሃሳባዊ ማዕቀፍ ላይ ተመርኩዞ፣ የመተንተኛ ዘዴውን ወስኖ፣ የተለያዩ ሥነጽሑፋዊ ጉዳይዮችን በዓላማነት ሠንቆ፣ ዓላማውን ለማሳካት የሚያስችሉ ሂደቶችን ተከትሎ የሚካሄድ ሲሆን፣ ሰፊ እና ጥልቅ ምርምርን እንዲሁም ጥሩ ግንዛቤን ጭምር የሚጠይቅ ተግባር ነው፡፡

ሥነጽሑፋዊ ጥናት ወይም ሥነጽሑፋዊ ሂስ እንደሚያነሳው ርዕሰጉዳይ የሚለያይ ሆኖ፤ በየወቅቱ የሚከየኑ የሥነጽሑፍ ሥራዎችን የይዘት ትኩረት እና የአቀራረብ ስልት በመግለጥ ሥነ ጽሑፋዊ ግንዛቤን ለማስፋት እና አጠቃላዩን የሥነ ጽሑፍ ዘርፍን ለማሳደግ ያለው አዎንታዊ ፋይዳ የሚያጠያይቅ አይደለም፡፡ ይህን ዘርፈ ብዙ የሥነ ጽሑፍ ጥናት ጠቀሜታ ቴዎድሮስ ገብሬ (2001፣129) T.S Eliotን ዋቢ አድርገው፣ "ሥነ ጽሑፋዊ ጥናት፣ የጥቅሉን ሥነ ጽሑፍ ህልውና ለማቆየት የመተንፈስን ያህል ግድ የሆነ ተግባር ነው" በማለት ያጠቃልሉታል፡፡ ሥነጽሑፋዊ ጥናቶች በጊዜ ሂደት ውስጥ የሚከሰቱ የተለያዩ ሥነ ጽሁፋዊ ጉዳዮችን ለውጥ እና የየወቅቱን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ

ይቀናጃሉ፤ ይተነተናሉ፤ ይብራራሉ፡፡ በዚህ ሥነጽሑፍን የመርጎም ወይም የመመርመር ሂደት ውስጥ ደግሞ የተለያዩ ለመተንነኛ መሳሪያነት ምቹ የሆኑ ሥነጽሑፋዊ ንድፈሃሳቦችን (Literary theories) መርጦ መጠቀም የውዴታ ግዴታ መሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡

ሥነጽሑፋዊ ንድፈሃሳብ (Literary theory) የሚለው ስያሜ የተለያዩ ጥልቅ እንቅስቃሴዎችን እና አተያዮችን የሚገልጽ ሲሆን፣ በሥነጽሑፋዊ አሃዶች፣ በፊልሞች እና በተለያዩ ባህላዊ ስርዓቶች ምርምር ላይ በተሰማሩ የሥነሰብዕ አባላት (Members of Humanities) ወይም ተመራማሪዎች ዘንድ ጥቅም ላይ የሚውሉ የመተንተኛ መነጽሮች ናቸው፡፡ ሥነጽሑፋዊ ንድፈሃሳብ ዘርፈ ብዙ የሆነ ስያሜ በመሆኑ በሥነጽሑፍ እና በባህል ጥናት ሥራ ውስጥ ልዩልዩ ጽሁፋዊ አሃዶችን ለመለየት እና ለመተንተን ምቹ የሆኑ ንድፈሃሳቦችን ሁሉ አቅፎ የያዘ ሲሆን፣ ይኸውም ለምሳሌ፡- በስርዓተፆታ ተሟጋቾች (Feminists)፣ በማርክሳውያን (Marxists)፣ እንዲሁም ሥነጽሑፍን በሚያስተምሩ ነገርግን ሌላ ዝንባሌ ባላቸው የሥነልቦና እና የፍልስፍና ጥናቶች ውስጥ የሚያገለግሉ አተያዮችን ሁሉ ያካትታል (Julian Wolfreys, 2001)፡፡

በተጨማሪም Gregory Castle (2007)፣ ሥነጽሑፋዊ ንድፈሃሳብ በአዲስ ምዕራፍ ብቅ ያለው ከ1970ዎቹ ወዲህ መሆኑን ገልጸው፣ ይኸውም የፍልስፍና፣ የታሪክ፣ የፖለቲካ እና የሥነልቦና ጭብጦችን የሚያስተዋውቁ እንዲሁም በማርክሲዝም፣ በመዋቅራዊ ሂስ (Structuralism)፣ በድህረ-መዋቅራዊ ሂስ (Poststructuralism)፣ በአንስታይ ሂስ፣ በነገረ ባህላዊ ሂስ (Cultural Studies)፣ በሃዲስ ታሪካዊ ሂስ (Newhistoricism) እና በመሳሰሉት ንድፈሃሳባዊ ልማዶች መተንተን የሚሹ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የፈለቁበት ወቅት እንደነበረ ያትታሉ፡፡ ታዲያ እነዚህ እና ሌሎችም በቁጥር የበዙ እና የተለያየ አይነት ያላቸው ንድፈሃሳባዊ ልማዶች በአዲስ መልክ መምጣት የሥነጽሑፍንም ሆነ የንድፈሃሳቦችን ባህርይ እና ተፈጥሮ ለመረዳት ውስብስብ ተግዳሮቶችን እንደፈጠሩም Castle (2007) ይገልጻሉ፡፡ ስለሆነም እነዚህን ጨምሮ በዚህ ዘመን ያሉ ሌሎች ብዙ ቁጥር ያላቸውን ሥነጽሑፋዊ ንድፈሃሳቦች ሥርዓት፣ ጽንሰሃሳብ፣ አስፈላጊነት እና መርህ በውል መለየት እና መመርመር የሚሻ ጉዳይ መሆኑንም መገንዘብ ይቻላል፡፡

የዚህ ጥናት ዋነኛ ትኩረት ደግሞ በአማርኛ ሥነጽሑፍ ላይ በመሆኑ ስለዚህ ጉዳይ ጥቂት ነገሮችን እንመልከት፡፡ ይህን የአማርኛ ሥነጽሑፍ ጥናት አስመልክተው በአማርኛ ሥነጽሑፍ ጥናት ላይ ቅኝት ያደረጉት ታዬ አሰፋ እና ሽፈራው በቀለ (2000)፣ የአማርኛ ሥነጽሁፍ ጥናት ከራሱ ከአማርኛ ሥነ ጽሁፍ መጀመር ጋር የተያያዘ ሆኖ በኢጣሊያን አጥኚዎች ግንባር ቀደምትነት በተለይም በአገራችን የዘመናዊ ሥነጽሑፍ ታሪክ የመጀመሪያው የአማርኛ ዘመናዊ ሥነጽሑፍ ሥራ (የአፈወርቅ ገ/ኢየሱስ ልቦለድልቦለድ ታሪክ) ብቅ ካለበት ጌዜ ማለትም በፈረንጆች 1908 ገደማ ጀምሮ እንደተጀመረ እና ቀስ በቀስም በተለያዩ የሀገራችን ምሁራን አማካኝነት እያደገ መጥቶ ዛሬ ያለበትበት ደረጃ ላይ እንደደረሥ ያስረዳሉ፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ቴዎድሮስ ገብሬ (2001፤ 129)፣ "ከሥነ ጽሑፍ ትይዩ እየሰፋ መጣ የተባለው የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ጥናት በአንድ አይነት ደረጃ፣ አንድ ጉዳይ ላይ አተኩሮ፣ አንድ መስመር ተከትሎ እዚህ የደረሰ አይደለም" በማለት የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ጥናት ወዲህ፣ ከራሱ ከሥነጽሑፍ ዘርፍ መጀመር ጋር የተያያዘ እድሜ ያለው እና አብሮ እያደገ የመጣ እንደሆነ፤ ወዲህ ደግሞ ጊዜ-ተኮር እና ሁኔታ-ተኮር ከመሆኑ የተነሳ በጊዜ ልዩነት ልዩ ልዩ ጉዳዮች የሚዳሰሱበት ተግባር መሆኑን ያስረግጣሉ፡፡ ስለዚህ ሥነ ጽሑፋዊ ጥናት (የአማርኛን ጨምሮ) የረጅም ዘመን ታሪክ ባለቤት፣ ቀጣይነት ያለው እና ሥነጽሑፍ ባለበት ሁሉ የሚኖር ዘመን ተሻጋሪ ተግባር ነው ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡

ከፍ ሲል እንደተጠቀመው፣ የአማርኛ ሥነጽሑፍ ጥናት ልክ እንደየትኛውም አይነት ሥነጽሑፋዊ ጥናት ሁሉ ይዞት የሚነሳውን ዋነኛ ጉዳይ ለመተንተን እና በተጨባጭ ለማሳየት የሚረዱ አሊያም ይዞት ከተነሳው ዓላማ አንፃር በሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ላይ የሚቀርቡ ይዘቶችን ሊያጎሉ በሚችል መንገድ ልዩ ልዩ ሥነጽሑፋዊ ንድፈሃሳቦችን (Literary theories) ገርቶ እና አስማምቶ ይጠቀማል፡፡ በዚህ መሰረት ይህ ጥናት፣ የድህረ ጦርነት ክስተትን ተከትሎ በተለይም ከዘመናዊነት እሳቤ (Modernism) ትይዩ ብቅ እንዳለ እና በዚያው በ20ኛው ክፍለ ዘመን ታላቅ ሥነጽሑፋዊ ሽፋን እንዳገኘ የሚነገርለትን የነገረህላዌ ፍልስፍና (Existentialism) በዋና ማናበቢያነት መርጦታል፡፡

"ነገረህላዌ" (Existentialism) የሚለው ቃል የተገኘው በ1940ዎቹ አጋማሽ በፈረንሳያዊው ፈላስፋ Gabriel Marcel አማካኝነት እንደሆነ እና በሥራ ላይ መዋል የጀመረው ደግሞ

በዚሁ ወቅት ላይ በጀርመናዊው ጸሐፊ እና ፈላስፋ Jean-Paul Sartre አማካኝነት እንደሆነ Azhar እንዲህ ያስረዳሉ፤

> The term ‘Existentialism’ seems to have been coined by the French philosopher Gabriel Marcel in the mid 1940s and adopted by Jean-Paul Sartre who, on October 29, 1945, discussed his own existentialist position in a lecture to the club Main tenant in Paris. (Iram Azhar, 2013; 2)

በእርግጥ የነገረህላዌ ፍልስፍና ታሪክም ሆነ ብያኔ በተለያዩ የፍልስፍናው አራማጆች እና ተመራማሪዎች ዘንድ የተለያየ ስለመሆኑ የዘርፉ ተመራማሪዎች እና እራሳቸው ፈላስፋዎችም የሚጋሩት ሃሳብ ነው፡፡ ይሁን እንጅ በዚህ ፍልስፍና ላይ የተሰማሩት ሁሉም አካላት ይህንኑ ፍልስፍናዊ እሳቤ በተመለከተ ሙሉ በሙሉ ወይም ፍጹም የማይገናኝ ሃሳብ አላቸው ማለት እንዳለሆነ ልብ ይሏል፡፡ እንዲያውም አብዛኛዎቹ ከሚጋሯቸው ጉዳዮች መካከል አንደኛው እና ዋናው፣ የሁሉም የዘርፉ ፈላስፋዎች የፍልስፍናቸው ማዕከላዊ ጉዳይ የሰው ልጅ መሆኑ ነው (ቴዎድሮስ፣ 2001)፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ በሥራዎቻቸው ውስጥ ተመላልሰው የሚመጡ እና ደጋግመው የሚያነሷቸው ልዩ ልዩ የነገረ ህላዌ ጭብጦችም ነገረህላዌያኑ በዚሁ ፍልስፍና ላይ ያላቸውን ተቀራራቢ ወይም የጋራ ሃሳብ የሚያሳይ ሌላው ጉዳይ ነው፤ Azhar (2013) እና ቴዎድሮስ (2001)ም በዚህ ጉዳይ ይስማማሉ፡፡

መሠረቱ ከጥንታውያን ታላላቅ ፈላስፋዎች፣ ቅዱሳን እና ትንቢተኞች እሳቤ ጋር እንደተቆራኘ የሚነገርለት ነገረህላዌ በተለያዩ የኪነጥበብ ሥራዎች ላይ በተለይም ደግሞ በሥነጽሑፍ ሲንጸባረቅ የቆየ እና ከሥነጽሑፍ ጋር የጠበቀ ዝምድና ያለው ፍልስፍናዊ እሳቤ ስለመሆኑ ብዙ ምሁራን ያትታሉ፡፡ በዚህ መሠረት ቴዎድሮስ (2001)፣ ይህ የህልውና ፍልስፍና ሁለንተናዊነት ያለው ማህበራዊ ክስተት በመሆኑ በየትኛውም ስፍራ፣ በማንኛውም ዓውድ ሊነሳ የሚችል ማህበራዊ እና ሰብዓዊ የህልውና ጥያቄ መሆኑን ጠቅሰው፣ ማንኛውም ህልው ሥርዓት ከዚህ የአስተሳሰብ ዘይቤ ሊወጣ እንደማይችል በአንክሮ ያስቀምጣሉ፡፡ በዚህ ሃሳብ መነሻነትም ከሥነጽሑፍ ኪን ጋር ላለው ዝምድና ሁለት አበይት ምክንያቶችን ያስቀመጡ ሲሆን፤ የመጀመሪያው የዘመናዊ የነገረ ህላዌ ፍልስፍና መሠረት የተጣለው በራሱ በሥነጽሑፍ ኪን ውስጥ ነው የሚል ሲሆን፤ የሁለተኛው ደግሞ፣ ዓበይት የፍልስፍናው አቀንቃኞች የተለያዩ የሥነጽሑፍ ከያኒያን ከመሆናቸውም በላይ በተለያዩ የሥነጽሑፍ ሥራዎቻቸው ታላቅ ክብር እና ዝና የነበራቸው

ታላላቅ ደራሲያን እና ጸሐፊ ተውኔቶች መሆናቸው ነው በማለት፣ ከAzhar (2013) እና ከWirahadi (2008) ትንታኔ ጋር ተዛማጅ የሆነ ሃሳባቸውን ያራምዳሉ፡፡

ከቴዎድሮስ (2001)፣ Azhar (2013) እና Wirahadi (2008) ማብረራሪያ፣ መነሻውን ከአውሮፓ ያደረገው እና ሥፊ መጠነርዕይ ያለው የዘመናዊ የሰው ልጅ የህልውና ፍልስፍና እንደየትኛውም የዓለም አገራት ሁሉ በእኛ አገር የአማርኛ ሥነጽሑፍ ላይም የራሱን አሻራ ማሳረፉ አይቀርምና፤ ይህ ጥናትም ይህን ከሥነጽሑፍ ጋር ያለውን ቅርብ ዝምድና ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ በዚህ ፍልስፍናዊ እሳቤ ዋነኛ የመተንተኛ መነጽርነት የሚጠቀም ይሆናል፡፡ ይህ የነገረህላዌ ፍልስፍና ከሥነጽሑፍ ጋር ያለውን ጥብቅ ቁርኝት በተመለከተ ደግሞ ከላይ በጥቂቱ ጠቆም ያደረኩት፣ "የህልውና ጥያቄ በየትኛውም ሥፍራ፣ በማንኛውም ዘመን ሊነሳ የሚችል ሰብዓዊ እና ማህበራዊ ጥያቄ በመሆኑ የትኛውም ህልው ሥርዓት ከዚህ አይነቱ የአስተሳሰብ ዘይቤ ውጭ ሊሆን አይችልም" የሚለው የቴዎድሮስ (2001፤ 144) ሐተታ በሚገባ ያጠነክረዋል፡፡

ሁሉንም የሰው ልጆች የህልውና መልኮች አንድ በአንድ ለመዘርዘር አስቸጋሪ ቢሆንም፤ አብዛኛዎቹ የፍልስፍናው አራማጆች ደጋግመው ከሚያነሷቸው እና ከተለመዱት የነገረ ህላዌ ጭብጦች መካከል ግን ከማንነት የቀደመ ህልውና (Existence precedes essence)፣ ነጻነት፣ ምርጫ እና ኃላፊነት (Freedom, Choice and Responsibility)፣ ሁኔታዊነት (Situatedness)፣ ጭንቀት፣ ስጋት እና ቀቢጸተስፋ (Anxiety, Dread and Despair)፣ ባይታወርነት (Alienation)፣ ምንምነት? (Nothingness)፣ ኦናነት (Forlornness)፣ ሞት (Death)፣ እውናዊነት እና ኢ- እውናዊነት (Authenticity and inauthenticity)፣ ከንቱነት (Absurdity)፣ ግላዊነት (Individualism)፣ ክስተት (Facticity)፣ ኢ- አሳባዊነት? (Anti-intellectualism)፣ አሳባዊነት? (Intentionality) ወዘተ የሚሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡ እነዚህ እና ሌሎችም የነገረህላዌ ጭብጦች እርስ በእርስ የተዛመዱ እና የተዋለዱ በመሆናቸው በተለያዩ አካላት ዘንድ ከስያሜ ልዩነት በዘለለ ተያያዥ የሆኑ ጉደዮችን ይዘው ሲመጡ ማስተዋልም አዲስ ነገር አይደለም፡፡ እንዲያውም አንዳንዶቹ የምክንያት እና ውጤት ያክል ዝምድና ያላቸው በመሆናቸው አንዱ ሲነሳ ሌላውንም እየጠራ ሰንሰለታዊ አካሄድ ሊሄድ የሚችልበት አጋጣሚም ብዙ ነው፡፡

የአማርኛ ሥነጽሑፍ በርካታ ዘውጎችን ያቀፈ፣ ሠፊ እና ዘርፈ ብዙ በመሆኑ ይህ ጥናት በረጅም ልቦለድ ዘውግ ላይ ያነጣጠረ ሲሆን፣ ይህ የሥነ ጽሑፍ ዘውግ ደግሞ በ20ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ላይ በሃገራችን ብቅ ያለ እና ዛሬም ድረስ የዘለቀ አንዱ እና (ምናልባትም ዋናው?) የሥነ ጽሑፍ ዘርፍ ነው፡፡ የህይወት ማሳያነቱ እና የይዘት ትኩረቱ ስፋት ደግሞ ይህን ዘውግ ለበርካታ ጥናቶች ማሄጃነት ተመራጭ እንዲሆን ያደርገዋል የሚል እምነትም አለኝ (ለዚህም ነው ወደዚሁ ዘውግ ማዘንበሌ)፡፡ ይህ ከሥነ ጽሑፍ አብራክ የተወለደ የረጅም ልቦለድ ጥበብ በየዘመኑ የሚከሰቱ የሰው ልጆችን ፈርጀ ብዙ ጉዳዮች መነሻ በማድረግ ይቀነበባል፡፡ የሚከየንበት ስልትም ቢሆን በደራሲው ዕውቀት፣ ልምድ፣ ችሎታ እና ፍልስፍና ልክ በመሆኑ ቀደም ብየ እንደጠቆምኩት ይህንን ዘውግ በቅርጽም ሆነ በይዘት በብዙ መልኩ ለምርምር ክፍት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

በዚህ ጥናት ለምርመር የተመረጠው የደራሲ አዳም ረታ ሥራ የሆነው እና በቅርቡ ለንባብ የበቃው *ሐፍ (2010 ዓ.ም.)* የተሰኘው ረጅም ልቦለድ ሲሆን፣ ጥናቱም በዚሁ ልቦለድ ውስጥ የተንፀባረቁ ልዩልዩ የሰው ልጆችን ህልውናዊ ገፅታዎች በመፈተሽ ከላይ  በተቀመጠው የነገረ ህላዌ ፍልስፍና ጽንሰሃሳብ መሠረት ተንትኖ ለማሳየት ብሎም ልቦለዱ ከዚሁ ከነገረህላዌ ፍልስፍና ጋር ያለውን ግንኙነት ለመግለጥ አልሞ የተነሳ ነው፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ደግሞ ከላይ ከተጠቀሱት እና ሌሎችም ተጨማሪ የነገረህላዌ ጭብጦች መካከል በልቦለዱ ውስጥ የቀረቡት ገናን ጭብጦች የትኞቹ እንደሆኑ፣ የቀረቡበት ስልት ምን እንደሚመስል ብሎም እርስ በእርስ ያላቸው ዝምድን ምን እንደሚመስል ይዳስሳል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አንዳንድ የአማርኛ ሥነጽሑፍ ሥራዎች (በተለይ ደግሞ ረጅም እና አጭር ልቦለዶች) ከነገረህላዌ ንድፈ ሃሳብ አንፃር በተለያዩ ጊዜያት እና በተለያዩ አካላት አማካኝነት ከዚህ ጥናት መካሄድ በፊት እንደተተነተኑ አጥኚው ባደረገው የቀደምት ጥናቶች ክለሳ አረጋግጧል፡፡ በዚህም መሰረት ከዚህ ቀድሞ በአማርኛ ልቦለድ ላይ ከተካሄዱ የህልውናዊነት ጥናቶች መካከል፡- የመሰለች ተሻገር (2010) በአለማየሁ ገላጋይ ቅበላ እና ኩርቢት ልቦለዶች፣ የቴዎድሮስ ገብሬ (2001) በፍቅር እስከ መቃብር፣ አደፍርስ፣ የቴዎድሮስ እንባ እና ከአድማስ ባሻገር፣ የአክሊሉ ደሳለኝ (2010) በተመረጡ የአዳም ረታ ሥራዎች (ግራጫ ቃጭሎች፣ ኤልዛቤል፣ ስፊንክስ፣ ከልጀቷ፣ የአበቦች ታሪክ፣ የድንች

*መዋሲት እና እቴመይቴ)* እንዲሁም የፀደይ ወንድሙ (2007) በ*ፍቅር እስከ መቃብር፣ ከአድማስ ባሻገር እና ገራጫ ቃጭሎች* ላይ የተካሄዱ ጥናቶች ይጠቀሳሉ፡፡ በእነዚህ የአማርኛ የድርሰት ሥራዎች ላይ ይህን መሠል ህልውና ተኮር ጥናት መካሄዱ በእርግጥም ይህ የነገረህላዌ ንድፈ ሃሳብ ለአማርኛ ሥነጽሑፍ ዘርፍ እንግዳ ጉዳይ እንዳልሆነ እና ከዘርፉ ጋር ያለውን ዝምድናም ማሳያ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ በዚህ የሂስ መነፅርነት የደራሲ አዳም ረታ ቀደምት (ሌሎች) ሥራዎች ከዚህ በፊት በተለያዩ ጊዜያት ከአንድም ሁለት ጊዜ መተንተናቸው የደራሲው ሥራዎች ለነገረህላዌ ፍልስፍና ያላቸውን የበለጠ ቅርበት ሌላው አመላካች ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ መሰረት የዚሁ ደራሲ ሥራ የሆነው እና ለዚህ ጥናት የተመረጠው *አፍ (2010)* ረጅም ልቦለድም ልዩልዩ ሰብዓዊ እና የህልውና ጉዳዮችን አቀናጅቶ የያዘ ሥራ መሆኑን አጥኚው ባደረገው ጥልቅ ንባብ አስተውሏል፡፡

*አፍ* ረጅም ልቦለድ ምንም እንኳን ከሰውልጅ የህልውና ፍልስፍና ጋር በእጅጉ የተቀራኘ እና ለምርምር ክፍት ቢሆንም እስከ አሁን ግን ምንም አይነት ጥናት እና ምርምር ያልተካሄደበት ወይም ደግሞ በየትኛውም አይነት የሂሳዊ ትንታኔ መነፅር ያልታየ ረቂቅ ሥራ ሆኖ የቆየ ስለመሆኑ የዚህ ጥናት አጠኚ ባደረገው ዳሰሳ ማረጋገጥ ችሏል፡፡ ስለሆነም ይህን የተለያዩ ሰብዓዊ ጉዳዮች ማህደር የሆነ ልቦለዳዊ ሥራ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በመተንተን ራሱን (የልቦለድ አሃዱን) ከሰው ልጅ የህልውና ፍልስፍና ጋር ያለውን ቀጥተኛ ግንኙነት አጉልቶ ለማሳየት መፈለግ እና በዚህ ልቦለድ ናሙናነት ደግሞ የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ከህልውና ፍልስፍና ጋር ያለውን ተዛምዶ ለመግለጥ አብዝቶ መሻት ዋነኛው አነሳሽ ምክንያት ነው፡፡

## 1.3. ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች

የዚህ ጥናት አብይ ጥያቄ፣ ለምርምር የተመረጠው *አፍ (2010)* ረጅም ልቦለድ ከነገረህላዌ ፍልስፍና ጋር ምን አይነት ግንኙነት አለው? የሚል ሲሆን፤ ይህን አብይ ጥያቄ በተገቢው መንገድ ለመመለስ የሚያስችሉ ዝርዝር ጥያቄዎች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፤

1. በልቦለዱ ውስጥ የቀረቡት ገናን የነገረህላዌ ጭብጦች እነማን ናቸው?

2. በልቦለዱ ውስጥ ለቀረቡት የነገረህላዌ ጭብጦች መነሻቸው ወይም መሠረታቸው (ምንጫቸው) ምንድን ነው?

3. በልቦለዱ ውስጥ የቀረቡት የነገረህላዌ ጭብጦች እንዴት ባለ ስልት ተገልጸዋል?

4. በልቦለዱ ውስጥ የቀረቡት የነገረህላዌ ጭብጦች የእርስ በእርስ ተዛምዶስ ምን ይመስላል?

## 1.4. የጥናቱ ዓላማዎች

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ፣ ለምርምር የተመረጠው የአዳም ረታ *ሕፍ (2010)* ረጅም ልቦለድ ከነገረህላዌ ፍልስፍና ጋር ያለውን ግንኙነት መመርመር እና ማሳየት ነው፡፡ ይህን አብይ ዓላማ ለማሳካት የሚያስችሉ የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፤

1. በልቦለዱ ውስጥ የቀረቡት ገናን የነገረህላዌ ጭብጦች የትኞቹ እንደሆኑ መፈከር፡፡
2. በልቦለዱ ውስጥ የቀረቡት የነገረህላዌ ጭብጦች መነሻቸው ወይም መሠረታቸው ምን እነደሆነ ማብራራት፡፡
3. በልቦለዱ ውስጥ የቀረቡት የነገረህላዌ ጭብጦች የተገለፁበትን ስልት መመርመር፡፡
4. በልቦለዱ ውስጥ የቀረቡትን የነገረህላዌ ጭብጦች የእርስ በእርስ ተዛምዶ ተንትኖ ማሳየት፡፡

## 1.5. የጥናቱ ፋይዳ

ይህ ጥናት ለምርምር በተመረጠው የአዳም ረታ *ሕፍ (2010)* ረጅም ልቦለድ ውስጥ የተንጸባረቁ የህልውናዊነት ጭብጦችን ለይቶ በማውጣት ተንትኖ የማሳየት እና ከነገረህላዌ ፍልስፍና ጋር ያለውን ግንኙነት የመግለጥ አብይ ዓላማን አንግቦ የተነሳ በመሆኑ፣ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች (እና ተጠቃሚዎች) ይኖሩታል፡፡

1. የልቦለዱን ሐተታ ወይም ጭብጥ ከነገረህላዌ ንድፈሃሳብ አንፃር በመተንተን እና በመግለጥ፣ ልቦለዱ በዚህ ጥናት ለሚነሱት የህልውናዊነት ጭብጦች እና መሰል ሰብዓዊ ጉዳዮች ማህደር መሆኑን በመጠቆም እንዲሁም አንዳች ቁምነገር ያዘለ

መሆኑን በማመላከት በሌሎች ተመራማሪዎች ዘንድ የተሻለ ዕይታ እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ ይኸውም ልቦለዱን ሌሎች ተመራማሪዎች ይህ ጥናት ባላየበት አቅጣጫ እንዲፈትሹት በማነቃቃት በአንድ በኩል፣ እራሱ ልቦለዱ ለሌሎች የጥናት እና ምርምር መስኮች ክፍት መድረክ እንደሆነ ጥቆማ ይሰጣል (በሌላ አንጻር እንዲመረመር በር ይከፍታል)፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ለተመራማሪዎች እንደ መነሻ ወይም መንደርደሪያ በመሆን ያገለግላል ማለት ነው፡፡

2. የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ንባብን ብሎም አጠቃላይ ዘርፉን ለሚያሳድጉ እና በተመሳሳይ መልኩ ለሚሠሩ ሌሎች ጥናቶች እንደማነቃቂያ ከመሆኑም ባሻገር በዘርፉ የእውቀት መስክ ላይ አንዳች ቁም ነገራዊ አሻራውንም በማሳረፍ የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ዘርፍ እና የአማርኛ ሥነ ጽፋዊ ጥናት እድገት አንድ እርምጃ ከፍ እንዲል የራሱ የሆነ ትልቅ እና አዎንታዊ የሆነ ሚና ይኖረዋል፡፡

3. ተደራሲያን ልቦለዱን በዚህ ጥናት መነሻነት ደጋግመው እንዲያነቡት እና እንዲያጣጥሙት በማድረግ አንድም የልቦለድ አሃዱን ተነባቢነት ከፍ ያደርጋል፤ አንድም ደግሞ በልቦለዱ ብሎም በሥነ ጽሑፍ ላይ ያላቸውን ግንዛቤ እና መረዳት በእጅጉ ይጨምራል ተብሎ ይታመናል፡፡

በአጠቃላይ ይህ ጥናት ለሌሎች ተመራማሪዎች ይህን መሰል የጥናት አቅጣጫን የመጠቆም፣ ለደራሲያን ተጨማሪ የይዘት ትኩረትን የማስተዋወቅ፣ ለተደራሲያን የሥነ ጽሑፋዊ ግንዛቤ ማዳበሪያ የመሆን እንዲሁም ለሥነ ጽሑፍ እና ለሥነ ጽሑፋዊ ጥናት ዘርፎች ተጨማሪ የመረጃ ማዕከል የመሆን አይነተኛ አስተዋጽኦ አለው የሚል ጽኑ እምነት አለኝ፡፡

## 1.6. የጥናቱ ገደብ እና ውስንነት

ይህ ጥናት በዋናነት ለምርምር የተመረጠው ሐፍ ረጅም ልቦለድ ከነገረህላዌ ፍልስፍና ጋር ያለውን ግንኙነት በመርመር በዚህ ናሙናነት ደግሞ የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ከዚሁ የህልውና ፍልስፍና ጋር ያለውን ተዛሞዶ ለመግለጥ የሚሞክር ይሆናል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ደግሞ ለምርምር በተመረጠው ረጅም ልቦለድ ውስጥ ተመላልሰው የሚከሰቱ ልዩ ልዩ የህልውና ገጽታዎች (የነገረህላዌ ጭብጦች) እነማን እንደሆኑ፣ እነዚህ ጭብጦች

እንዴት ባለ ስልት እንደቀረቡ፣ መነሻ ምንጫቸው ምን እንደሆነ እና እርስ በእርስ ያላቸው ዝምድና ምን እንደሚመስል ይፈትሻል፡፡ እነዚህን ጉዳዮች (የነገረህላዌ ጭብጦች) ለመፈተሽ ደግሞ የእውኑ አለም ነጸብራቅ የሆኑትን የገፀባህርያትን ህላዌ በጥልቀት እና በስፋት መቃኘትን ይጠይቃል፡፡ ስለሆነም የገፀባህርያትን ህላዌ በተለያዩ አቅጣጫዎች በውል ለመቃኘት ያስችል ዘንድ ከበርካታ የሥነጽሑፍ ዘርፎች መካከል የአማርኛ ረጅም ልቦለድ ዘውግን ምርጫው አድርጓል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ቀደም ሲል በጥናቱ ዳራ ላይ እንደተጠቆመው የእውኑን ዓለም ሰዎች ህላዌ በተመሳስሎ በመቅረፅ እና በስፋት በማሳየት ረገድ ከሌሎች የሥነ ጽሑፍ ዘውጎች ይልቅ ልቦለድ በተለይም ደግሞ ረጅም ልቦለድ ትልቁን ድርሻ እንደሚወስድ የዚህ ጥናት አጥኚ በጽኑ ያምናልና ነው፡፡ በዚህ መሠረት ይህ የምርምር ሥራ በዚሁ በረጅም ልቦለድ ዘውግ ላይ ብቻ በመወሰን ከበርካታ የአማርኛ ረጅም ልቦለዶች መካከል ደግሞ ጥናቱ አንግቦት የተነሳውን ዋነኛ ጉዳይ በተሻለ ያሳያል ተብሎ በታመነበት እና በ2010 ዓ.ም. ለንባብ በበቃው የደራሲ አዳም ረታ*አፍ* ረጅም ልቦለድ ላይ ብቻ ትኩረቱን አሳርፏል፡፡ ይህ ረጅም ልቦለድ ከዚህ አቀስድሞ ምንም አይነት ጥናት እና ምርምር ያልተካሄደበት ከመሆኑም በላይ ለዚህ ጥናት ዐውድ በይበልጥ አመቺ ሆኖ በመገኘቱ ጥናቱ በዚሁ ልቦለድ ላይ የተገደበ ሆኗል፡፡ በሌላ አገላለጽ *አፍ (2010)* ረጅም ልቦለድ፣ በዚህ ጥናት ዓብይ ጉዳይ አንጻርነት ወይም ደራሲው በዚሁ ረጅም ልቦለድ ውስጥ በጭብጥነት ባነሳቸው ልዩ ልዩ ህልውናዊ ፅንሰሃሳቦች እና ማህበራዊ እውነታዎች መሠረትነት የዚህ ጥናት ብቸኛ ምርጫ ሆኗል ማለት ነው፡፡ እናም በዚህ ጥናት ውስጥ *አፍ (2010)* ረጅም ልቦለድ የሚያትታቸውን ህልውናዊ መልኮች በነገረህላዌ ፍልስፍና ዋነኛ ማናበቢያነት በጥልቅ እና በተደጋጋሚ ንባብ በመፈተሽ ልዩ ልዩ የነገረህላዌ ጭብጦች ተለይተው እና ተተንትነው ይቀርቡበታል፡፡ ከዚህ አንጻር ደግሞ በዚህ ጥናት ውስጥ ለምርምር ለተመረጠው አፍ (2010) ረጅም ልቦለድ መተርጎሚያነት የሚውለው ንድፈሃሳባዊ አቅጣጫ የነገረህላዌ ፍልስፍና (Existentialism) ይሆናል ማለት ነው፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ጥናቱ ለሚያነሳቸው ልዩ ልዩ የህልውናዊነት ጭብጦች መከሰቻቸው ይኸው የሰው ልጆች የህላዌ ፍልስፍና በመሆኑ እና የሚመዘዙትም ከዚሁ ፍልስፍና ስለሆነ፣ በዚህ ፍልስፍዊ ንድፈሃሳብ መነፅርነት በጭብጦቹ ፍካሬ ላይ ያነጠጥራል፡፡

የአንድን ልቦለድ ጭብጥ ለመተንተን ሲታሰብ በልቦለዱ ኪናዊ እሴት መታገጊያነት በርካታ ማህበረ ፖለቲካዊ ጉዳዮችን ማንሳት ይቻል ነበር፡፡ ምንም እንኳን የዘመኑን እውነታ ቸል ብሎ በልቦለድ ኪናዊ እሴት ላይ ብቻ የሚያተኩር ጥናት ሙሉ ባይሆንም (ቴዎድሮስ 2001)፤ ይህ ጥናት ግን ለምርምር ማሄጃነት በተመረጠው ልቦለድ ውስጥ የተንጸባረቁ እና ልቦለዱ በተከየነበት ዘመን የሚቀነቀኑ ሌሎች ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሥነልቦናዊ እና መሰል ጉዳዮችን አጉልቶ ከማሳየት ወይም የልቦለዱን ማህበረፖለቲካዊ ፋይዳ ከመመርመር ይልቅ በልቦለዱ ኪናዊ እሴት ላይ ማለትም ልቦለዱ በሚያትታቸው ህልውናዊ ጉዳዮች ላይ ብቻ የተገደበ ሆኗል፡፡ በሌላ አባባል እነዚህን ቀደም ሲል የተጠቆሙትን ዝርዝር ጉዳዮች ወይም የልቦለዱን ማህበረፖለቲካዊ ፋይዳ በግልጽ እና በስፋት ማሳየት ሳይቻል ቀርቷል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ደግሞ ልቦለዱን ለግል ትርጓሜ ማጋለጥ እንዳይሆን በመስጋት ነው፡፡ ታዲያ ይህ ጉዳይ ደግሞ የዚህ ጥናት የመጀመሪው ውሱንነት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ፣ ይህ ጥናት በአንድ ንድፈ ሃሳብ (በነገረህላዌ ፍልስፍና) ላይ ብቻ የተወሰነ እንደሆነ ከፍ ሲል ተገልጧል፡፡ ይህ ደግሞ ተገቢነቱ እምብዛም ስለመሆኑ ቴዎድሮስ (2001፤ 136) እንዲህ ያስነብቡናል "በአንድ ፍጹም ነጠላ ንድፈ ሐሳብ ላይ ብቻ ተወስኖ ሥነ ጽሑፋዊ ምርምርን ለማካሄድ መሞከር ማለት፣ በሥነ ጽሁፋዊ ትችት እና ንድፈ ሐሳብ ውስጥ ዘወትር ለሚወገዙ ሁለት ሕጸጾችን- ከልክ ያለፈ የቀንጻይነት (...) ሕጸጽ እና ቴክስትን የንድፈ ሐሳብ 'ባሪያ' የማድረግ ሕጸጽ- ለመፈፀም መፍቀድ ነው የሚሆነው"፡፡ ቢሆንም ይህ ጥናት ግን ለተመረጠው ቴክስት ማናበቢያነት ይሆኑ ዘንድ ሌሎች ተጨማሪ ንድፈ ሃሳቦችን አይጠቀምም፡፡ ምክንያቱ ደግሞ አንደኛ፣ ከላይ እንደተነሳው ለማናቢያነት የተመረጠው ብቸኛ ፍልስፍናዊ ንድፈሃሳብ በጥናቱ ውስጥ በዋናነት ከሚነሱት መሠረታዊ ጉዳዮች ጋር ካለው የጠበቀ ቁርኝት ወይም ከጥናቱ ዓላማ አንጻር ሲሆን፤ ሌላው እና ሁለተኛው ደግሞ፣ አጥኚው ሌሎችን ተጨማሪ ንድፈሃሳቦች እንዳስፈላጊነቱ ገርቶ እና አላምዶ በዚህ ጥናት ውስጥ ለመጠቀም አስቦ የነበረ ቢሆንም ካጋጠመው የጊዜ ውሱንነት አንጻር ይህን ማድረግ ሳይችል ቀርቷል፡፡ ይህ ደግሞ ሌላው እና ሁተኛው የዚህ ጥናት ውሱንነት ነው፡፡

## 1.7. የጥናቱ ሥነዘዴ

በዚህ ንዑስ ክፍል ውስጥ ደግሞ ረጅም ልቦለዱ የተመረጠበት መመዘኛ፣ በጥናቱ ውስጥ መረጃ ለማሰባሰብ የሚረዱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፣ የጥናቱ ዘዴ (ስልት) እና የመረጃ አተናተን ስልት እና ሂደት የሚሉት ጉዳዮች ይቀርቡበታል፡፡

### 1.7.1. ረጅም ልቦለዱ የተመረጠበት መመዘኛ

ይህ ጥናት በዋናነት ይዞት የተነሳው ዓብይ ጉዳይ፣ የህልውናዊነት ጭብጦች ለጥናት በተመረጠው ረጅም ልቦለድ ውስጥ ያላቸውን (የተሰጣቸውን) ቦታ በመፈተሽ ልቦለዱ ከነገረህላዌ ፍልስፍና ጋር ያለውን ግንኙነት መመርመር እና በዚህ ናሙናነት ደግሞ የአማርኛ ሥነጽሑፍ ከዚህ የህልውና ፍልስፍና ጋር ያለውን ዝምድና መግለጥ ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህ ጭብጦች በስፋት ተንጸባርቀውበታል ተብሎ የታመነበት እና ጭብጦቹንም ለይቶ ለማሳየት አመቺ ይሆናል ተብሎ የታሰበው *ሐፍ (2010)* ረጅም ልቦለድ ሲሆን፣ ይኸውም የጥናቱን ዓላማ መሰረት አድርጎ ተመርጧል፡፡ ስለዚህ ለዚህ ጥናት ማሂጃነት የተመረጠው ልቦለድ በውስጡ የያዛቸውን ህልውናዊ ይዘቶች መሰረት በማድረግ እነዚህን የህልውና ገጽታዎች ደግሞ ለይቶ እና ተንትኖ ለማሳየት ያስችላል በሚል እምነት በዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ (Purposive sampling method) የተመረጠ ነው ማለት ነው፡፡ በሌላ አባባል አጥኚው ይህን ሐፍ (2010) ረጅም ልቦለድ ባነበበበት ወቅት፣ በተዋቀረባቸው ታሪኮች እና በገፀ ባህርያቱ ኑባሬ ውስጥ ከዚህ አስቀድሞ ካነበባቸው ሌሎች ልቦለዶች በተሻለ ልዩ ልዩ ህልውናዊ ጉዳዮችን አስተውሏል፡፡ ይሁን እና የዚህ ጥናት አጥኚ እስካሁን ድረስ እነዚህን ህልውናዊ ጉዳዮች እና ይህን ልቦለድ በናሙናነት ወስዶ ያጠና አንድም አካል አላገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት እነዚህን ህልውናዊ ጉዳዮች ተንትኖ በጉልህ ለማሳየት ካደረበት ጽኑ ፍላጎት አንጻር ይህን ለማድረግ ይረዳ ዘንድ ደግሞ ሐፍ (2010) ረጅም ልቦለድን በናሙናነት መርጦታል፡፡

### 1.7.2. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ይህ ጥናት ለትንተናው ወሳኝ የሆኑ መረጃዎችን ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች የሚሰበስብ ሲሆን፣ እነዚህ የመረጃ ምንጮች ደግሞ ለዚህ ጥናት ካላቸው ቅርበት አንጻር በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ተመድበዋል፡፡ በዚህ መሰረት ለጥናቱ በአይነተኛ ማጠንጠኛነት የተመረጠው የአዳም ረታ ሐፍ (2010) ረጅም ልቦለድ በቀዳማይ የመረጃ ምንጭነት የሚያገለግል

ሲሆን፤ ስለነገረህላዌ ፍልስፍና፣ ጭብጦች እና መሰል ህልውናዊ ፅንሰሃሳቦች የሚያወሱ ሌሎች ልዩልዩ ድርሳናት እና መዛግብት እንዲሁም ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተያያዥነት ያላቸው ቀደምት ጥናቶች ደግሞ ካልዓይ የመረጃ ምንጭ ሆነው አገልግለዋል፡፡ እነዚህን በጽሑፍ የተሰነዱ ቀዳማይ እና ካልዓይ የመረጃ ምንጮች (መዛግብት) በምንባባዊ የትንታኔ ስልት አማካኝነት በተደጋጋሚ እና በጥልቀት በማንበብ ለጥናቱ ይበጃሉ ተብሎ የታመነባቸው መረጃዎች ሁሉ ተሰብስበዋል፡፡ እንግዲህ ከዚህ አንጻር፣ በዚህ ጥናት ውስጥ ሥራ ላይ የሚውለው ምንባባዊ የትንታኔ ስልት ወይም የሰነድ (Document) ፍተሻ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ሆኗል ማለት ነው፡፡

### 1.7.3. የጥናቱ ዘዴ (ስልት)

የሰው ልጆች በህይወት ዘመናቸው ውስጥ ራሳቸውን ለማሻሻል ሲሉ በበርካታ ጉዳዮች ይጠመዳሉ፤ ይለፋሉ፤ ይደክማሉ፡፡ የህልውና ጭብጣዊ ገጽታዎች የሚባሉትም እነዚሁ በሰው ልጅ ህልውና ላይ የተመሰረቱ እና በሰዎች ህላዌ ውስጥ ተመላልሰው የሚመጡ ሁነቶች ናቸው፡፡ በአለም ላይ ካሉ እና ተፈጥሯዊ ከሆኑ ሌሎች ነገሮች ሁሉ ይልቅ ዋና ጉዳዩን በሰው ልጆች አጠቃላይ የህይወት ገጽታ ላይ በማድረግ የሚታወቀው እንደዚሁም እነዚህን የሰው ልጆች ራስን የማሻሻል ዑደታዊ የሆኑ ከፍተኛ ፍላጎቶች ለመመርመር የበለጠ ምቹ እና ተመራጭ የሚሆነው ንድፈሃሳብ ደግሞ የነገረህላዌ ፍልስፍና (Existentialism) ነው፤ እነዚሁ የተለያዩ የህልውናዊነት ጭብጦችም የሚመዘዙት ከዚሁ የህልውና ፍልስፍና ውስጥ ነው፡፡ ስለሆነም "የህልውናዊነት ጭብጦች በአዳም ረታ ሶፍ ውስጥ" የሚል ርዕስ ይዞ የተነሳው ይህ ጥናት ይህንኑ የነገረህላዌ ፍልስፍና በዋና መተንተኛነት በመጠቀም ለጥናት የተመረጠው ልቦለድ በፈጠረው ዓለም ውስጥ የሚኖሩ የሰው ልጅ ወኪል ገፀ ባህርያትን ህልውናዊ ሐተታዎች ለይቶ ተንትኗል፡፡

### 1.7.4. የመረጃ አተናተን ስልት እና ሂደት

በምርምር ሂደት ውስጥ ናሙና መምረጥ፣ መረጃ መሰብሰብ እና የመረጃ መተንተኛ ዘዴን መወሰን ብቻውን ከግብ እንደማያደርስ በማመን፤ ይህ "የህልውናዊነት ጭብጦች በአዳም ረታ ሶፍ ውስጥ" የተሰኘ አይነታዊ ጥናት በሚከተሉት ሂደቶች ውስጥ አልፏል፡፡

ይህ ጥናት በቅድሚያ ለትንተናው ይበጃሉ ያላቸውን መረጃዎች ሁሉ በቤተ-መጻሕፍት ውስጥ አሊያም በመረጃነት ተሰንደው የሚገኙ ልዩ ልዩ መዛግብትን በማገላበጥ እና

በጥልቀት በማንበብ ከያሉበት አፈላልጎ አሰባስቧል፡፡ ታዲያ የተሰበሰቡት መረጃዎች ሁሉ ሙሉ በሙሉ ለትንተና ይቀርባሉ ወይም ይተነተናሉ ማለት አይደለምና፣ ይህ ጥናት ላስቀመጠው ግብ ያላቸውን አስፈላጊነት በውል መዝኖ ከተሰበሰቡት መረጃዎች መካከል በጣም ወሳኝነት ያላቸውን ብቻ መርጧል፡፡ እነዚህ የተመረጡት መረጃዎች ደግሞ ለጥናቱ መተንተኛ ይሆን ዘንድ ከተወሰነው ንድፈሃሳብ ወይም የመተንተኛ ስልት (የነገረህላዌ ፍልስፍና) ጋር በማናበብ እና በማገናዘብ በመልክ-በመልክ አደራጅቷል፡፡ በመጨረሻም ግልጽ እና ተጨባጭ በሆነ መንገድ በመተንተን ለመሪ ጥያቄዎቹ ምላሽ ሰጥቷል፣ አንግቦት የተነሳውን ዓላማም ማሳካት ችሏል፡፡

## 1.8. የምዕራፍ አደረጃጀት

ይህ ጥናት በአራት ዋና ዋና ምዕራፎች የተከፋፈለ ሲሆን፣ ምዕራፍ አንድ የጥናቱን ዳራ፣ የጥናቱን አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱን የምርምር ጥያቄዎች፣ የጥናቱን ዓላማዎች፣ የጥናቱን ጠቀሜታ (ፋይዳ)፣ የጥናቱን  ወሰን (ገደብ) እና ውስንነቶች እንዲሁም የጥናቱን ሥነ ዘዴ አካቶ ይዟል፡፡

ምዕራፍ ሁለት ደግሞ በዋናነት  የጥናቱ ማዕከላዊ ጉዳይ የሚተነተንበትን የንድፈ ሃሳባዊ ጽሑፍ ክለሳ እና የቀደምት ጥናቶች ክለሳን ያካተተ ሲሆን፣ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የነገረህላዌ ንድፈ ሃሳብ እና የህልውናዊነት ጭብጦች ፅንሰ ሃሳባዊ ትንተና እንደዚሁም የቀደምት ጥናቶች ክለሳ የተካሄደባቸው ንዑሳን ርዕሶች ቀርበውበታል፡፡

ምዕራፍ ሦስት "የህልውናዊነት ጭብጦች ትንተና በሖፍ ውስጥ" በሚል ርዕሰ ጉዳይ ስር አምስት ንዑሳን ርዕሶች የተነሱ ሲሆን፣ እነዚህም፡ ነጻነት እና ኃላፊነት፣ ኦናነት፣ ሁኔታዊነት፣ የርእይ መነጠቅ እና ቀቢጸ ተስፋ የሚሉት ናቸው፡፡ ይኸውም ለትንተና በተመረጠው ሖፍ ረጅም ልቦለድ ውስጥ በተንፀባረቁት የህልውናዊነት ጭብጦች ላይ የተደረገውን ትንታኔ የያዘ ምዕራፍ ነው፡፡

አራተኛው እና የመጨረሻው ምዕራፍ ደግሞ ከዚህ ምዕራፍ አሰቀድሞ በነበሩት ሦስት ምዕራፎች ውስጥ የተነሱት ጉዳዮች በማጠቃለያ የቀረበበት ክፍል ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# የተዛማጅ ጽሑፍ ክለሳ

## 2.1 የንድፈ-ሃሳባዊ ጽሑፍ ክለሳ

### 2.1.1. ነገረህላዌ

ስለ ነገረህላዌ (Existentialism) ምንነት ቁርጥ ያለ እና ሁሉን አቀፍ የሆነ ትንታኔ ማግኘት በእጅጉ አስቸጋሪ ነው፡፡ በርካታ ተመራማሪዎችም ስለዚህ ፍልስፍና ትርጓሜ ውስብስብነት ሲገልጹ ማስተዋል ብርቅ ነገር አይደለም፡፡ እያንዳንዱ በዚህ የፍልስፍና ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ምሁራን ወይም ተመራማሪዎች እንደሚያገኙት የመረጃ ምንጭ እንዲሁም እንዳላቸው የግንዛቤ፣ የአመለካከት፣ የእምነት፣ የፍልስፍና እና የዕውቀት ልክ በየወቅቱ የተለያዩ ሃሳቦችን ያራምዳሉ (Azhar, 2013)፡፡ በዚህ ምክንያት፣ አብዛኛዎቹ ተመራማሪዎች ራሳቸው ስለዚህ ፍልስፍናዊ እሳቤ አንድ አይነት ትርጓሜ እና ታሪክ አለመኖር ያስቀምጣሉ (Flynn, 2006)፡፡ ይሁን እንጅ ስለዘርፉ የተሰነዘሩት ትርጓሜዎች ሁሉ ሙሉ በሙሉ የተራራቁ እና ምንም ግንኙነት የሌላቸው ናቸው ማለት በፍጹም አይደለም፡፡ ይልቁንም ተቀራራቢ እና ወደ አንድ አይነት ፅንሰ ሃሳብ የሚመሩ ከመሆናቸውም የተነሳ "ነገረህላዌ በሰው ልጆች ሁለንተናዊ ህይወት ላይ መሰረት ያደረገ የህልውና ፍልስፍና ነው" የሚለውን ብያኔ አብዛኛዎቹ ልሂቃን የሚጋሩት እና የሚያራምዱት ሃሳብ ነው፡፡ ምክንያቱ ደግሞ፣ ይህ የፍልስፍና እሳቤ "በእያንዳንዱ ግለሰብ ህልውናዊ ሁኔታ (Condition of existence of the individual person)፣ ስሜት (emotion)፣ ድርጊት (action)፣ ኃላፊነት (responsibility)፣ አስተሳሰብ (thought) እና በእያንዳንዱ የሰው ልጅ የህልውና ጥያቄ ላይ ያነጣጠረ ፍልስፍናዊ እሳቤ" ስለመሆኑ ሁሉም እንደሚስማሙ Azhar (2013) ያስረዳሉ፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ቴዎድሮስ ገብሬ (2001)፣ የነገረህላዌ ፍልስፍናን አስመልቶ የሚሰነዘሩ ሃሳቦች የተለያዩ ነገር ግን የማይራራቁ መሆናቸውን ገልጸው፣ በዚህ ፍልስፍናዊ እሳቤ ላይ የተሰማሩ ፈላስፋዎችን እና የሚሰነዘሯቸውን የብያኔ ሃሳቦች ተመሳስሎ ያመለክታሉ ያሏቸውን ሦስት ዓበይት ጉዳች ያስቀምጣሉ፡፡ በዚህ መሠረት የመጀመሪያው፣ ከፍ ሲል

እንደተጠቆመው የሁሉም የነገረህላዌ ፈላስፋዎች ማዕከላዊ ጉዳይ የሰው ልጅ መሆኑ ሲሆን፣ በሁለተኛነት የሚያስቀምጡት ደግሞ በሁለተኛው የአለም ጦርነት ሳቢያ ሰዎች ላጧቸው የጋራ ቁሳዊ እና መንፈሳዊ እሴቶች ምላሽ በሚሆኑ ጉዳዮች እና የወደፊት ዕጣ ፋንታን በመተንበይ ላይ ማተኮራቸው እንደሆነ ያብራራሉ፡፡ ይኸውም አብዛኛዎቹ የዘርፉ ታላላቅ እና ተጽዕኖ ፈጣሪ ፈላስፋዎች እና ጸሐፊያን ብቅ ያሉት የሁለተኛውን የዓለም ጦርነት ተከትለው መሆኑ እና በወቅቱ በሥራዎቻቸው ያስተጋቧቸው የነበሩ መልክዕቶች ደግሞ የጦርነቱን ክስተቶች የነበረ መሆኑን ለማመልከት ነው፡፡ ሌላው እና ሦስተኛው ደግሞ፣ የአብዛኛዎቹ ፈላስፋዎች የጭብጥ ምርጫ መመሳሰል መሆኑን ይገልጣሉ፡፡ Azhar (2013)ም ቢሆኑ፣ በቁጥር ወስነው አያስቀምጧቸው እንጅ እነዚህን ጉዳዮች ይጋራሉ፡፡

Robert Solomon (2003; 175-176)፣ ደግሞ "አጽንኦቱን በህልውና ላይ ያደረገ ፍልስፍና ነው" ካሉ በኋላ፣ ህልውና  ሲባል ደግሞ ከየትኛውም ረቂቅ እና ከሰው ውጭ ከሆኑ ነገሮች በተቃራኒ በሰው ልጅ ላይ ብቻ የተወሰነ ከመሆኑም ባለፈ ከእያንዳንዱ ሰው ተናጠላዊ ህልውና ላይ ብቻ ያነጣጠረ እንጅ ህብረ-ህልውና እንዳልሆነ እንዲህ በሰፊው ያስነብቡናል፤ "[…] it is the philosophy puts the emphasison existence (in opposition to any number of abstract and impersonal conceptions of meaning and human life) […] existence refers to personal, individual existence rather than collective existence"፡፡

ከፍ ሲል ለማንሳት እንደተሞከረው Azhar (2013) በዚህ ፍልስፍናዊ እሳቤ ዙሪያ የሚሰጡ በርካታ ትርጓሜዎች መኖራቸውን ጠቅሰው፣ ከእነዚህ መካከል ደግሞ የተወሰኑትን ምሁራን እና ስለዚሁ ፍልስፍና ያስቀመጧቸውን ፍቺዎች እንደሚከተለው በቀጥታ አስፍረዋል፡፡

ነገረ ህላዌ ከሌላው ተፈጥሮ ይልቅ አጽንኦቱን በሰው ልጆች ልዩ ልዩ ህልውናዊ መልኮች ላይ ያሳረፈ ከመሆኑም በላይ በእያንዳንዱ ግለሰብ ህላዌ ላይ ያነጣጠረ እሳቤ ነው ('Existentialism is an attitude and outlook which emphasizes human existence and the qualities which are distinctive in the individual persons rather than man in abstract or nature and the world in genral') (Titus, 1959; 290)፡፡

ነገረ ህላዌ ሁለት ዋና ዋና ጭብጦችን ማለትም የሰው ልጆችን የህልውና ትንተና (analysis of human existence) እና ምርጫ የሚጠቁም የፍልስፍና እንቅስቃሴ ነው

(“Existentialism is a ‘philosophical movement oriented twoards two major themes, the analysis of human choice’”) (Stevens, 2000; 556)፡፡

ነገረ ህላዌ የሰው ልጅ በቀደምቶቹ (Advanced) ቴክኖሎጂያዊ፣ ቁሳዊ እና ጠረኛ ማህበረሰቦች ውስጥ ያጧቸውን ሁነቶች እንደገና ለማረጋገጥ እና ለማግኘት የሚሞክሩበት መሠረታዊ ፍልስፍና ነው (‘Existentialism is essentially the philosophy of man and his attempt to reaffirm and regain the lost status of man in this advanced, thechnological and mechanized society’) (Taneja, 2005; 2008)፡፡

ነገረህላዌ የሰው ልጆች ህላዌ ተቀባይነት እንዲያገኝ እንደዚሁም ማንኛውም እውነት እና ድርጊት የሰው ልጆችን ግለሰባዊ ሁኔታ እንዲገልጽ የሚያደርግ እሳቤ ነው (‘By Existentialism we mean a doctrin which maks human life possible and addition, declares that every action implies a human setting and a human subjectivity’) (Cahn, 2012; 1192)፡፡

እንግዲህ ከዚህ በላይ ከተወሰዱት አጠቃላይ ብያኔዎች በመነሳት፣ ነገረህላዌ በህይወት ውስጥ ራስን ለማግኘት የሚደረግ ጥረት ወይም ደግሞ በነጻ ፍላጎት፣ ምርጫ እና ግለሰባዊ ኃላፊነት ውስጥ የህይወትን ትርጉም የመፈለግ የሰው ልጆች ወይም ደግሞ መሠረቱን በሰው ልጆች ህላዌ ላይ ያደረገ ፍልስፍናዊ እሳቤ ነው ተብሎ ሊገለጽ ይችላል፡፡

Mallah (2016) ደግሞ የሚከተለውን ያብራራሉ፤

> Existentialism is the only philosophy which considers individuality as a supreme…in general terms existentialism may be described as an attempt to reach the inmost core of human existence in a concreteand individual fashion. Therefore it is called a philosophy of a concrete man. (MALLAH, 2016; 2)
>
> ነገረህላዌ በግለሰቦች ትክክለኛ ህልውና ላይ ትኩረቱን በማሳረፍ የግለሰብዓዊነትን ገናንነት የሚያቀነቅን ብቸኛ የፍልስፍና መስክ ሊባል ይችላል፡፡ በግለሰቦች አጠቃላይ ህልውና ላይ በማነጣጠር እና ግለሰብዓዊነትን ዋና ጉዳዩ በማድረግ የሚካሄድ የፍልስፍና ዘርፍ በመሆኑም የትክክለኛ ሰውነት ፍልስፍና ተብሎም ሊጠራ ይችላል (Mallah, 2016; 2)፡፡

እንግዲህ ይህ የነገረህላዌ ፍልስፍና የግለሰቦችን ነጻነት እና ምርጫ አስፈላጊነት አጉልቶ በማሳየት ለእያንዳንዱ ህልውና፣ ነጻነት እና ምርጫ መከበር ዘብ የሚቆም ነው ማለት እንችላለን፡፡ እንደዚህ ዘርፍ እሳቤ እያንዳንዱ ሰው ወይም ግለሰብ በህይወቱ ውስጥ የራሱን እድል እራሱ የመወሰን እና የማራመድ እንደዚሁም የህይወት ጎዳናውን በራሱ አቅጣጫ የመምራት አቅምም ሆነ ስልጣን አለው፡፡ እያንዳንዱ የሰው ልጅ በተፈጥሮው ከሌሎች የተፈጥሮ አካላት በተለየ መልኩ ንቁ እና ፈጣሪ እንደዚሁም ተመራማሪ መሆኑ ለማናችንም የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡ በተቃራኒው ደግሞ ሌሎች የተፈጥሮ አካላት ከሰው ልጅ በተለየ መልኩ ቋሚ እና የማይለወጥ ማንነት ያላቸው ከመሆናቸውም በላይ ማድረግ የሚፈልጉትንም ይሁን የሚከውኑትን ማንኛውንም አይነት ድጊት የመምረጥ ነጻነት እና የራሳቸውን አለም እራሳቸው የመፍጠር ችሎታም ሆነ አቅም የላቸውም፡፡ ስለዚህ ለነገረህላዌያን (Existentialists) ለእነዚህ ሁሉ ጸጋዎች ብቸኛው ባለቤት የሰውልጅ ነው የሚል ፅኑ እምነት አላቸው፡፡

በአጠቃላይ ነገረህላዌ በሰው ልጅ የህልውና ምርምር ላይ ልዩ ትኩረት ያደረገ እና ሰዎች በቁሳዊው አለም (objective world) ወይም ተፈጥሯዊ አለም ላይ ሲኖሩ እራሳቸውን ለማግኘት አለፍ ሲልም ህላዌያቸውን ለማሻሻል የሚያልፉባቸውን ውጣውረድ መንገዶች የሚያጠና፣ የሚመረምር የ20ኛው ክፍለዘመን የፍልስፍና ጉዞ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም በቁሳዊው አለም ውስጥ እራስን የመፈለግ እና የማግኘት ወይም የህይወትን ትርጉም የመረዳት ፍልስፍና ነው ተብሎም ሊገለጽ ይችላል፡፡ ይህ የፍልስፍና መስክ ማንኛውም ሰው በአለም ላይ ሲኖር ከየትኛውም አይነት የህግ፣ የጎሳ ሥርዓት ወይም ማህበረባህላዊ ደንብ አስገዳጅነት (አጋዥነት?) ነጻ መሆን እንዳለበት ያምናል፡፡ እንደ ነገረህላዌ እሳቤ እያንዳንዱ የሰውልጅ የፈለገውን አመለካከት፣ እምነት፣ ሥርዓት በአጠቃላይ ሙሉ ማንነቱን የመፍጠር፣ የመገንባት እና የመከተል ሙሉ ስልጣኑ ለራሱ ለግለሰቡ ብቻ የተተወ መሆን አለበት፡፡ ስለዚህ በሰው ልጅ እራሱን በራሱ የመፍጠር ሂደት መካከል የትኛውም አይነት ቅድመ ሁኔታ ሊገድበውም ሆነ ጣልቃ ሊገባበት ፈጽሞ አይገባም የሚል እሳቤ ነው ማለት ነው፡፡ ለዚህም ነው ቀደም ሲል "ነገረህላዌ በህይወት ውስጥ ትክክለኛውን ማንነት (Self) የመፈለግ እና እውናዊውን ሠብዓዊ ትርጉም (Personal meaning) የመመርመር ጉዞ ነው ሊባል ይችለል" የተባለው፡፡ ይህን አስመልክተው Richard Kearney (1988; 196)ም፣ "ነገረህላዌ በሰውልጆች ላይ ብቻ

በመወሰን የህይወታቸውን ሁለንተናዊ ጉዳዮች የሚገልጽ ፍልስፍና ነው” በማለት ይህን ሃሳብ ያጠናክራሉ፡፡

### 2.1.2. የነገረህላዌ ፍልስፍና ታሪካዊ እድገት

በርግጥ ስለነገረ ህላዌ ፍልስፍና ወጥ የሆነ ታሪካዊ ዳራ ማስቀመጥ በእጅጉ አስቸጋሪ እንደሆነ በተለያዩ የዘርፉ ሊቃውንት ዋቢነት ከላይ ጠቁሜያለሁ፡፡ ከዚህ ባለፈ ግን ልክ እንደትረጓሜው ሁሉ ስለታሪካዊ እድገቱም የሚሰነዘሩት ሃሳቦች ተወራራሽ እንደሆኑ አሁንም ልብ ይሏል፡፡

Michael G. Cole B.A. (1975) እና Umar Wirahadi (2008)፣ ዘመናዊ የነገረህላዌ ፍልስፍና አዲስ እና ያልተለመደ የድህረጦርነት ክስተት አለመሆኑን ገልጸው፣ በ19ኛው ክፍለዘመን በዴንማርካዊው ፈላስፋ እና የሃይማኖት ጠቢብ Soren Kierkegaard አማካኝነት ሥራ ላይ መዋል እንደጀመረ ያትታሉ፡፡ እንደ Cole B.A.(1975) እና Wirahadi (2008) ሃሳብ፣ በእርግጥ ይህ የነገረህላዌ ፍልስፍና በተወሰነ መልኩ ያለማቋረጥ እያደገ የመጣው እና በሌሎች ታላላቅ ዘመናዊ ፈላስፋዎች እና ጸሐፊያን ዕይታ ውስጥ የገባው ከKierkegaard ወዲህ ነው፡፡ በተለይ Wirahadi (2008)፣ የነገረህላዌ ፍልስፍናዊ ጽንሰሃሳብ ከKierkegaard ቀጥሎ እነNietzsche፣ Martin Heidegger፣ karl Jaspers እና Jean-Paul Sartre ታላላቅ ሥራዎች ላይ እንደተንጸባረቀ ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ይህ ፍልስፍናዊ ጽንሰሃሳብ ቀደም ባሉት ታላላቅ ፈላስፋዎች ሲታይ የቆየ መሆኑን ጠቅሰው፣ ቀደምትነቱን ደግሞ ለ Blase Pascal ይሰጡታል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ Thomas Flynn (2006)፣ ይህ የሰው ልጅ የህልውና ፍልስፍና የጥቅሉን የፍልስፍናን (The philosophy itself) ያክል እድሜ ያሰቆጠረ እሳቤ እንደሆነ ያትታሉ፡፡ በዚህ መሠረት የምዕራባዊያንን ፍልስፍና እድሜ የተመለከትን እንደሆነ ደግሞ ወደ 6ኛው ዓ.ዓ (ቅድመ ልደተ ክርስቶስ) እንደሚወስደን Azhar (2013) ያስረዳሉ፡፡ ስለሆነም ከFlynn (2006) ሃሳብ፣ የነገረህላዌ ፍልስፍና መጀመር ወደዚያው እንደሚያመራ እና እራሱ ፍልስፍና ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ የነበረ እሳቤ እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡ የነገረህላዌ ፍልስፍና፣ የድህረ ጦርነት መልክ ይዞ ብቅ ያለ ቢመስልም የፍልስፍና ጉዳዮችን በማራመድ እና የሰው ልጆችን ህይወት በማንጸባረቅ ረገድ የራሱን የፍልስፍናን ያህል እድሜን ያሰቆጠረ ጉዳይ መሆኑን Flynn (2006) እንዲህ ያስረዳሉ፤ “If it bears the

marks of its post-war apearance, existentialism as a manner of doing philosophy and a way of addressing the issues that matter in people's lives is at least as old as a philosophy itself" (Flynn, 2006; ix)፡፡ ስለዚህ የነገረህላዌ ፍልስፍና ከ20ኛው ክፍለ ዘመን የሥነ ጽሑፍ ንድፊ ሃሳብነትም የላቀ እና ቀደምትነት ያለው የፍልስፍና ዘርፍም እንደነበረ ይኸው የFlynn ሃሳብ አይነተኛ ማስረጃ ነው፡፡

Stephen Michelman (2008) በበኩላቸው፣ ከ20ኛው ክፍለ ዘመን ቀደምት ናቸው ከምንላቸው የነገረህላዌ አስቦች መካከል የSartreን የህልውና እሳቤ ቀዳሚነት ለሚጠራጠሩ የ1950ዎቹ እና የ1960ዎቹ ሃሳባውያን አንዱ መከራከሪያቸው "የSartre የህልውናዊነት ፍልስፍና ዘሩ የተቀዳው ከቀደምቶቹ ታላላቅ ፈላስፎች ከእነ ሽክስፒር፣ ቅዱስ አውገስቲን እና ከሌሎች ቀደምት ቅዱሳን ሃሳብ ወይም ፍልስፍና በመሆኑ በእነርሱ ሩቅ እና ሰፊ ተፅዕኖ ስር የወደቀ ነው" የሚል ነው፡፡ ይኸውም "የSartre የህልውናዊነት ፍልስፍና በዚያን ወቅት ከነበረው የፍልስፍና እሳቤ የተቀዳ በመሆኑ በ20ኛው ክፍለ ዘመን ላለው የዘርፉ እሳቤ ፈር ቀዳጅ ነው ሊባል አይችልም" በማለት የሚቃረኑ ወገኖች የሚያራምዱት ሃሳብ ነው፡፡ ይህ ደግሞ አንድም ነገረህላዌ በፍልስፍና ታሪክ ውስጥ የነበረውን ቀደምትነት፣ አንድም ደግሞ ቀድሞውንም ቢሆን ይህ የፍልስፍና ዘርፍ ከሰው ልጅ ሁለንተናዊ ህላዌ እና ራስን የማወቅ ፍላጎት ጋር የተቆራኘ ፅንሰ ሃሳብ ይዞ የቆየ መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡

Baskaya (2011)ም የነገረህላዌ ፍልስፍና ከአርስቶትላውያን እሳቤ ጋር የተገናኘ እንደሆነ ገልጸው፣ እንደ አርሰቶትል እሳቤ ከሆነ ደግሞ አንድ እና አንድ ብቻ ቁሳዊ አካል የለም፤ ቁሳዊ አካል (Object) ወይም ደግሞ (ተፈጥሮ?) ስፍር ቁጥር የሌለው ወይም ወሰን የለሽ ነው፡፡ ነገር ግን እኛ መረዳት ወይም መገንዘብ የምንችለው የተወሰኑትን ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ እንደ አርስቶትላውያን እምነት ከሆነ ህልውና የሚባለው ጉዳይ ዛሬ ላይ ካለው የግለሰባዊነት ህልውና ጉዳይ ይልቅ የአለምን (የተፈጥሮን) ህልውና ሁሉ የሚመለከት ነው ማለት ይቻላል በማለት ያትታሉ፡፡ ታዲያ ከዚህ በተለየ መንገድ በ20ኛው ክፍለዘመን ይኸው የነገረህላዌ ፍልስፍና ርዕዮተዓለሙን በማጥበብ ከአጠቃላዩ የሰው ልጅ የጋርዮሽ ህልውና በላቀ እና በረቀቀ መልኩ በእያንዳንዱ የሰው ልጅ ህላዌ ላይ እያነጣጠረ እና ፊቱን ወደዚሁ ተናጠላዊ ህላዌ በማዞር ልዩ ልዩ ሰብዓዊ ጉዳዮችን የሚመለከት እሳቤ እየሆነ እንደመጣም ይጠቁማሉ፡፡ ስለዚህ የዘመናችን የነገረህላዌ እሳቤ በዓለም ላይ ከሚገኙ እና እልቆቢስ ከሆኑ ህልው ነገሮች ሁሉ አንዱ ወደሆነው የሰው ልጅ ህላዌ ብሎም

ከአጠቃላይ የሰው ልጅ ባህርይ (essence) ይልቅ ወደ እያንዳንዱ የህይወት ገጽታ ወይም ደግሞ ግለሰባዊ ጉዳይ የትኩረት አቅጣጫውን በማጥበብ ዛሬ ላይ የተለመደ የሰው ልጅ ተናጠላዊ ወይም ግለሰባዊ የህልውና (Individual existence) ፍልስፍና ሆኗል ማለት ይቻላል፡፡

በዚህ ጥናት የመግቢያ ክፍል ላይ እንደተጠቀመው፣ ምንም እንኳን በ20ኛው ክፍለዘመን “ነገረህላዌ” የሚል ስያሜ አግኝቶ በአዲስ እና በዘመናዊ መንገድ በስፋት ቢቀነቀንም፤ ይህ የህልውና ፍልስፍና ፅንሰሃሳብ ከ469 እስከ 399 ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ጀምሮ በዘመኑ ታላላቅ ፈላስፋዎች፣ ቅዱሳን (Saints) እና ትንቢተኞች (Seers) በእነSocrates እና Plato አማካኝነት እንደ ፈለቀ ብሎም በተለያዩ ሥራዎች ሲንንጸባረቅ የቆየ ስለመሆኑ Azhar (2013) ምስክር ናቸው፡፡ በዘመኑም ለመጀመሪያ ጊዜ የሰው ልጅ እንደ ትክክለኛ የእውቀት እና የምርምር ባለቤት ተደርጎ የታየበት ወቅት ሲሆን፣ በተለይም Socrates፣ የሰው ልጅ ለውጤታማ እና ትክክለኛ (genuine) ዓለማዊ ኑባሬ የራስ ምርምር እና እውቀት (self-enquiry and self-knowledge) ሊኖረው ግድ ነው የሚል እምነት የነበረው ታላቅ ፈላስፋ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የSocrates ተከታይ የሆነው Plato በርካታ የነገረህላዌ ፍሬ ሃሳቦችን ያሰላስል እና በንግግሩ መካከልም የተለያዩ ህልውናዊ ቃላትን አካቶ ይጠቀም የነበረ ሌላው ግንባርቀደም ፈላስፋ ነው፡፡ ከነSocrates እና Plato በተጨማሪ ደግሞ St. Augustine በተናጠላዊ ህልውና ላይ በማተኮር የሰዎችን ውድቀት፣ ከሃይማኖት መውጣት (spiritual withdrawal) እና የተለያዩ ህልውናዊ እንቅስቃሴዎችን ያራምድ የነበረ ወይም ህልውናዊ አተያይ የነበረው ቀደምት ፈላስፋ ስለመሆኑ ጠቅሰው፣ እንዲያውም በ20ኛው ክፍለዘመን እንደ አዲስ ብቅ ባሉት በMarcel እና በSartre የነገረህላዌ እሳቤ ውስጥ የAugustine ፅንሰሃሳብ በግልጽ እንደሚስተዋል Azhar (2013) ያስረዳሉ፡፡

Mobini እና Salim pour (2016; 7)፣ “ነገረህላዌ የታላቁን የሰው ልጅ እሳቤን ያህል የእድሜ ዘመን ያለው እና በፍልስፍናው፣ በጥበባቱ፣ እንደዚሁም በሥነ ጽሑፉ ዘርፍ የተንጸባረቀ የአስተሳሰብ ዘይቤ ነው” በማለት፣ ከ Flynn (2006) ሃሳብ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሐተታቸውን ያስቀምጣሉ፤ (“The existentialism is a method of thought in philosophy, art, and literature that is as old as the oldest human’s thoughts”) (Mobini እና Salim pour (2016; 7)፡፡

የ20ኛው ክፍለ ዘመን የህልውናዊነት ጽንሰ ሃሳብ እንደ አዲስ የፍልስፍና የትምህርት መስክ ይተዋወቅ እንጅ ታሪካዊ ስሩ ግን ከረጅም ጊዜ በፊት ሲመረመር እና ሲጠና የቆየ ፍልስፍናዊ እሳቤ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም የነገረህላዌ ፍልስፍናን ጽንሰ ሃሳብ የሚያሳዩ የተለያዩ ጉዳዮች መንጸባረቅ ከጀመሩ ረጅም ዘመንን ያስቆጠሩ ብቻም ሳይሆኑ የራሱን የሰውን ልጅ ህልውና ያህል ረጅም እድሜም ያላቸውም ጭምር ናቸውና፤ Mobini እና Salim pour (2016)፡፡

> "The existential philosophy in the 20th century was introduced as a school of philosophy but it historic roots could be searched in a long time ago because the discussed issues in the existentialism philosophy are as old ashuman existence" (Mobini እና Salim pour, 2016; 87).

በፍልስፍና ታሪክ ወደ ኋላ መለስ ብለን ስንመረምር በአሁኑ ወቅት ላደገው የነገረህላዌ እሳቤ ሀረጉ የተመዘዘው ከፋናወጊው ፈላሰፋ ከሶቅራጠስ "Know they self" ከተሰኘው የሰው ልጅ የህልውና አተያይ እንደሆነ Mallah (2016) ከዚህ በላይ ከተጠቃቀሱት ሊቃውንት ጋር ተዛመጅ የሆነ ሃሳባቸውን ያራምዳሉ፡፡ እንደ Mallah (2016) እምነት፣ ምንጩ ከሶቅራጦስ ዘመን ይቀዳል የተባለለት የነገረህላዌ ፍልስፍና ዛሬ ለደረሰበት ዘርፈ ብዙነት እና ብልጽግና ቀደምቶቹ የ19ኛው እና የ20ኛው ክፍለዘመን ጸሐፊያን እነ ፊዮዶር ዶስቶዮቭስኪ እና ሲ ኤፍ ካፍካ ሥራዎች አስተዋፅኦ ከፍተኛ ድርሻ የሚሰጠው ነው፡፡

Stefan Blea (2018)፣ ደግሞ የነገረህላዌን ታሪክ በሦስት ዋናዋና ምዕራፎች ከፋፍለውታል፡፡ በዚህ መሰረት የመጀመሪያው የነገረህላዌ እንቅስቃሴ በ1840ዎቹ አካባቢ ታላላቅ ተጽዕኖ ፈጣሪ ሥራዎችን በዴንማርክ ባበረከተው ምሁር ሶረን ኬርክጋርድ (Soren Kierkegaard) ተወክሏል፡፡

የሁለተኛው ምዕራፍ ደግሞ በዋናነት በ1880 እና በ1940 መካከል በነበሩት የተለያዩ ሥራዎቻቸው አማካኝነት የጀርመን ሀሳባውያንን የሚመለከት ሲሆንን ከእነዚህ መካከል ደግሞ ፍሬደሪክ ኒቼ (Friedrich Nietzsche)፣ ኤድመንድ ሃሰርል (Edmund Husserl)፣ ካርል ጃስፐርስ (Karl Jaspers) እና ማርቲን ሄዲገር (Martin Heidegger) ይገኙበታል፡፡

ሦስተኛው እና የመጨረሻው ምዕራፍ ደግሞ ነገረህላዌ የተሻለ እውቅናን ያተረፈባቸውን አዝማናት የሚመለከት ሲሆን፣ ይኸውም በ1930 እና በ1970 መካከል ባሉት ጊዜያት

ውስጥ በፈረንሳያውያን ፈላስፋዎች አማካኝነት የላቀ የፍልስፍና ዝንባሌ እና ታላቅ እምርታ እያሳየ የመጣበትን ወቅት ያጠቃልላል፡፡ ከወቅቱ ዋና ዋና ፈላስፋዎች መካከል ደግሞ አልበርት ካሙ (Albert Camus)፣ ጋብሬል ማርሴል (Gabriel Marcel)፣ ሲሞነ ደ ቢቯ (Simone de Beauvoir)፣ ሞሪስ ሜርሉፖንቲ (Maurice Merleau-Ponty) እና በተለይ በተለይ ደግሞ ጉልህ ስፍራ የሚሰጠው ዣን ፖል ሳረተር (Jean-paul Sartre) ግንባር ቀደም ተጠቃሾች ናቸው፡፡

በተመሳሳይ መልኩ፣ በ19ኛው ክፍለዘመን የነገረህላዌ የፍልስፍና ዘርፍ እንዲያንሰራራ በግንባር ቀደምትነት ያቀነቅን የነበረው እና በወቅቱም "የነገረህላዌ አባት" የሚል ስያሜን የተቀዳጀው ሶረን ኬርክጋርድ (Soren Kierkegaard) እንደነበረ Mallah (2016) ያስረዳሉ፡፡ ከኬርክ ጋርድ ጎን ለጎን ደግሞ ሌሎች በርካታ የዘርፉ ፈላስፋዎች እና ጸሐፊያን ዘርፉን በማሻሻል ብሎም የዛሬውን ቅርጽ በማስያዝ ረገድ ከፍተኛውን ድርሻ ከሚይዙት መካከል ፍሬደሪክ ኒቼ (Friedrich Nietzsche)፣ ካርል ጃስፐርስ (Karl Jaspers)፣ ዣን ፖል ሳርተር (Jean-paul Sartre)፣ ሲሞነ ደ ቢቯ (Simone de Beauvoir) እና የመሳሰሉት ይገኙበታል ሲሉም ከBlea (2018) ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሃሳባቸውን ያክላሉ፡፡

ወደ 19ኛው እና 20ኛው ክፍለዘመን ስንመጣ ደግሞ፣ Wolcott H.F (1992)፣ ለነገረህላዌ ፍልስፍና በአዲስ መልክ ብቅ ማለት የSartreን ሥራዎች እንደ ምክንያት በማስቀመጥ ይህንን ወቅት ዘርፉ መሻሻል ያሳየበት እና ትልቅ ተቀባይነትንም ያገኘበት ጊዜ እንደሆነ ያብራራሉ፡፡ በተመሳሳይ፣ ይህ ዘመናዊ የነገረህላዌ ፍልስፍና ምንጭ ከወደ ፈረንሳይ ፓሪስ ከሁለተኛው የአለም ጦርነት ማብቂያ አካባቢ በዣን ፖል ሳረተር (Jean-paul Sartre) እና ሲሞነ ደ ቢዋቨ (Simone de Beauvoir) አማካኝነት እንደፈለቀ Flynn (2006) ያስረዳሉ፡፡ እንደFlynn እምነት የነገረህላዌ እንቅስቃሴ በፍልስፍናው መስክ ብቅ ካለበት ጊዜ ጀምሮ በሰዎች ሁለንተናዊ የህልውና ጉዳይ ላይ ያነጣጥር የነበረ የፍልስፍና ዘርፍ ነው፡፡

Michelman (2008) ደግሞ፣ የነገረህላዌ ፍልስፍናን መጀመር ጥቂት አሰርት አመታትን ወደ ኋላ በመውሰድ ዋናው እና ትክክለኛው የህልውናዊነት ፍልስፍና ምዕራፍ ከመጀመሪያው የአለም ጦርነት በኋላ በ1920ዎቹ እና በ1930ዎቹ ከወደጀርመን እንደመጣ እንደዚሁም በወቅቱ ይህ የፍልስፍና ዘርፍ እንዲያቆጠቁጥ እና እንዲያንሰራራ ያደረጉት

ደግሞ Karl Jaspers እና Martin Heidegger እንደሆኑ ያስረግጣሉ፡፡ በመቀጠልም ይላሉ Michelman በሁለተኛው ምዕራፍ ይህ ፍልስፍና በ1930ዎቹ እና በ1940ዎቹ በጀርመናዊው ፈላስፋ በFriedrich Nietzsche እና በዴንማርካዊው Soren Kierkegaard ትኩረት እያገኘ መጣ፡፡ በዚሁ በሁለተኛው ምዕራፍ ዋና ተዋናይ የነበረው ደግሞ ፈረንሳያዊው ጸሐፊ እና ፈላስፋ Jean-Paul Sartre ነበር በማለት ከእነFlynn እና Wolcott በተለየ መንገድ ያትታሉ፡፡ በተጨማሪም ከ1945 ጀምሮ አዲስ መስመር እና ዘመናዊ መልክ እንዲይዝ በማድረግ ረገድ ከሌሎቹ ማለትም ከSimone de Beauvoir እና Maurice Merleau-Ponty ጋር በመሆን የነገረህላዌ ምሁራንን እንቅስቃሴ በዋና ተዋናይነት መራ እንጅ ነገረህላዌ ሙሉ በሙሉ የSartre ፍልስፍና ነው ሊባል አይችልም ሲሉ ሌሎቹን አካላት ማለትም የSartreን የነገረህላዌ ፍልስፍና አፍላቂነት የሚያቀነቅኑ ወገኖችን ይሞግታሉ፡፡

እንደMichelman (2008)፣ በ1950ዎቹ፣ በ1960ቹ እና በ1970ቹ ዓመታት የነገረህላዌ የፍልስፍና መስክ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ብሎም ወደሌሎች አለማት (የአለም አገራት) እየተስፋፋ እና እየተሰራጨ መጣ፡፡ የፈላስፋዎቹ ሀሳብም ቢሆን ከጊዜ ወደጊዜ ወደተለያዩ መስኮች ማለትም ወደአዕምሮ ህክምና (psychiatry or psychotherapy)፣ ሃይማኖታዊ አስተምህሮ (theology) ዘርፎች እና ወደሥነ ጽሑፋዊ (literary)፣ ሥነ ማህበረሰብዓዊ መደብ (race) እንደዚሁም ወደ ፆታዊ (gender) ንድፈሃሳቦች (theories) የትኩረት አቅጣጫውን እያዞረ እና እየተከፋፈለ መጣ፡፡ ከዚሁ ጋር በተገናኘ፣ የነገረህላዌ ፍልስፍና ወደ ሥነጽሑፍ ንድፈሃሳብነት (Literary theory) እና ማህበራዊ የትችት አንጻርነት (social criticism) መስክ በመምጣት ተጽዕኖ መፍጠር የጀመረው ደግሞ በ1930ዎቹ እና በ1940ዎቹ ገደማ በHeidegger አመካኝነት ነው በማለት Hubert L.drefus እና Mark A.Wrathall (2006) የMichelmanንን ሀሳብ ይጋራሉ፡፡

Azhar (2013) ደግሞ፣ ለ20ኛው ክፍለዘመን የነገረህላዌ ፍልስፍና የፊር ቀዳጅነት ሚናን ለGabriel Marcel እና ለJean-Paul Sartre ያቀዳጇቸዋል፡፡ ከዚህ ባለፈ ግን ከላይ ካስቀመጧቸው ግንባርቀደም የፍልስፍና አባቶች በኋላ በተለይ በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ እና በ20ኛው ክፍለዘመን መባቻ አካባቢ እራሳቸውን እንደ ነገረህላዌ ፈላስፋ ይቆጥሩ የነበሩ በርካታ ዘመናዊ ፈላስፋዎች እና ጸሐፊያን በዚሁ የህልውና ፍልስፍና ላይ የየራሳቸውን ትላልቅ አሻራ ጥለው እንዳለፉ ያትታሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል ደግሞ የFyodor

Dostoevsky '*Notes from underground*' በዚህ የነገረህላዌ ፅንሰሃሳብ ላይ የተመሰረተ ፋናወጊ የሥነጽሑፍ ሥራ ነው፡፡ Dostoevsky በሥራዎቹ ውስጥ የሰዎችን ግለሰባዊ አመለካከት (subjectivity) እና ነጻነት በጥልቀት መርምሮ ያሳየ ዘመናዊ ጸሐፊ እንደሆነም Peterfreund and Denise (1967)ን ዋቢ አድርገው ይገልጻሉ፡፡ ይሁን እንጅ በዋናነት አዲስ መልክ ይዞ ብቅ ያለው ከመጀመሪያው የዓለም ጦርነት በኋላ ሲሆን፣ ታላቅ እምርታ ያሳየው እና ተፅዕኖ መፍጠር የጀመረው ደግሞ የሁለተኛውን የአለም ጦርነት ተከትሎ ነው፡፡ በወቅቱ በእነዚህ ታላላቅ ጦርነቶች ምክንያት የተከሰቱት ልዩ ልዩ ይዘት ያላቸው አሰቃቂ የውድመት ክስተቶች በፈጠሩባቸው አካላዊ፣ ማህበራዊ እና ሥነ ልቦናዊ ቀውሶች ሳቢያ የሰውልጆች በገዛ ህልውናቸው እርግጠኞች እንዳይሆኑ እና በየትኛውም ነገር ላይ አመኔታ እንዲያጡ ሆነዋል፡፡

ሰዎች የተለያዩ መንፈሳዊም ሆኑ ቁሳዊ ሃብቶቻቸውን አጥተውባቸዋልና በራሳቸው ብሎም በፈጣሪያቸው (በአምላካቸው) የነበራቸው ተስፋ ሁሉ አብሮ ወድሞባቸዋል፡፡ ምንም የማይሳነው፣ ሁሉን አወቅ፣ የመኖር ምስጢር እና የሰላም አምላክ አድርገው ይቆጥሩት የነበረው ፈጣሪያቸው ከመካከላቸው ተገኝቶ ከዚያ ሁሉ ጥፋት አላዳናቸውም፤ የእርዳታ እጁንም አልዘረጋምና ህልው እንዳልሆነ እና እነርሱም እረዳት አልባ ፍጡራን እንደሆኑ ማሰብ ጀመሩ፡፡ በዚህ ምክንያትም በህይወታቸው ለደህንነት ስጋት፣ ለእርግጠኛነት እጦት እና ለህላዌ ትርጉም አልባነት በሽታዎች ተጋላጭ ሆኑ፡፡ እናም ሰዎች በህይወታቸው ውስጥ አዲስ ዋጋ እና ትርጉም መፈለግ ሲጀምሩ ዘመናዊውን የነገረ ህላዌ ፍልስፍና ወደማግኘት እና መተርጎም መጡ (Azhar፣ 2013)፡፡

የ20ኛው ክፍለዘመን የነገረህላዌ ፍልስፍና (Existentialism) የተቃውሞ ድምጽ እና ነጸብራቅ ሆኖ የተጀመረ ንቅናቄ ሲሆን፣ ቀደም ባሉት ጊዜያት የነበረውን ማንኛውንም የእውናዊነት (Rationalistic) እና መላምታዊ (Speculative) ፍልስፍና ለመቃወም ሲባል የተጀመረ እንቅስቃሴ ነው (Azhar, 2013)፡፡ እንደ Azhar ትንታኔ በተለይ ደግሞ የHegelian (የሄግሊያን) ፍልስፍና ያነጣጥር የነበረው ዓለምን እንደ ፈጣሪ ስጦታ እና የሰው ልጆችን ደግሞ ረዳት የሌላቸው የትልቅ ሚስጥራዊ ድራማ ተዋናይ ወይም ገፀ ባህርያት አድረጎ ይቆጥር በነበረው የቁሳውያን እሳቤ ላይ ነበር፡፡ ይሁን እንጅ ከዚህ አተያይ በተለየ መልኩ ነገረህላዌ የሰዎችን ሁኔታዊ አስተሳሰብ ወይም ግለሰባዊ ህላዌ እና የህላዌ ፍላጎትን የሚያጎላ ፍልስፍናዊ እሳቤ ነው፡፡

ዘመናዊው የነገረህላዌ ፍልስፍና እንደ ፍቅር ወይም ጥልቅ የሆነ የፍቅር ስሜት (Passion)፣ ደስታ (ecstasy)፣ የውሳኔ ባለቤትነት ወይም ውሳኔ ሰጭነት (decision-making) ፣ ጭንቀት፣ ህመም (sickness)፣ ተስፋ መቁረጥ እና ሞት የመሳሰሉ የሰው ልጆችን ዋና ዋና የህልውና መልኮችን ቁብ ሳይሰጥ ከቆየው የጥንታዊው (Classical) ፍልስፍና በተለየ መልኩ እነዚህን ህልውናዊ ጉዳዮች የሚያጎላ ፍልስፍናዊ እሳቤ ነው፡፡ በሌላ አባባል ይህ ዘመናዊ የህልውና ፍልስፍና በእያንዳንዱ ግለሰብ ሁኔታ (individual situation)፣ የህልውና፣ የትክክለኛነት እንዲሁም የሁለንንተናዊ ነጻነት (universal freedom) ላይ የሚያተኩር ሰብዓዊ አተያይ ነው፡፡ ዋነኛ ዓላማውም ቢሆን፣ በዘመናዊው ዓለም ውስጥ እያንዳንዱ የሰው ልጅ የተሟላ ህይወትን እንዴት መምራት እንደሚችል ማስገንዘብ እንደሆነ Azhar (2013)፣ Guignon (2005)ን ጠቅሰው ሃሳባቸውን ያስቀምጣሉ፡፡

Mobini እና Salim pour (2016) ደግሞ፣ የህልውናዊነት የፍልስፍና ጽንሰሃሳብ ስርዓታዊ የእውቀት መስክ እንዲሆን ያደረገው በዋናነት William Friederich Hegel ነው ይላሉ፡፡ ይህ የHegel የፍልስፍና ለውጥ ዘይቤ ደግሞ ሌሎችን የህልውናዊነት ሃሳባውያንን ወደ ፍልስፍና መስክ ፊታቸውን እንዲያዞሩ ወይም እንዲያዘነብሉ አድርጓቸዋል፡፡ በዚህም መሰረት ከክርስቲያናዊ ህልውናውያን (Christian existentialist) መካከል አንዱ የሆነው Kierkegaard በክርስትና እምነት እና በፍልስፍና መካከል ያለውን ግንኙነት ለማሳየት ሞክሯል፡፡ Kierkegaard፣ ፍልስፍና የእምነት መነሻ ሳይሆን ሰዎች ሞራላዊ እና ሃይማኖታዊ ህላዌ እንዲኖራቸው የሚያግዝ እሳቤ ነው ብሎ ያምናል፡፡ Nietzsche በበኩሉ፣ ለጀርመናውያን ሳይንሳዊ የፍልስፍና ማዕከል ፈላስፋዎች የፍልስፍና ልምዳቸው ትክክለኛው ውጤት አስፈሪ እና አድካሚ እንደሆነ ለማሳየት በመፈለግ፣ ይኸው ፍልስፍና የባሪያዎችን (የጥቁሮችን?) ሃይለኛ የስኬት ባህርይ የማግለል ባህል እንዳለው እና ይኸውም ለታላቁ ዓላማቸው መሳካትም ዋነኛ እንቅፋት እንደሚሆን በራሱ ፍልስፍና ለማሳየት ሞክሯል፤

> Nietzsche is someone who shows that the enthusiasm for the truth resulted from the idealist tradition of German Scientific-academic philosopy is fearful and weaking. Nietzsche's philosophy addresses those who have the Courage to reject slaves' behavior, those who have courage to overcome the obstacle on their way to achieving their great goal.
>
> (MObini and Salim pour, 2016; 87)

በተመሳሳይ መልኩ Heidegger የታላላቅ ፈላስፋዎች የህልውናዊነት ፍልስፍና ስልት በሚሳካ መልኩ የተደራጀ አይደለም፤ በማለት እንደ Nietzsche እና Kierkegaard ሁሉ የጀርመናውያን ሃሳባውያንን የፍልስፍና ልምድ በተለያየ መልኩ በመቃወም እና ይኸው የፍልስፍና ባህል ከንቱ እንደሆነ እና ስኬታማ እንዳልሆነ በግልጽ የሚያሳዩ ርዕሰ ጉዳዮችን በማቅረብ አሳይቷል፡፡

እንደ Mobini እና Salim pour (2016) ሃሳብ በኋላ ግን፣ በ19ኛው እና በ20ኛው ክፍለዘመናት በተለያዩ ዘርፎች የተሰማሩ በርካታ የሥነ ሰብዕ ተመራምሪዎች ወይም ሥነ ሰብዓውያን (Humanists)፣ አማንያን (Theists)፣ በአምላክ ህላዌ የማያምኑ ወይም ኢ-አማንያን (atheists)፣ አይሁዳውያን(Jewish)፣ እና ክርስቲያን (Christian) ጸሐፊያን እና ፈላስፎች ቀደምትነት ላለው የህልውናዊነት እሳቤ መስፋፋት እና ማደግ ታላላቅ ሚናን ተጫውተዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል በ19ኛው ክፍለ ዘመን እነ Kierkegaard, Nietzsche, Dostoevsky, Leo Tolstoy የሚጠቀሱ ሲሆን፤ ወደ 20ኛው ክፍለ ዘመን ስንመጣ ደግሞ፣ እነ Jean-Paul Sartre, Simone de Beauvoir, Albert Camus, Martin Heidegger, Gabriel Marcel, Karl Jasper, Martin Buber, Rudulf Bultmann, Berdyaev እና Maguel de Unumuno ዋና ዋናዎቹ እንደሆኑ Mobini እና Salim pour (2016) ያብራራሉ፡፡

እንግዲህ ቀደም ብየ እንደጠቆምኩት ይህን (የነገረህላዌ) ፍልስፍናን አስመልክቶ በተለያዩ አካላት ከዚህ በላይ ባየነው መልኩ ታሪካዊ ዳራው መቀመጡ የዘርፉን ውስብስብነት እና ዘርፈ ብዙነት በጉልህ ከመግለጹም በላይ ዛሬም ድረስ ገና ሊጠና እና ሊመርመር የሚገባው ፍልስፍናዊ የእውቀት መስክ እንደሆነ አይነተኛ ማሳያ ነው፡፡ ያም ይሁን ይህ ግን ይህ ፍልስፍና ከጥንት ጀምሮ የነበረ እና በተለይ ደግሞ ወደ 19ኛው እና 20ኛው ክፍለዘመናት በተለያዩ የኪነጥበብ ሥራዎች በተለይም ደግሞ በሥነጽሑፍ አማካኝነት በዘመናዊ መልክ እንዳንሰራራ ከፍ ሲል ከተቀመጡት መረጃዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ የዚህን ፍልሥፍና ትክክለኛ ጽንሰሃሳባዊነት ወይም አሁናዊ መልክ በተመለከተ ቴዎድሮስ ገብሬ (2001፤ 141-142) እነ Flynnን እና John Macquarrieን ዋቢ አድርገው "የነገረ ህላዌ ፍልስፍና በረጅሙ የሰውልጅ የስልጣኔ ታሪክ ውስጥ ከሰው ልጅ ህልውና ጋር ተቆራኝቶ ዛሬን ጭምር የዘለቀ ርዕሰ ጉዳይ እና የአስተሳሰብ ዘይቤ" መሆኑን ከጠቀሱ በኋላ፣ 'ትክክለኛው የነገረ ህላዌ ዘመን' ብለው የሚደመድሙት ግን የ20ኛውን ክፍለ ዘመን ነው፡፡ ስለሆነም

አብዛኛዎቹ መረጃዎች ከሚያመለክቱት እና በርካታ ተመራማሪዎችም ከሚያስቀምጡት ፍንጭ አንጻር ይህ የሰው ልጆች የህልውና ፍልስፍና ጥንታዊ መሠረት ያለው እና በ19ኛው እና በ20ኛው ክፍለ ዘመናት ሠፊ ሽፋን የተሰጠው እሳቤ ነው ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡

## 2.1.3. የነገረህላዌ ፍልስፍና እና ሥነጽሑፍ

ቀደም ባሉት ንዑሳን ክፍሎች የነገረ ህላዌን ፍልስፍና ምንነት እና ታሪካዊ እድገት በጥቂቱ ለማየት ሞክረናል፡፡ ታዲያ በእነዚህ ንዑሳን ክፍሎች ውስጥ ይህ የነገረህላዌ ፍልስፍና ከሥነጽሑፍ ጠቢባን ጋር የቆየ እና የጠበቀ ግንኙነት እንዳለው በግልጽም ይሁን በህቡዕ ተገልጧል፡፡ ይህን ማለቴ ያለምክንያት ሳይሆን ይህ የህላዌ ፍልስፍና ከኪነጥበብ በተለይም ደግሞ ከሥነጽሑፍ ጋር ያለውን ዝምድና ለማጠየቅ ነው፡፡ ይህ የፍልስፍና መስክ እንዲያንሰራራ የሆነውም በኪነጥበብ ጠበብቶች በተለይም ደግሞ በሥነጽሑፍ ባለሙያዎች መሆኑ ለእነዚህ ሁለት ሙያዎች መዛመድ ትልቅ ማሳያ  እንደሆነ ልብ ይሏል፡፡ በእርግጥም የፍልስፍናው ዋና ዋና አራማጆች ፈላስፋዎች ብቻ ሳይሆኑ፣ የሁለቱም ታላላቅ ሙያዎች ማደሪያ ጭምር እንደነበሩ ከፍ ሲል በጥቂቱ ካየናቸው መረጃዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

Mobini እና Salim pour (2016)፣ ይህ የ20ኛው ክፍለዘመን የነገረህላዌ ፍልስፍና ጥንታዊነት ያለው እሳቤ መሆኑን ከላይ ባየነው መልኩ ካብራሩ በኋላ፣ ከፍልስፍናነቱ ባሻገር ደግሞ ከተለያዩ ዘመዊ ኪነጥበባት ጋር ግንኙነት ያለው እና ኪነጥበባዊ እንቅስቃሴም ጭምር እንደሆነ በመግለጽ ከእነዚህ ዘመናዊ ኪኖች ጋር የሚያዛምዱትን አራት ዋና ዋና ምክንያቶች ያስቀምጣሉ፡፡ እነዚህ ዋና ዋና ምክንያቶች ደግሞ ከዘመናዊ የኪነ ጥበብ ሥራዎች ማለትም ከሲኒማ ጥበባት፣ ከሥነ ጽሑፍ ሥራዎች እና ከሌሎችም የፈጠራ ጥበባት ጋር ያለውን ቁርኝት በግልጽ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ከእነዚህ መካከልም የመጀመሪያው አመክንዮ፣ የሁሉም ነገረህላዌያን ፈላስፋዎች እሳቤ እና የአመለካከት ዳራ (background) ወይም ቀድሞ የገነቡት ዝንባሌ ሲሆን፣ ይኸውም የህልውናዊነት ፍልስፍናን ከጥበባት እና ከዘመናዊ ሥነ ጽሑፍ ጋር ጥልቅ እና ሊቋረጥ የማይችል እንደዚሁም የጠበቀ ዝምድና  እንዲኖረው አድርጎታል የሚል ነው፡፡ “The main objections of existentialisms from the philosophy which is the background of all their opnions

and thoughts is the first factor that makes existentialism philosophy find a profound and unbreakable connection to art and modern literature" (Mobini እና Salim pour, 2016; 87).

ሌላው እና ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ የዘመናዊ ፊልም ጥበብ ባለሙያዎች እና ህልውናውያን እራሳቸው ስለሰው ልጅ እና ራሱ የሰው ልጅ በአለም ላይ ስላለው ስፍራ የሚሰጡት ትርጓሜ እንደሆነ MObini and Salim pour (2016)፣ Macquaryን ጠቅሰው ያብራራሉ፡፡ ምንም እንኳን በነገረህላዌ ልሂቃን መካከል አለመግባባቶች የነበሩ ቢሆንም፣ ነገር ግን ሁሉም በህልውና በተለይም ደግሞ በሰው ልጅ ህልውና ላይ ያነጣጠሩ ነበሩ፡፡

በሦስተኛ ደረጃነት የተቀመጠው ምክንያት ደግሞ የዘመናዊ ሲኒማ ጥበብ ከነገረህላዌ ፍልስፍና ጋር የሚጋራው ታሪካዊ ዳራ ሲሆን፣ በእንደዚህ አይነቱ ሲኒማ ውስጥ የሚሳሉት ገጸባህሪያት የዘመኑን ወይም የወቅቱን ሁነቶች (ጭብጣዊ ገጽታዎች) የሚያንጸባርቁ እና በአለመረጋጋት፣ በእረፍት እጦት እና በብጥብጥ ተጽዕኖዎች ስር የወደቁ ሆነው ይቀረጻሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ታዲያ ገጸባህርያት ብቸኛ እና ተስፋ የለሽ እንዲሁም ሌሎችን አካላት በቀላሉ የማይረዱ ይሆናሉ፤ አሊያም ደግሞ በእጅጉ የተጋነኑ ግንኙነቶችን (romantic relationships) የሚፈጥሩ ይሆናሉ፡፡

የነገረህላዌ ፍልስፍና ከጥበባት፣ ከሥነጽሑፍ እና ከሌሎች የፈጠራ ጥበባት ጋር ዝምድና ይኖረው ዘንድ በመጨረሻ እና በአራተኛ ደረጃ የሚጠቀሰው ምክንያት ደግሞ አብዛኛዎቹ የፊልም ባለሙያዎች ከፍልስፍና እና ከሥነ ጽሑፍ ጋር ያላቸው የጠበቀ ቁርኝት ነው "The fourth reason that makes existentialism familiar with art, literacy and artistic creation is the deep familiarity of most modern film workers with philosophy and literature" (Mobini እና Salim pour, 2016; 88)፡፡

ይህ የፍልስፍና ዘርፍ ከሥነጽሑፍ ጋር ስላለው ግንኙነት የሁሉም የዘርፉ ምሁራን ሃሳብ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ቀደም ሲል እንደተጠቆመው ይህ ፍልስፍና በሥነጽሑፍ ውስጥ ስለማደጉ ሁሉም ተመራማሪዎች በአንድ ድምጽ መስክረውለታልና፡፡ ቴዎድወሮስ (2001፤ 144)፣ ይህን ፍልስፍና ለጥናት እና ምርምር መተንተኛነት ሲጠቀሙ፣ በመተንተኛ ንድፈሃሳብነት የመረጡባቸውን ሦስት ዋናዋና ምክንያቶች ዘርዝረዋል፡፡ ከእነዚህ መካከል ደግሞ በተለይም ሁለቱ ምክንያቶች ከዚህ ሃሳብ ጋር

የሚዛመዱ እና ለማጠናከሪያነት የሚሆኑ ናቸው፡፡ በዚህ መሠረት የመጀመሪያው፣ "የዘመናዊ ህልውናነት አስተሳሰብ መሠረት የተጣለው በሥነጽኁፍ ኪን ውስጥ ነው" የሚል ሲሆን፤ የሁለተኛው ደግሞ፣ ከፍ ሲል እንደተነሳው "ዓበይት የፍልስፍናው አቀንቃኞች የፈላስፋነታቸውን ያክል ከያኒያንም ነበሩ" የሚል ነው፡፡ እግዲህ እነዚህ ሁለት ጉዳዮች የሁለቱን ሙያዎች ውህደት በአያሌው ይገልጣሉ የሚል እምነት አለኝ፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ፍልስፍና በሥነጽሑፍ ይገለጣል፤ ሥነጽሑፍም ቢሆን በሰዎች ህላዌ መነሻነት ይከየናልና ነው፡፡

እንግዲህ እስከአሁን እንዳየነው፤ ለ20ኛው ክፍለዘመን ነገረህላዌያን (Existentialists) የፍልስፍና እምነታቸው፣ በአለም ላይ ካሉ ፍጡራን ሁሉ ሰዎች ሁሉንም ነገሮች (Man is everything) ናቸው የሚል ይመስላል፡፡ ይህ የነገረህላዌ ፍልስፍና እንደ ሥነ ጽሑፋዊ ሂስነቱም የሰውልጆች ከሚጋሯቸው ማህበራዊም ሆኑ ሥነልቦናዊ ጉዳዮች በላቀ ሁኔታ በእያንዳንዱ ግለሰብ የህይወት ገጠመኝ ላይ ትኩረቱን በማሳረፍ የሰዎችን ስጋት (dread)፣ ጭንቀት (angush)፣ ተስፋቢስነት (despair)፣ እምነት (fidelity)፣ ተስፋ (hope)፣ ሞት (death)፣ ፖለቲካዊ፣ ሃይማኖታዊ እና ጾታዊ ጉዳዮች፣ ነጻነት፣ ኃላፊነት፣ የህልውና ምንትነት (meaning of existence) እና መሰል ሰብዓዊ ጉዳዮችን ወይም ጭብጣዊ ገጽታዎችን ምንነት፣ አስፈላጊነት እና መገለጫ መንገዶን በሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ውስጥ ለመመርመር እና ለመተንተን አይነተኛ ንድፈ ሃሳባዊ ማዕቀፍ በመሆንም እያገለገለ ይገኛል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ነገረህላዌ የእያንዳንዱን የሰውልጅ ግለሰባዊ የህልውና ሁኔታ፣ ስሜት፣ ድርጊት እና አመለካከት የሚያጠና ፍልስፍናዊ እሳቤ ነውና (Mart, 2012)፡፡

### 2.1.4. የህልውናዊነት ጭብጦች

#### 2.1.4.1. ነጻነት እና ኃላፊነት

ከሁሉ በፊት ነጻነት እና ኃላፊነት የነገረህላዌ ማዕከላዊ (ምናልባትም ተቀዳሚ?) ጭብጦች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ለዚህም ይመስላል፤ Flynn (2006; 8) "ነገረህላዌ የነጻነት ፍልስፍና ነው" የሚሉት፡፡

ህልውናዊ ነጻነት ማለት ማንኛውም ሰው የፈለገውን ድርጊት ሁሉ በነጻነት መፈጸም እንደሆነ Diagle እንዲህ ያትታሉ፤ "one is always free to do whatever one wants" Diagle (2010; 44)፡፡ እንደ ነገረህላዌያን እምነት ነጻነት እያንዳንዱ በዓለም ላይ (በምድር

ላይ) የሚኖር ሰው ከምንም እና ከማንም እርዳታ ወይም ዕገዛ ነጻ በሆነ መንገድ በየትኛም ጊዜ ያሻውን ሁሉ መተግበር ነው፡፡ የሰው ልጅ የራሱን ህይወት በራሱ መንገድ መግለጽ፣ መምራት፣ በጥቅሉ ራሱን የመፍጠር ነጻነት አለው፡፡ ይሁን እንጅ የዚህን ያህል ሙሉ ነጻነት ያለው የሰው ልጅ፣ የነጻነቱን ያህል ሙሉ ኃላፊነቱም ለራሱ ለግለሰቡ ይሆናል፡፡ እንደ Flynn (2006) ገለጻ፣ ማናችንም ነጻ የሆንነውን ያክል ኃላፊዎችም (Responsible) ነን፡፡ እያንዳንዱ ሰው አንድን ድርጊት በነጻነት ሲከውን ድርጊቱን ተከትሎ ለሚመጣው ውጤትም ኃላፊው እራሱ ግለሰቡ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ነጻነት እና ኃላፊነት የማይላቀቁ ወይም ደግሞ ተለያይተው የማይታዩ የህልውና ጭብጣዊ ገጽታዎች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ነጻነት ባለበት ሁሉ ኃላፊነት አለና ነው፡፡ ይህን አስመልክቶ Daigle (2010; 49)፣ Sartreን ጠቅሰው "If I am absolutely free, however, I also entirely responsible; I am not determind by any thing; there is no transcendent order determining me" (እኔ ነጻ ከሆንኩ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ኃላፊም ነኝ፤ በምንም ነገር አልወሰንም፤ እኔን ሊመራኝ ወይም ሊወስነኝ የሚችል ከራሴ የተሻለ ምንም ነገር የለም) በማት ያስረዳሉ፡፡ እንደ Sartre እምነት  ማንኛውም ሰው ወደዚች ምድር ሲመጣ ከምንም ነገር ነጻ ሆኖ እና ወደ አለም ከተቀላቀለ በኋላ ደግሞ ለሚፈጽመው ድርጊት ሁሉ ኃላፊነትን ተሸክሞ ነው፡፡ ይህን ሃሳብ Sartre፣ "Man is thrown to the world" (የሰው ልጅ ወደዚች ምድር የተወረወረ ወይም የተጣለ ነው) በማለት ይገልጹታል፡፡

ሰዎች በዓለም ላይ ሲኖሩ በተለምዶ ከተለያዩ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊ እና መሰል ደንቦች እና ስርዓቶች ጋር ሆኖ እናስተውላለን፡፡ በተለይም በሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ "የሰው ልጅ ማህበራዊ እንስሳ ነው" የሚለው ብሂል እንደ ዋና መርህ የሆነም ይመስላል፡፡ እንግዲህ የሰውልጅ አንዱ ከሌላው ጋር በጋራ እና በአብሮነት የመኖር ጠንካራ ባህል እንዳለው ለማጠየቅ እንደዚህ አይነት "ማህበራዊ እንስሳ" የሚል ጥቅል ስያሜ ተሰጥቶታል ማለት ነው፡፡ ማህበራዊ እንስሳነት ደግሞ የጋራ በሆነ ባህል፣ እምነት፣ አመለካከት፣ ደንብ ስርዓት ወዘተ-ወዘተ በአጠቃላይ በጋራ ማህበራዊ እሴት ይገለጻል፡፡ እነዚህ የጋራ እሴቶቻቸውም የማህበረሰቡ አባላት እያንዳንዳቸው ማድረግ ያለባቸውን ወይም የሌለባቸውን፣ የሚከተሉትን ወይም የሚቃወሙትን ተግባር የሚወስኑ በአጠቃላይ በጋራ የሚመሩባቸው ቃላዊም ሆኑ ጽሑፋዊ ደንብ እና ስርዓቶች ይኖሯቸዋል፡፡ ለነገረህላዌ ልሂቃን ግን እንደዚህ አይነቱ ዘልማዳዊ መነዳት አይዋጥላቸውም፡፡ ምክንያቱም

ማንኛውም ሰው እራሱን በራሱ የመቅረጽ እና የማስተዳደር ወይም ሙሉ ህይወቱን የመምራት መብቱም ሆነ ስልጣኑ ለራሱ ለባለቤቱ የተተወ ነው ብለው ያምናሉና፡፡ ስለዚህ ከእነዚህ እና መሰል የሰውን ልጅ የህይወት ጉዞ ከሚወስኑ ነገሮች ገለልተኛ መሆን ነው ነጻነት የሚባለው፡፡ ባጭሩ ለነገረህላዌያን ነጻነት ማለት አንድን ሰው ሊወስኑ ከሚችሉ ማናቸውም ማህበራዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊ እና መሰል ጉዳዮች ሁሉ ነጻ መሆን ማለት ነው፡፡ ይህ ብቻም ሳይሆን በነገረህላዌያን ዘንድ በሰው ልጅ ህላዌ ውስጥ ፈጣሪ (አምላክ) የሚባል ኃይልም የለም፤ ይልቁንም የሰው ልጅ የራሱን ህላዌ መፍጠር እና መኖር ይችላል ተብሎ ይታመናል፡፡ ታዲያ ይህ መሰል ነጻነትም ከኃላፊነት ውጭ ተነጥሎ የማይታይ እና ያለኃላፊነት ፈጽሞ የማይታሰብ ነው፡፡ Daigle (2010; 50) Sartreን ጠቅሰው የነጻነትን እና የኃላፊነትን ግንኙነት እንዲህ ያስነብቡናል፡፡

> The situation is mine because it is the image of my free choice of my self, and everything which it presents to me is mine in that this presents me and symbolizes me. is it not I who decide the coefficient of adversity in things and even their unpredictability by diciding my self?
>
> Thus there are no accidents in a life, a community event which suddenly bursts forth and involves me in it does not come from the outside. If I am mobillized in a war, this war is my war, it is in my image and I deserve it. I deserve it first because I cauld always get out of it by suicide or by desertion; these ultimate possibles are those which must always be present for us when there is a question of envisaging a situation for lack of getting out of it, I have chosen it. (BN708) (Daigle, 2010; 50)
>
> ሁኔታው እኔው እራሴው ነኝ፤ምክንያቱም ይህ ለራሴ የመረጥኩትን የእኔን የነጻ ምርጫ ሃሳብ የሚገልጽ እና ማንኛውም ወደራሴ የማቀርበው ወይም ለራሴ የምሰጠው ነገር እኔኑ የሚወክል እና የእኔው ምልክት ነው፡፡አደጋ የመፈጸም ምልክት እያሳየሁ እና ሊገመት በማይችል ሁኔታ እንኳን አደጋው በእኔ እየተፈጸመ ቢሆንፈጻሚው እኔው እራሴ አይደለሁምን?
>
> ስለዚህ አጋጣሚ ብሎ ነገር የለም፤ አንድ ማህበራዊ ክስተት በድንገት ቢከሰት እና እኔን ያሳተፈ ቢሆን ክስተቱ ከውጭ ወይም ከሌላ የመጣ ሊሆን ፈጽሞ አይችልም፤ ጦርነቱን ያንቀሳቀስኩት እኔ ደግሞ የራሴው ጦርነት፣ የእኔ ሀሳብ እና ለእኔ የሚገባ የሆናል፡፡ ለዚያውም በመጀመሪያ የችግሩ ሰለባ የምሆነው እኔው ነኝ፡፡ ምክንያቱም ይህ ሁኔታ በታወሰኝ ቁጥር እራሴን ለማጥፋት በመሞከር ወይም እራሴን በመክዳት ነጻ ለመውጣት እሞክራለሁና፡፡ አንድ ክስተት ትዝ ባለን ጊዜ የሚኖሩን የመጨረሻ አማራጮች እነዚህ ናቸውና፣ ከሁኔታው ለመውጣት ወይም ለማምለጥ ስቸገርም የምመርጠው ይህንኑ ነው፡፡ (Daigle, 2010; 50)

ነጻነት እና ኃላፊነት ጥብቅ የሆነ የምክንያት እና ውጤት ትስስር እንዳላቸው ከዚህ በላይ ከሰፈረው የSartre ሰፊ ትንታኔ መረዳት ይቻላል፡፡ በነጻነት የምንመርጠው ምርጫ እና የምናስተላልፈው ውሳኔ እንደዚሁም የምንፈጽመው ድርጊት ሁሉ በሌሎች አካላት ዘንድ ባያስጠይቀን እንኳን ከራሳችን ንጹህ ህሊና የተፋታን፣ ለሚመጣውም ተያያዥ ችግር ግንባር ቀደም ተጠቂ እንሆናለን፡፡ ስለዚህ በህይወታችን ውስጥ እያንዳንዱ በነጻነት የሚከናወን ተግባር ውጤቱ ኃላፊነትን ይጠይቃል፡፡

እንደ Sartre እምነት አለም የተፈጠረችው ከየትኛውም አይነት ልማዳዊ እና ሥነ ምግባራዊ እሴቶች ውጭ ነው፡፡ ለእነዚህ ሁሉ የነገሮች መፈጠር ምክንያቱ የሰው ልጅ ነውና ተጠያቂውም ራሱ ነው፡፡ Mobini  እና Salim Pour (2016) ም፣ የህልውናዊነት ትልቁ እና ዋናው እሳቤ (ጭብጣዊ ገጽታ) የሰው ልጅ ነጻነት መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህን ነጻነት የሚያገኘው ደግሞ እራሱ ከመረጠው ኃይል (power) ነው፡፡ ታዲያ የሰው ልጅ ለራሱ ባህርይ (behavior)፣ ንግግር (speech)፣ እና ሃሳብ (thought) ሁሉ እራሱ ግለሰቡ ኃላፊነት አለበት በማለት የSartreን ሃሳብ ይደግፋሉ፡፡ ስለዚህ ማንኛውም ሰው የራሱን ዓለም የመፍጠር እና የራሱን የህይወት መንገድ የመቀየስ ነጻነት አለው፡፡ ሰው በራሱ ምንም (nothing) ነው፤ ማንነቱ የሚወሰነው እራሱ በሚፈጥረው የህይወቱ መልክ ነው፡፡ እንደ ህልውናዊነት እሳቤም የሰው ልጆች ታሪካዊ ተፈጥሮ (historic nature) የላቸውም፤ ይልቁንም ከሌሎች ፍጡራን ሁሉ በተለየ መልኩ ማንነታቸው በሥነ ህይወታዊ፣ በታሪካዊ እና በባህላዊ ምርጫቸው የሚወሰን እና በራሳቸው የሚፈጠር ነው፡፡

ለነገረ ህላዌ ልሂቃን ማንኛውም ሰው ያመነበትን ተግባር ሁሉ የመከወን ነጻነት አለው፡፡ ስለሆነምከምንም ኃይል ተጽዕኖ ውጭ በሆነ መንገድ የራሱን እሴት ራሱ ግለሰቡ መፍጠር ይቻላል፡፡ እንደ Sartre አባባል፣ በሰዎች ምርጫ እና ውሳኔ ወይም ደግሞ ነጻነት ውስጥ የፈጣሪ ጣልቃ ገብነት እንኳን ቢሆን መኖር የለበትም፤ ሰዎች የራሳቸውን እሴት እና አለማዊ ህይወት መፍጠር አለባቸው “There is no God who decides for us and imposes values on us; accordingly, we must creat our own values” (Daigle, 2010; 44)፡፡ ስለዚህ ነጻነት ከየትኛውም የተፈጥሮ ኃይል ነጻ በሆነ መንገድ የራስን ደንብ እና ሥርዓት በራስ መፍጠር ነው ማለት ይቻላል፡፡ ነገር ግን ይላሉ Daigle፣ Sartreን ዋቢ በማድረግ እራሳችን በመረጥነው እና በወሰንነው ደንብ እና ሥርዓት ወይም በራሳችን እሴት ሳቢያ የሚመጡ ውጤቶችንም ሙሉ በሙሉ ለመቀበል እራሳችንን ማዘጋጀት

አለብን ("As beings that are free, we can do that but we must be ready to accept the consequences")፡፡ ይህ ደግሞ ማንኛውንም ድርጊት የመፈጸም ነጻነት ያለው ማንኛውም ሰው ድርጊቱን ተከትሎ የሚመጣውን ኃላፊነትም ለመሸከም እራሱን ማሳመን አለበት ማለት ነው፡፡ በጥቅሉ ለነገረህላዌ ልሂቃን ነጻነት እና ኃላፊነት ተነጣጥለው የማይታዩ "የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች" ወይም ደግሞ እንደ "ድር እና ማግ" የተሰናሰሉ ናቸው ብሎ መደምደም ይቻል፡፡ ለዚህም ነው በዚህ ጥናት ውስጥ ተጣምረው የሚቀርቡት፡፡

#### 2.1.4.2. ኦናነት (Forlornness)

እንደ Sartre እምነት ኦናነት (Forlornness) የሚባለው በአለም (Universe) ላይ ፈጣሪ (አምላክ) የሚባል ኃይል የለም፤ ስለዚህ የዚችን አለም መዘዝ መጋፈጥ የምንችለው እኛ የሰው ልጆች ብቻ ነን ብሎ ማመን ነው፡፡ ይህንን ሀሳብ Tan (2007; 93) Sartreን ጠቅሰው እንዲህ የብራራሉ፤ "The state of being forlorn means; only that God does not exist and that we have to face the consequences of this"፡፡ ስለዚህ እንደ ነገረ ህላዌያን እምነት ኦናነት ማለት ከፈጣሪ የጸዳ ማንነት መገንባት ነው ማለት ይቻላል፡፡ እናም በህይወት ውስጥ መመኪያ፣ ረዳት (አጋዥ) እና ተስፋ የሚጣልበት ኃይል በሥነ ፍጥረት (Universe) ውስጥ የለም፤ ነገሮች ሁሉ በእኛው እና ለእኛው የሚሰሩ ወይም የሚቀርቡ ናቸው፡፡ ከዚህ በመነሳት በዚህ አስተሳሰብ ውስጥ ለወደቁ ሰዎች እምነት የሚባል ነገር የላቸውም ማለት ይቻላል፡፡ በዚህ ረገድ ደግሞ ኦናነት፣ እምነት አልባነት ተብሎም ሊተረጎም ይችላል፡፡ ምክንያቱም እንደ ነገረህላዌ ልሂቃን ሀሳብ ኦና የሆኑ ሰዎች ሙሉበሙሉ በሚባል ደረጃ በምንም ነገር አያምኑምና ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ Hong wu (2013; 438) ስለ ኦናነት የSartreን ሃሳብ እንደሚከተለው ቃልበቃል ጠቅሰው እና አስፍረውት እናገኛለን፤

> Indeed everything is permissible If God does not exist, and as a result man is forlorn, because neither within nor with out does find any thing to cling to and all possibility of finding values in a heaven of ideas disappears along with Him. (Sartre, 1996; 669)

> በእርግጥ አምላክ የሚባል ኃይል ከሌለ ማንኛውም ነገር ለሰዎች የተፈቀደ ይሆናል፡፡ በዚህ ምክንያት ደግሞ ሰዎች ኦና ይሆናሉ፡፡ ምክንያቱም ከአምላክ ጋርም ሆነ ከአምላክ ውጭ ሳይሆኑ እራሳቸውን ከሌላ ማነኛውም ነገር ጋር

> በማጣበቅ በመንግሥተሰማያት ውስጥ ከአምላክ ዘንድ ሊገኙ የሚችሉ ዕድሎች ወይም ጸጋዎች (Possibilities) ይጠፋሉ፤ መልካም እሴቶችን ያጣሉ፡፡ (Sartre, 1996; 669)

በዚህ ምክንያት Hong wu (2013) ኦናነትን ከባይታወርነት ጋር ያገናኙታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ Mallah (2016) ኦናነት ከጭንቀት (anguish) ጋር የተገናኘ ሲሆን፣ ይኸውም በህይወታችን ውስጥ የሚረዳን ወይም የሚያግዘን አንዳችም ነገር የለም ብለን በምናምንበት ወቅት የሚፈጠር ስሜት እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ እንደ Mallah ገለጻ፣ የሰውልጅ ከእርሱ የተሻለ እና ከእርሱ በላይ የሆነ መመሪያ የሌለው ፍጡር እንደሆነ ያምናል፡፡ ይህ ደግሞ ገደብ የለሽ ነጻነትን ያመለክታል፡፡ በ Mallah እምነት ለዚሁ ኦናነት ጭብጣዊ ገጽታ ዋና መከሰቻው ነጻነት ነው፡፡ ሰዎች ከምንም እምነት ነጻ ሆነው በሚከውኗቸው ተግባራት ውስጥ እንደየምርጫቸው የየራሳቸውን ውሳኔ ይወስዳሉ፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ ለጭንቀት እና ኦናነት ያጋልጣቸዋል ማለት ነው፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ቀደም ሲል እንደጠቆምሁት የሚያምኑበት፣ ተስፋ የሚጥሉበት፣ ከጭንቀታቸው ሚጠለሉበት ወይም ደግሞ ይረዳኛል፣ ያግዘኛል፣ ይመራኛል ብለው የሚመኩበት እና የሚያስቡት ኃይል የላቸውምና ነው፡፡ በህይወታቸው ውስጥ ሁሉም ድርጊታቸው ከራሳቸው ብቻ የሚፈልቅ እና ከአምላካቸው ውጭ በመሆኑ ተስፋ ከመሰነቅ ይልቅ ተስፋ መቁረጥ እና መጨነቅ ብሎም ከባዶነት ስሜት ውስጥ መዘፈቅ ይከሰታል፡፡ ይህን መሰል ባዶነት ነው እንግዲህ "ኦናነት" ብዬ የገለጽሁት፡፡

### 2.1.4.3. ሁኔታዊነት (Situatedness)

"Although my freedom is absolute, it always takes place in a particular context. This is what makes freedom meaningful" (Hegel).

የእያንዳንዱ ሰው ህልውና ፍጹም በሆነ ነጻነት የታጀበ ከሆነ ባህርይው ወይም ደግሞ አጠቃላይ ማንነቱ ወደ አንድ የተወሰነ ሁኔታ ማለትም ነጻነቱ ወደመራው ከባቢያዊ ሁኔታ እንዲቀላቀል ያደርገዋል፡፡ በሌላ አገላለጽ፣ ከፍ ሲል ከHegel እንደቀነጨብኩት ሃሳብ፤ የአንድ ሰው ነጻነት ምንም እንኳን ፍጹም ነው ተብሎ ቢታመንም (ፍጹም ነጻ የሆነ ቢመስልም)፣ ነጻነቱ የሚቀዳው ከአንድ የተወሰነ አውድ ውስጥ ነው፡፡ ይህ ማለት የሰው ልጅ በህይወት በሚኖርበት ወቅት ህይወቱን የሚገፋው በአንድ የተወሰነ ከባቢያዊ ሁኔታ ወይም ማህበራዊ አውድ ውስጥ ነው፡፡ በዚህ ወቅት ታዲያ ከሌሎች ሰዎች የሚጋራቸው

አንዳንድ የህይወት ገጽታዎች አይጠፉም፡፡ በአብሮ መኖር የህይወት ሰንሰለታዊ ጉዞ ወቅት እያንዳንዱ ሰው በማወቅ ወይም ባለማወቅ ከሌሎች አካላት ወደራሱ፣ አሊያም በተገላቢጦሽ ሌሎች አካላት ከእርሱ (ከእሱ ወደ ሌሎች) የሚወራረሱት ልምድ መኖሩ ግድ ነው፡፡ ምክንያቱም እንደ ነገረህላዊያን እምነት የትኛውንም አይነት ነጻነት የሚፈጥሩት አካል(body)፣ አጋጣሚ ወይም ሁኔታ (circumstances) እና ታሪክ (past) ናቸው፡፡ ለነጻነት ደግሞ ትርጉም የሚሰጠው ወይም ትርጉም እንዲኖረው የሚያደርገውም አውድ (context) ነውና ማንኛውም ሰው ሙሉ በሙሉ ከአውዳዊነት የጸዳ አይደለም፡፡ ስለዚህ ባጭሩ ከሁኔታዊነት አንጻር ሲታይ፣ የሰዎች ህልውና ከአንድ  አውድ የተቀዳ ወይም ከአንድ የተወሰነ ሁኔታ የተወሰደ ነው ማለት ይቻላል፡፡

አንድ ሰው ከምንም ነገር ነጻ ሆነ ወይም ራስመር (being self) ሆነ ማለት በዙሪያው የተለያዩ የህይወት ዕድሎች (possibilities) ይበዙለታል፤ ብዙ አማራጮችም (choice) ይቀርቡለታል፡፡ በዚህ ወቅት ደግሞ የተለያዩ ሁኔታዎችን መምሰል ወይም እንደ ሁኔታዎች መቀያየር ይከሰታል፡፡ ስለዚህ ነጻነት ወጥ ያልሆነ እና ተለዋዋጭ (illusory) ህልውናን ይፈጥራል ማለት ነው፡፡ ይህን ሁኔታዊነት በተመለከተ Burnham; Heideggerን ጠቅሰው፣ "human existence cannot be abstracted from its world because being-in-the world is the part of the ontological structure of that existence" (5) በማለት ያትታሉ፡፡ ከዚህ አንጻር የማነኛውም ሰው ህልውና ከሚኖርበት ዓለም ሙሉ በሙሉ የተሰወረ ወይም ልዩ የሆነ አይደለም፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ዓለማዊነት (being-in-the world) ወይም በዓለም ላይ መኖር በራሱ የህልውና አነጻራዊ ገጽታ ነውና፡፡

እንደሁኔታዊነት (situatedness) ጽንሰሃሳብ፣ እያንዳንዱ የህይወታችን እንቅስቃሴ (act) ከሌሎች በዙሪያችን ካሉ አካላት ህልውና የተቀዳች ስትሆን፣ በአንጻሩም የሌሎቹ ሰዎች ህልውና ከእኛ የተቀዳ ድርጊት ይኖረዋል፡፡ ይህ ደግሞ የሰው ልጆች ነጻነታቸው በፈቀደላቸው ልክ ሁኔታዊ (situated) መሆናቸውን ያሳያል "Each of my acts says something about how I view others, but, resprocallyeach of their acts is a veiw about what I am" Burnham (6)፡፡ ስለዚህ በአለም ላይ ስንኖር የእያንዳንዳችን እንቅስቃሴ በአካባቢያችን ከሚኖሩ አካላት ስላየነው ነገር የሚገልጸው (የሚያስተላልፈው) አንዳች መልዕክት አለ፡፡ ይኸውም ሰዎች ምንም ያህል ፍጹም የሆነ ነጻነት ቢኖረንበቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ አካባቢያችንን እንደምንመስል ወይም ከአካባቢያችን

የምንወርሳቸው ልማዶች እንደማይጠፉ ግልጽ ማሳያ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ Flynn (2006; 135) “The human situation is an inherently ambiguous mixture of these two components, facticity and transcendence, the given and the taken” (የሰው ልጅ ሁኔታ በተፈጥሮው የሁለት ውስብስብ ቅንጣቶች ማለትም የትክክለኛ (facticity) እና የተሻሻለ (transcendence) ማንነት ወይም ደግሞ የተሰጠው (the given) እና የተቀበለው (the taken) ማንነቶች ውህድ ነው) በማለት ያብራራሉ፡፡

ማንኛውም ሰው ወደ ምድር ሲመጣ ወደ ፊት መሆን ያለበትን ህላዌ ተሰጥቶት ሳይሆን እንዲሁ ነጻ ተፈጥሮውን ይዞ ነው፡፡ ይህን ነጻ ተፈጥሮውን ተጠቅሞ በዙሪያው ባሉ የተለያዩ ቅድመሁኔተዎች ማለትም በዘር ሃረግ (parentage)፣ በብሔረሰብ (nationality)፣ በማህበራዊ ማንነት (social identity) ወይም በቀደመ ምርጫ (previous choice) እና መሰል ጉዳዮች ውስጥ እራሱን በመንከር የራሱን ድቅል ህልውና ይፈጥራል፡፡ የሚኖረው ህላዌም ከቅብብሎሽ ወይም ከመስጠት እና ከመቀበል ውጭ አይሆንም፡፡ በዚህ መሠረት የማንኛውም ሰው ነጻነት ሁኔታዊ እና የሌሎችን አካላት ሃሳብ (judgement) ፈጽሞ ያላገለለ ነው ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡

### 2.1.4.4. የርእይ መነጠቅ (Disillusionment)

ፍላጎት ወይም ምኞት የሰው ልጅ የሁለጊዜም መገለጫ ነው ማለት ይቻላል፡፡ እያንዳንዱ የሰውልጅ በቀናት መፈራረቅ የራሱ የሆነ ዓላማ፣ ዕቅድ፣ ምኞት ወይም ፍላጎት ይዞ ይነሳል፡፡ የተመኘውን ሲያገኝ ሌላ አዲስ ምኞት ይሰንቃል፤ ዛሬ ላይ የተመኘው ከግቡ ባይደርስ እንኳን ነገ ሌላ ተስፋን ይዞ ብቅ ይላል፡፡ ስለዚህ የሰዎች ፍላጎት ሰዎች በህይወት እስካሉ ድረስ አብሮ የሚኖር ሰንሰለታዊ እና ሁልጊዜም የማያቋርጥ ተግባር ነው ማለት እንችላለን፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥም “ርእይ” የሚለውን ቃል ለዚህ ገደብ የለሽ እና የሰው ልጅ የምንጊዜም ባህሪ ለሆነው ህልም፣ ምኞት፣ ዕቅድ ወይም ፍላጎት ወኪል አድርጌ ተጠቅሜበታለሁ፡፡ ቃሉን ደግሞ ከቴዎደሮስ ገብሬ (2001) ተውሸዋለሁ፡፡ ይህንኑ ቃል አለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌ (1948፣ 817) “ማሰብ፣ መመኘት፣ መገምገም፣ መገመት፣ መጠንቆል፣ መሟረት፣ ትንቢት መናገር፣ መላመምታት” በማለት ይፈቱታል፡፡

የሰው ልጆችን ተፈጥሯዊ የሆነ እና የማያቋርጥ የርእይ ባለቤትነት አስመልክቶ Maxwell የሚከተለውን ሃሳብ ያስቀምጣሉ፡፡

> The human nature is dynamic and receptive to change; which could be voluntary or involuntary; therefore in its quest to ensure that basic needs such as food, shelter and security are guaranteed all efforts are deployed towards the achievement of these goals. (Maxwell 2014; 250)
>
> ወደደም ጠላም የሰው ልጅ በተፈጥሮው ለለውጥ የተዘጋጀ እና በለውጥ ጉዞ ውስጥ የሚያለፍ እንደዚሁም ለውጥን ለመቀበል የተዘጋጀ ሲሆን በዚህ የለውጥ ጥረት (ሂደት) ውስጥ ደግሞ መሰረታዊ ፍላጎቶቹን ማለትም ምግብ፣ ልብስ፣ መጠለያ እና የደህንነቱን መጠበቂያ ነገሮች ለማሟላት ወይም ለማረጋገጥ አልሞ እና ጽኑ ፍላጎትን ሰንቆ በተለያየ ጎራ ላይ ይሰማራል፡፡ (Maxwell 2014; 250)

የርእይ መነጠቅ (Disillusionment) የሚባለው ደግሞ ይኸው የሰው ልጆች የማያቋርጥ ምኞት፣ ፍላጎት፣ ህልም ወይም ዕቅድ በከንቱ ሲቀር ወይም ደግሞ እንዳሰቡት ሳይሳካ ሲቀር ነው፡፡ ሰዎች አሳድደው የደረሱበት የልፋታቸው ውጤት በሆነ ነገር ሳቢያ በድንገት ከእጃቸው ሲያመልጥ የርእይ መነጠቅ ወይም የዓላማ አለመሳካት ሊባል ይችላል፡፡

Maxwell (2014) እንደሚያብራሩት፣ ሰዎች የህላዌ መሰረታዊ ፍላጎቶቻቸውን ለማረጋገጥ ወይም ደግሞ ህይወታቸውን የተሻለ እና ውጤታማ ለማድረግ ሃሳብ ብቻም ሳይሆን ቦታም ትተው ወይም ለቅቀው ሊሄዱ ይችላሉ፤ በወቅቱ ካሉበት ቦታ የተሻለ እና ውጤታማ ያደርገኛል ብለው ወዳሰቡት ቦታ የሰደዳሉ፤ ይፈልሳሉ፡፡ በቦታ እና በጊዜ ልዩነትም የተለያየ ርዕዮት ይሰንቃሉ፤ ያሳድዳሉ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ሰዎች ያሉበትን ቦታ ጥለው የሚሄዱት ደግሞ የተሻለ ህይወት ፍለጋ መሆኑ ግልጽ ሚስጥር ነው፡፡ ማለትም ይህ ተግባር ብዙ ጊዜ  ሰዎች ሲከውኑት የሚስተዋል እና የተለመደ ሁነት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህ በሌላ ተስፋ፣ ለሌላ ዓላማ፣ በሌላ ጊዜ፣ ወደ ሌላ ቦታ የሚደረግ ስደት ወይም ፍልሰት ደግሞ የሰዎችን የርዕይ መነጠቅ ያጎላዋል፡፡ ስለዚህ ይህ አይነቱ ከቦታ ወደ ቦታ፣ ከአንድ ሃሳብ ወደ ሌላ ሃሳብ በሚደረግ ዝውውር ስኬትን ማነፍነፍ እና ከጫፍ ሳይድሱ መመለስ ወይም ደግሞ ያለሙትን፣ የታገሉለትን፣ የደከሙለትን ውጤት ከመዳፍ በማስገባት፣ በመቅመስ እና በማጣጣም ፋንታ ከስኬት በር ላይ ደርሶ መመለስ፣ የውጤትን ጭላንጭል፣ የስኬትን ወጋገን በመናፈቅመቅረት ለሰዎች የርእይ መነጠቅ አይነተኛ ማሳያዎች፣ ሁነኛ መገለጫዎች ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ሰዎች በእጅጉ የለፉበት/ለት፣ የደከሙበት/ለት፣ ዘርፈብዙ መስዋዕትነት የከፈሉበት/ለት ተግባር በተለያየ ምክንያት ከግቡ ሳይደርስ ሲቀር ወይም ደግሞ ህልማቸው ወደ ቅዠት ሲለወጥ፣ እቅዳቸው ከንቱ ሲቀር፣

በጥቅሉ የተለያየ አይነት የዓላማ መሳከር ወይም አለመሳካት ሲገጥማቸው ርእያቸውን ተነጠቁ (disillusioned) ይባላል፡፡

#### 2.1.4.5. ቀቢጸ ተስፋ (Despair)

ተስፋ መቁረጥ ከአጠቃላይ የማንነት መበጥበጥ ወይም መታወክ ጋር በእጅጉ ተዛማጅነት ያለው ክስተት ወይም የህይወት ገጽታ ነው ("it is related to the breakdown of one's identity") ነው፡፡ ሰዎች በአንድ የተወሰነ ጉዳይ ላይ ከገዛ እራሳቸው ጋር በሚፈጥሩት አለመግባባት ወይም ከራስ ጋር በሚደረግ ከመጠን ያለፈ እሰጥ አገባ፣ ግብግብ ሳቢያ ከተስፋ መቁረጥ ውስጥ ይወድቃሉ፡፡ ይኸውም በሰዎች ላይ በተለያዩ ምክንያቶች ሊከሰት የሚችል ሲሆን ቀደም ሲል ከ "ርእይ መነጠቅ" ላይ እንዳነሳሁት ያለሙት፣ ያሰቡት፣ የተመኙት እና ያቀዱት ነገር በተደጋጋሚ አልሳካ ሲላቸው ወይም ደግሞ ባጭሩ ርእያቸውን ሲነጠቁ በህይወታቸው ተስፋ ይቆርጣሉ፡፡ ከዚያም አስበውትም ሆነ ሳያስቡት ወደሌላ ያልተጠበቀ ቀውስ ውስጥ ይገባሉ፡፡ ይህ እንግዲህ ተስፋ መቁረጥ የሚወልደው የማንነት ወይም የህልውና መሳከር ነው፡፡

የሰዎች ተስፋ ቢስነት በእለት ከእለት ህይወታቸው ውስጥ ከሚያጋጥሟቸው ያልተጠበቁ እና እርግጠኝነት ከሌላቸው ጉዳዮች ይመነጫል (Tan, 2007)፡፡ ሰዎች ተስፋ የሚቆርጡት በህይዎታቸው ውስጥ እርግጠኛ ይሆኑባቸው የነበሩ በርካታ ነገሮች ሲፈራርሱ ወይም ሲወድሙ ነው፡፡ እንደ Tan ሃሳብ ለሰዎች ተስፋ መቁረጥ ምንጩ፡ የመጀመሪያው የአለም ጦርነት ነው፡፡ ከዚህ አስደንጋጭ ክስተት በኋ ሰዎች ብዙ ዕድሎች መክነውባቸዋል፤ በርካታ ነገሮች ወድመውባቸዋል፡፡ በዚህ ምክንያት ደግሞ ቀቢጸተስፋ ሆነዋል፤ በአምላካቸውም እንዳያምኑ ሆነዋል፤ ከፈጣሪያቸው ተፋትተዋል፡፡ እንደ Tan (2007) ማብራሪያ ከሆነ ተስፋ ማጣት (loss of hope)፣ በፈጣሪ አለማመን (disbelieve in God)፣ ከሰዎች ጋር ታማኝ የሆነ ግንኙነት ማጣት (loss of personal sincere relationships)፣ የማንነት እጦት (loss of identity)፣ ብሎም የገንዘብ ባለቤትነት ወይም ባለንብረትነት እጦት (loss of material possessions) አይነተኛ የተስፋ መቁረጥ ስሜቶች (moods) ናቸው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ተስፋ ቢስነት የሰዎች የእለት ከእለት እርግጠኛ ያልሆነ እና ሊገመት የማይችል ህላዌ የሚፈጥረው ክስተት መሆኑን Tan (2007; 95) እንዲህ ገልጸውታል፤

“Despair is the outcome of uncertainty and unpredictability of man’s daily life” ፡፡ Sartreም በበኩላሰው፣ በህይወታችን ውስጥ ለምንወስነው ውሳኔ ዋስትና ማጣት እና በወደፊቱ ህይወታችን ብሩህነት እርግጠኛ አለመሆን ነው በማለት የተስፋ መቁረጥን ትርጓሜ እንደሚያስረግጡት Tan (2007) ያስቀምጣሉ፡፡

## 2.2. የቀደምት ጥናቶች ክለሳ

በዚህ ንዑስ ክፍል ስር የነገረህላዌ የትችት አንጻርን በዋነኛ መነጽርነት በመጠቀም የተለያዩ ህልውናዊ ጭብጦችን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የዳሰሱ እና በአጠቃላይ ከዚህ ጥናት ጋር በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ዝምድና ያላቸው የምርምር ሥራዎች ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸውን ተዛምዶ በሚያሳይ መልኩ ቅኝት ተደርጎበታል፡፡ የነገረህላዌ የትችት አንጻርን ዋነኛ ማዕቀፍ በማድረግ የተለያዩ የህልውናዊነት ጉዳዮችን ለመተንተን የሞከሩ በርካታ የሃገር ውስጥም ሆነ የውጭ ጥናቶች አሉ፡፡ ይሁን እንጅ በዚህ ጥናት በተለይም ደግሞ በዚህ ንዑስ ክፍል ውስጥ ቅኝት የሚደረግባቸው የሃገር ውስጥ ጥናቶች ብቻ ናቸው፡፡ ምክንያቱም የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የህልውናዊነት ጭብጦች በሕፍ ረጅም ልቦለድ ውስጥ እንዴት እንደተገለጹ እና ምን አይነት ስፍራ እንደተሰጣቸው በመመርመር በዚህ ልቦለድ ናሙናነት ደግሞ የነገረህላዌ ፍልስፍና ከአማርኛ ሥነጽሑፍ ጋር ያለውን ዝምድና መግለጥ በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ በአገር ውስጥ እና በአማርኛ ሥነጽሑፍ ሥራዎች በተካሄዱ ጥናቶች ላይ ትኩረት ማድረጉ የተሻለ እና ተመራጭ ይሆናል በሚል ጽኑ እምነት ቅኝቱ በአራት የአማርኛ ሥነጽሑፍ ጥናቶች ላይ አነጣጥሯል ማለት ነው፡፡ ታዲያ ይህ መጠነሰፊ ፍልስፍናዊ ንድፈሃሳብ እና ዘርፈብዙ ጭብጣዊ ገጽታዎቹ በሃገር ውስጥም ሆነ በሃገር ውጭ ጥናቶች በተለያዩ ጊዜያት የትኩረት ነጥብ መሆናቸው እነዚህ ህልውናዊ ጉዳዮች ከሥነጽሑፍ ጋር ያላቸውን ቁርኝት በድምቀት ማሳያ መሆኑንም ልብ ይሏል፡፡

ለዚህ ጥናት በተመረጠው እና የደራሲ አዳም ረታ ሥራ በሆነው ሕፍ ረጅም ልቦለድ ላይ እስካሁን በተደረገ ፍተሻ መሠረት ምንም አይነት ጥናት ያልተካሄደበት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በሌሎቹ የደራሲው ሥራዎች ላይም ቢሆን የተካሄዱት ጥናቶች ከዚህ የምርምር ሥራ ጋር ምንም አይነት ዝምድና ከሌላቸው በዚህ ክፍል ውስጥ ክለሳ አይደረግባቸውም፡፡ በዚህ መሠረት ከዚህ ጥናት ጋር ግንኙነት ያላቸው አራት ጥናቶች

ብቻ ተመርጠው ካላቸው ዝምድና ወይም ቅርበት አንጻር በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ከዚህ ጥናት ጋር በእጅጉ ቀረቤታ ያለው የመሰለች ተሻገር "የሰውልጅ ህልውና በቅበላ እና ኩርቢት ድርሰቶች፣ ነገረህላዌ ንባብ" የተሰኘው እና በነሃሴ 2010 ዓ.ም በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበው ጥናት ነው፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥም በርካታ የህልውናዊነት ጭብጦች ለጥናት ለተመረጡት ድርሰቶች *ታሪክ ናቸው* ከሚል ድምዳሜ ላይ ተደርሷል፡፡ ዓላማውም ቢሆን የኸው እንደሆነ በዚሁ ጥናት ውስጥ እንዲህ ተጽፎ እናነባለን "የዚህ ጥናት አብይ ዓላማ በአለማየሁ ገላጋይ ቅበላ የድርሰት ስራ ውስጥ የተገለጸው ታሪክ የነገረህላዌ ታሪክ መሆኑን ፈክሮ ያሳያል" (ገጽ፣ 5)፡፡ ከዚህ አንጻር በዓላማ አነጻደፍ ከዚህ ጥናት ጋር በተወሰነ መልኩም ቢሆን ልዩነት አለው፡፡ የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ፣ ለምርምር በተመረጠው የልቦለድ *ሥራ* ውስጥ የተገለጹ የህልውናዊነት ጭብጦችን ለይቶ በማውጣት እና ተንትኖ በለምርምር ተመረጠው ልቦለድ ከነገረህላዌ ፍልስፍና ጋር ያለውን ግንኙነት ማሳየት ሲሆን፣ የመሰለች ጥናት ደግሞ ለምርምር የተመረጠው *ቅበላ* ልቦለድ ሙሉ በሙሉ የነገረህላዌ ታሪክ እንደሆነ ለማሳየት ያለመ ነው፣ ለዚህም ነው በሁለታችን መካከል የዓላማ አነጻደፍ ልዩነት አለ ማለቴ፡፡

የመሰለች ጥናት በደራሲ አለማየሁ ገላጋይ ሁለት የልቦለድ *ሥራዎች (ቅበላ* እና *ኩርቢት)* ላይ ምርምር ለማድረግ ወስኖ የተነሳ ይሁን እንጅ ከዓላማው ላይ የተካተተው ግን አንዱ ማለትም *ቅበላ* የተሰኘው ልቦለድ ብቻ ሆኖ እናነባለን፡፡ ታዲያ በዚህ አኳኋን ለምርምር የተመረጡት ሁለቱ ልቦለዶች ሆነው ሳለ፣ ዓላማው በአንዱ ልቦለድ ላይ ብቻ መወሰኑ ለምን እንደሆነ አልተገለጠልኝም፡፡ በዚህ የመሰለች ጥናት ውስጥ *ኩርቢት* ልቦለድ ለርዕስ ማሟያነት ካልሆነ በስተቀር የጥናቱ አይነተኛ ናሙና አለመሆኑን ያስተውሏል፡፡

የመሰለች ጥናት ምንም እንኳን ከዚህ በላይ ያስቀመጥኩትን ዋና ዓላማ አንግቦ የተነሳ ቢሆንም ጭንቀት፣ ተስፋ መቁረጥ፣ ነጻነት፣ ከንቱነት፣ ሞት፣ በይታወርነት፣ ትክክለኛነት እና ትክክለኛ አለመሆን እና ክስተት የተሰኙ ስምንት ያህል የህልውናዊ ጭብጣዊ ገጽታዎች ተተንትነውበታል፡፡ ከዚህ አንጻር የጥናቱ ዓላማ፣ ርዕሰጉዳዩ እና ተተንትኖ የቀረበበት መንገድ ዝምድናው አልታየኝም፡፡ ምክንያቱም የጥናቱ ትንተና በዓላማው ላይ እንደተቀመጠው የድርሰቶቹን ሙሉ ታሪክ የህልውና ታሪክ መሆኑን ከማሳየት ይልቅ

ከህልውናዊነት ጭብጦች ላይ ያነጣጠረ ነውና፡፡ ማለትም ከፍ ሲል እንዳልኩት፣ ዓላማው የድርሰቶቹን ታሪክ የህልውና ታሪክነት ማሳየት ሆኖ ሳለ የህልውና ጭብጦች መተንተናቸው የተቀመጠውን ዓላማ አሳክቷል ለማለት አያስደፍርም የሚል እምነት አለኝ፡፡ ከትንተናው ላይም ቢሆን በዚሁ ክፍል ከቀረበው ሐተታ አንጻር በደፈናው “የነገረህላዌ ትንተና” ተብሎ ከሚቀመጥ ይልቅ “የነገረህላዌ ጭብጦች ትንተና” በሚል ቢስተካል የተሻለ ይመስለኛል፡፡ ስለዚህ በአንድ በኩል፣ ከአላማው እና ከቀረቡት ርዕሰነገሮች አንጻር የነገረ ህላዌ ንድፈሃሳብን ከልቦለዶቹ ታሪኮች ጋር ለማዛመድ የተሞከረበት ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ በትንተናው ውስጥ የህልውናዊነት ጭብጦችን መሠረት ያደረገ መሆኑ የሥራውን ወጥነት አጠያያቂ ያደርገዋል ብየ አምናለሁ፡፡ እንደ ዓላማው ከሆነ ደግሞ ጭብጦቹን በዋናነት ተንትኖ ማሳየት ነበረበት፤ አሊያም እንደዚህ አይነቶቹ ጥቅል ርዕሰነገሮች እና የተነደፉት ዓላማዎች የነገረህላዌ ጭብጦችን ማሳየት መሆኑን በግልጽ ማሳየት ነበረባቸው፡፡ የሆነው ሆኖ፣ ይህ የመሰለች ጥናት *በተመረጡት የሥነ ጽሑፍ አሃዶች ውስጥ የህልውናዊነት ጭብጦችን ለማሳየት የቀረበ ነው* ብንል እንኳን፣ ከዚህ ጥናት ጋር በሚከተሉት ጉዳዮች ይለያያል፡፡

ይህ ጥናት በዋናነት አምስት የህልውናዊነት ጭብጦችን የሚያነሳ ሲሆን ከመሰለች ጥናት ጋር የሚጋራው *ተስፋ መቁረጥ (Despair)* የተሰኘውን ጭብጥ ነው፡፡ ከዚህ ባለፈ ግን ሌሎቹ በዚህ ጥናት ውስጥ የተነሱት የርዕይ መነጠቅ፣ ሁኔታዊነት እና ኦናነት የተሰኙት ሦስት ጭብጦች በመሰለች ጥናት ዉስጥ በፍጹም ያልታዩ ሲሆን፣ ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ *ነጻነት* የሚባለው ጭብጥ *ከምርጫ እና ውሳኔ* ጋር በአንድነት በተደበላለቀ መልኩ ተተንትኗል፡፡ ይሁን እንጅ ነጻነት እና ኃላፊነት ምንም ጊዜ የማይላቀቁ የህላዌ ጭብጦች በመሆናቸው በዚህ ጥናት ውስጥ ከመሰለች በተለየ መልኩ በአንድ ላይ ተጣምረው እና ከምርጫ (Choice) በተለየ መልኩ በስፋት ተተንትነዋል፡፡ ምክንያቱም *ምርጫ እና ውሳኔ* ራሳቸውን የቻሉ ሌላ የህልውናዊነት ገጽታዎች እንጅ ከነጻነት ጋር በአንድነት የሚታዩ አይደሉም የሚል እምነት አለኝ፡፡ ስለሆነም እነዚህ ጉዳዮች ይህን ጥናት ከመሰለች ጥናት የተለየ የሚያደርጉት ዋናዋና ቁምነገሮች ናቸው፡፡ ከእነዚህ ጉዳዮች በተጨማሪ ደግሞ ለጥናት ማሄጃነት የተመረጡት የሥነ ጽሑፍ *ሥራዎች* (ናሙና ልቦለዶች)ም የተለያዩ ናቸው፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የቴዎድሮስ ገብሬ *በይነ ዲሲፕሊናዊ የሥነ ጽሑፍ ንባብ* በሚል ርዕስ በ2001 ዓ.ም በታተመው መጽሐፍ ውስጥ ካሉት አራት ያህል "መጣጥፎች" መካከል "የአማርኛ የርእይ መነጠቅ ልቦለዶች" የሚል ርዕስ የተሰጠው "መጣጥፍ"ከዚህ ጥናት ጋር በእጅጉ ይዛመዳል፡፡ በዚህ የቴዎድሮስ ገብሬ ጥናት ውስጥ እራሳቸው ቴዎድሮስ "በአንድ ዘመን ተመሳሳይ ጭብጦችን ይዘው ብቅ ያሉ እና በአማርኛ ሥነጽሑፍ ዘርፍ እምብዛም አቻ የማይገኝላቸው ልሂቃን ሥራዎች ናቸው"በሚሏቸው አራት የልቦለድ ሥራዎች *ፍቅር እስከ መቃብር፣ የቴዎድሮስ እንባ፣ አደፍርስ እና ከአድማስ ባሻገር* ውስጥ የተንጸባረቁ የጋራ የህልውና ትራጀዲያዊ ገጽታዎች ማለትም ሞት፣ የርእይ መነጠቅ እና ቀቢጸተስፋ እና ግዞት የተሰኙ ሦስት ጭብጦች ከነገረህላዌ ንድፈሃሳብ አንጻር ተብራርተው ቀርበዋል፡፡

የቴዎድሮስ ጥናት በአራት ልቦለዶች ላይ ያተኮረ ንጽጽራዊ ጥናት (comparative study) ሲሆን፣ ይህጥናት ደግሞ በአንድ የልቦለድ ሥራ ላይ ብቻ በመወሰን እና ትኩረቱን በማሳረፍ በተመረጠው ድርሰት ውስጥ የተገለጹ ወይም የተንጸባረቁ የህልውናዊነት ጭብጦችን አጉልቶ ለማሳየት የሚደረግ ጥናት ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ መሰረት የናሙና ምርጫችን የተለያየ ነው ማለት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ በቴዎድሮስ ጥናት ውስጥ *የርእይመነጠቅ* እና *ቀቢጸተስፋ* በአንድ ላይ ተጣምረው ቀርበዋል፡፡ እርግጥ ነው፣ የርእይ መነጠቅ እና ቀቢጸተስፋ ብቻ ሳይሆኑ ሌሎቹም አብዛኛቹ የህልውናዊነት ጭብጦች እርስ በእርሳቸው ጥብቅ የሆነ ግንኙነት ያላቸው ከመሆናቸውም በላይ አንዱ በሌላው ሳቢያ የሚፈጠሩ ክስተቶች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ማለትም እያንዳንዱ የህልውናዊነት ጭብጦች ተዛማጅ እና ተዋላጅ ናቸው (ቴዎድሮስ፣ 2001)፡፡ ይህ ከሆነ ታዲያ ሁሉን በአንድ ላይ አቆራኝቶ ማየት (ከነጻነት እና ኃላፊነት ውጭ) የተለመደ አካሄድ ሆኖ አላገኘሁትም፤ የተለመደ አካሄድ አለመሆን ብቻም አይደለም፡፡ በእኔ የእምነት እና የእውቀት ልክ የርእይ መነጠቅ እና ቀቢጸተስፋ የተለያዩ እና ለየብቻቸው ተነጣጥለው ሊታዩ የሚገባቸው እንደዚሁም ለየራሳቸው መገለጫዎች ያሏቸው ሁለት የተለያዩ የህልውናዊነት ጭብጦች ናቸው፡፡ ስለሆነም እነዚህ ሁለት የተለያዩ ጉዳዮች በዚህ ጥናት ውስጥ ለየብቻ ተነጣጥለው በስፋት ይተነተናሉ፡፡ ከዚህ ውጭ ግን በሁለታችን ጥናቶች ውስጥ የተነሳ ወይም የጋራ የሆነ የህልውናዊነት ጭብጥ የለም፡፡ በዚህ ረገድ በአንጻር ምርጫ እንመሳሰል እንጅ በምናነሳቸው ጭብጦች እንለያያለን ማለት ነው፡፡

በሦስተኛ ደረጃ ከዚህ ጥናት ጋር የሚዛመደው ደግሞ የአክሊሉ ደሳለኝ "Existentialism in the selected creative works of Adam Reta" የተሰኘው እና በ2010 በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ዲግሪ መሚያ ይሆን ዘንድ ለእንግሊዝኛ ትምህርት ክፍል (በእንግሊዝኛ ቋንቋ) የቀረበ ጥናት ነው፡፡ ይህ ጥናት ከአዳም ረታ ሥራዎች ውስጥ *ግራጫ ቃጭሎች ረጅም ልቦለድ እና ሌልዛቤል፣ ስፌንክስ፣ ከልጅቷ፣ የአበቦች ታሪክ፣ የድንች መዋሲት እና እቴመይቴ የሎሚ ሽታ* የተሰኙት አጫጭር ታሪኮች ላይ የተሰናዳ ሲሆን፣ ይኸውም አዳምን የተጠናወቱትን የነገረህላዌያን ሃሳቦች (Existentialist ideas) በግልጽ በመለየት አዳምን ሥነ ጽሑፋዊ የነገረህላዌ ሊቅ ወይም የነገረህላዌ ጸሐፊ (Literary existentialist) ብሎ ለመሰየም ታልሞ የተካሄደ ጥናት እንደሆነ በአላማው ላይ በግልጽ ሰፍሯል፤ "the main objectives of this study are to evidently identify the existentialist ideas with which Adam is overwhelmed and to title him as a literary existentialist" (P. 4)፡፡ በዚህ ረገድ ይህ ጥናት ሞልተው ከተረፉት የደራሲው ሥራዎች መካከል ጥቂቶቹን ብቻ ለዚያውም ደግሞ ለዚህ ጥናት ተስማሚ ሆነው የተመረጡትን ብቻ በመመልከት ደራሲውን ሙሉ በሙሉ "ከነገረህላዌያን ጸሐፍት ጎራ የሚመደብ ጸሐፊ ነው" ከሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱ ለእኔ አልታየኝም፡፡ መታወቅ ያለበት ነገር ግን፣ ደራሲው የነገረህላዌ አሳባዊ መባሉን በግሌ ለመንቀፍ ሳይሆን፣ ከዚህ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ግን በእነዚህ ሥራዎች ናሙናነት ብቻ መገደቡ በቂ አይደለም ለማለት ነው፡፡

ልክ ከላይ በመሰለች ጥናት እንዳነሳሁት፣ ከዓላማው ጋር ያላቸው ተዛማጅነት በውል ባይገለጥልኝም፤አሥር የሚደርሱ የህልውና ጭብጦች ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ ከእነዚህ መካከል ግን የአክሊሉን ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የጋራ የሚያደርገው አንደኛው ማለትም *ተስፋ መቁረጥ (Despair)* የተሰኘው ጭብጥ ሲሆን ሌሎቹ ግን በዚህ ጥናት ውስጥ ከታዩት የተለዩ ናቸው፡፡

በአክሊሉ ጥናት *ነጻነት (Freedom)* ለብቻው *ከኃላፊነት (Responsibility)* ተለይቶ ቀርቧል፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ ግን እነዚህ ጉዳዮች በጥምረት ይተነተናሉ፡፡ ከዚህ ባለፈ ግን በአክሊሉ ጥናት ፈጽሞ ያልታዩ ሦስት ጭብጦች በዚህ ጥናት ውስጥ ይነሳሉ፡፡ በተጨማሪም የአክሊሉ ጥናት በእንግሊዝኛ ቋንቋ የቀረበ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ እንደሚታወቀው በአማርኛ ቋንቋ ቀርቧል፡፡ ይህ ጥናት በእነዚህ ጉዳዮች ከአክሊሉ ጥናት

የሚለያይ ሲሆን፣ የአንጻር ምርጫን በተመለከተ ግን ይህ ጥናትም ሆነ የአክሊሉ ጥናት ተመሳሳይ ናቸው፡፡

አራተኛው እና የመጨረሻው ከዚህ ጥናት ጋር የሚዛመደው ደግሞ የጸደይ ወንድሙ “The case of existence in Feqer eske Maquaber, Kadmas Bashager and Geracha Qacheloch: From Existentialist Perspective” የተሰኘው እና በ2007 በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበው ጥናት ነው፡፡ ይህ የጸደይ ጥናት ይዞት የተነሳው ዓብይ ዓላማ በተመረጡት መጻህፍት ውስጥ ያሉትን የእያንዳንዱን ገፀ ባህርይ የህልውና ጉዳዮች (case of existence) ማብራራት ሲሆን፣ ዋና እና ማዕቀፉ ደግሞ የSartre የነገረህላዌ አተያይ ነው፤ ወይም የጥናቱ መተንተኛ አንጻር በ Sartre የህላዌ እሳቤ ላይ ብቻ የተገደበ ነው፡፡

በጸደይ ጥናት ውስጥ የተመረጡት እነዚህ ሦስት የተለያዩ ታላላቅ የአማርኛ ሥነጽሑፍ ሥራዎች በአንድ ንድፈሃሳብ ብቻ ለዚያውም ደግሞ በአንድ የንድፈ ሃሳብ አራማጅ ጽንሰሃሳብ መነጽርነት ብቻ መታየታቸው ተገቢነቱ አልታየኝም፡፡ ምክንያቱ ደግሞ የሥነጽሑፍ ጠበብቶች (ቴዎድሮስ፣ 2001) እንደሚሉት ሥነጽሑፍን ለአንድ ንድፈሃሳብ ተገዥ የማድረግ ስህተት ውስጥ መግባት ይመስለኛል፡፡ ሥነጽሑፍን ለአንድ ንደፈሃሳብ ተገዥ እንዲሆን አደረግን ማለት ደግሞ መልዕክቱን በውል ከማጤን ይልቅ (በማጤን ፋንታ) ከንድፈሃሳቡ ጋር ለማገናኘት በሚደረግ ጥረት ወዳልተገባ ስህተት እናመራለን የሚል እምነት አለኝ፡፡ ስለዚህ ከ Sartre አተያይ በተጨማሪ ሌላ ንድፈሃሳብን ተጠቅሞ መተንተን ባይቻል እንኳን ቢያንስ ከሙሉ የንድፈ ሃሳቡ መዕቀፍ አንጻር ማለትም የእነ Kierkegaard, Nietzsche, Heidegger, Marx እና የመሳሰሉት የህልውናዊነት አተያዮችን ባካተተ መልኩ ቢፈተሹ አይሻልም ነበረ ወይ? የሚል ጥያቄ ፈጥሮብኛል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የ Sartre አተያይ ብቸኛ ምርጫ የሆነበት ምክንያትም ቢሆን እንዲሁ ግልጽ አይደለም፡፡ ከዚህ ባለፈ ግን ለምርምር የተመረጡት ሦስት መጻሕፍት ከ Sartre የነገረህላዌ እሳቤ አንጻር ብቻ በስፋት ተተንትነውበታል፡፡ ይኸውም ልክ እንደ ቴዎድሮስ ገብሬ “መጣጥፍ” ሁሉ ትኩረቱን በሦስት ረጃጅም ለቦለዶች ልይ በማድረግ በድርሰቶቹ ገጸ ባህርያት አማካኝነት የተንጸባረቁ የህልውና ጉዳች (case of existence) የተብራሩበት ንጽጽራዊ ጥናት (comparative study) ነው ማለት ይቻላል፡፡

የሆነው ሆኖ፣ በዓላማ እና ርዕሰ ጉዳይ አነጻደፍም ሆነ በአንጻር ምርጫ ይህ ጥናት ከጸደይ ጥናት በእጅጉም ባይሆን የተለያየ ነው፡፡ የአንጻር ምርጫን በተመለከተ የ Sartreን አተያይ ጨምሮ የሌሎችንም የነገረህላዌ ልሂቃን ሥራዎች እሳቤ ያካተተ ይሁን እንጅ አጠቃላይ ማዕቀፉ የነገረህላዌ ፍልስፍና መሆኑ ደግሞ ይህ ጥናት ከጸደይ ጥናት ጋር የሚጋራው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ ባለፈ ደግሞ ቀደም ብየ እንደጠቀምኩት የጸደይ ጥናት በእንግሊዝኛ ቋንቋ የቀረበ መሆኑም ሌላው ከዚህ ጥናት የሚለየው ዓብይ ጉዳይ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## የህልውናዊነት ጭብጦች ትንተና በአፍ ረጅም ልቦለድ ውስጥ

በዚህ ምዕራፍ፣ በምዕራፍ አንድ ስር በተገለጸው የመተንተኛ ወይም የመፈከሪያ ስልት እንደዚሁም በምዕራፍ ሁለት ስር በተደራጁት ንድፈሃሳባዊ ትንታኔዎች መሰረትነት በዚህ ጥናት ለትንታኔ በተመረጠው አፍ (2010) ረጅም ልቦለድ ውስጥ የተንጸባረቁ ዋናዋና የህልውናዊነት ጭብጦች ተለይተው እና ተተንትነው የሚቀርቡ ይሆናል፡፡

ከዚህ በፊት በሁለት ምዕራፎች በተደጋጋሚ እንደተነሳው የዚህ ጥናት መሰረታዊ ዓላማ ለምርምር የተመረጠው ልቦለድ ውስጥ የተገለጹትን የህልውናዊነት ጭብጦች በመለየት እና በመተንተን ልቦለዱ ከነገረህላዌ ፍልስፍና ጋር ያለውን ግንኙነት መመርመር በመሆኑ፣ ለትንታኔ በተመረጠው አፍ ረጅም ልቦለድ ውስጥ  ያሉትን ገፀ ባህርያት (የእውኑ ዓለም ሰዎች ወኪሎች) ህልውና በመመርመር ላይ ያነጣጥራል፡፡ በዚህ ልቦለድ ውስጥ ያሉ ገፀ ባህርያት የየራሳቸውን ህላዌ ለማስቀጠል በግልጽም ሆነ በህቡዕ የሚታትሩ፣ የየራሳቸውን የህይወት ፍልስፍና ተከትለው የሚነጉዱ አሊያም ደግሞ በቤተሰቦቻቸው፣ በአካባቢያቸው ወይም በማህበረሰባቸው ደንብ እና ሥርዓት ውስጥ ሆነው በ"ኗሪ አኗኗሪ" ብሂል ውስጥ የሚዋልሉ የሁለት ዓለም (የራሳቸው እና የሌሎች) ሰዎች፣ የየራሳቸውን ምርጫ እና ውሳኔ ያላስጠበቁ እና በአጋጣሚዎች በተሞላች ህይወት ውስጥ የሚዋኙ፣ ሁሉም ማለት በሚቻል እረገድ ያቀዱትን፣ የተመኙትን፣ ያለሙትን ያላሳኩ (በአንዱ ሲሞላ በሌላው ወገን የሚፈስባቸው)፣ በመጨረሻም የህይወት (በአለም) ትርጉም የጠፋባቸው፣ የሰነቁትን ተስፋ የሚያጡ ሆነው ተቀርጸዋል፡፡ በመሆኑም በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የእነዚህ ገፀ ባህርያት የህላዌ መልኮች በጥልቀት ይተነተናሉ፡፡

በዚህ ጥናት ለትንተና የተመረጠው አፍ ረጅም ልቦለድ ውስጥ ጌርሳሞት፣ ዘሪሁን፣ ገለታ፣ ባካፋ እና አቡ ራሚሱ (አቡ (ቅጽል ስም )) የሚሉ ስያሜዎች የተሰጧቸው አምስት ዋና ገፀ ባህርያት እና በርካታ ንዑሳን ገፀ ሰዎች የተካተቱበት ሥራ ሲሆን፣ በዚሁ ልቦለድ ውስጥ በዋናነት ተንጸባርቀዋል ተብለው የታመነባቸው አምስት ዋናዋና የህልውናዊነት ጭብጦች ማለትም፤ "ነፃነት እና ኃላፊነት"፣ "እናነት"፣ "ሁኔታዊነት"፣ "የርእይ መነጠቅ" እና "ቀቢጸተስፋ" የተሰኙ የሰው ልጅ ህልውናዊ ገጽታዎችን በልቦለዱ ውስጥ ባሉ ገፀ ባህርያት

(በተለይ ደግሞ በእነዚህ በአምስቱ ገፀ ሰዎች) ህላዌ ናሙናነት እና ቀደም ሲል እንደተጠቆመው በምዕራፍ ሁለት ላይ የተነሱ ንድፈሃሳባዊ ሐተታዎችን መሰረት በማድረግ ከዚህ ጥናት ጋር ዝምድና ያላቸውን ደግሞ በማምጣት እና በማላመድ በልቦለዱ ታሪክ መንደርደሪያነት ትንታኔው ቀርቧል፡፡ እነዚህ የህልውናዊነት ጭብጦች ደግሞ እርስ በእርስ ካላቸው ጥብቅ የሆነ ቁርኝት አንጻር ዝምድናቸው የምክንያት እና ውጤት ያህል ቅርበት ያለው ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህን የህልውናዊነት ጭብጦች ተዛምዶ (መደራረብ) አስመልክተው ቴዎድሮስ ገብሬ (2001፣ 147)፣ "እነዚህ ገጽታዎች አንዱ ከሌላው ይዛመዳሉ፤ ይዋለዳሉ፡፡ ተዋረዳዊ የሚመስልም ግንኙነት በመሃላቸው አለ" በማለት ያብራራሉ፡፡

በዚህ ጥናት ለናሙና በተመረጠው ሐፍ ረጅም ልቦለድ ውስጥ ያሉት የዋና ገፀ ባህርያት ቁጥር እና በዋናነት የሚነሱት የህልውናዊነት ጭብጦች ቁጥር መመሳሰል ግን አጋጣሚያዊ እንጅ ሌላ አንዳችም ሚስጥር የለውም፡፡ ስለሆነም ከእነዚህ ዋና ገፀ ባህርያት በተጨማሪ ሌሎች ንዑሳን ገፀ ባህርያትም እንዳስፈላጊነቱ በትንተናው ሂደት ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉበት አጋጣሚ ብዙ እንደሚሆን ልብ ይሏል፡፡ የሆነው ሆኖ በዚህ የትንታኔ ሂደት ደግሞ በዚሁ የጥናቱ የትንተና ምዕራፍ ውስጥ ለሚነሱ ዓበይት ጉዳዮች ማሳያ ይሆናሉ ተብለው የታመነባቸውን ሐተታዎች ከዚሁ ልቦለድ ውስጥ በተለያየ መጠን ቀንጨብ በማድረግ ጭብጦችን በጉልህ ለማሳየት ይሞከራል፡፡ በዚህ መነሻነት "ነፃነት እና ኃላፊነት"፣ "እናነት"፣ "ሁኔታዊነት"፣ "የርእይ መነጠቅ" እና "ቀቢጸተስፋ" የተሰኙት ዋና ዋና የህልውናዊነት ጭብጦች ከዚህ በታች ባሉት ክፍሎች በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

### 3.1. ነፃነት እና ኃላፊነት

ቀደም ሲል ስማቸው ከተዘረዘሩት እና ለትንተና በተመረጠው ረጅም ልቦለድ ውስጥ ካሉት ገፀ ባህርያት መካከል ሁለቱ ዋና ዋና ገፀባህርያት ማለትም፣ ራሚሱ እና ጌርሳሞት ለዚህ ክፍል ዋነኛ ማሳያዎች ተደርገው ተወስደዋል፡፡ ራሚሱ ወይም በቤት ስሙ አቡ፣ በትምህርት አቀባበሉ የተመሰከረለት እና በአካባቢው ዘንድ የት ይደርሳል የተባለለት ልጅ ነው፡፡ በመጨረሻም ትምህርቱን በእንግሊዝኛ በዲግሪ ቋንቋ ጨርሶ ካገኛት ጋር እየተወዳጀ፣ የመጠጥ እና የጫት ሱሶች ማደሪያ ሆኖ፣ በአስራት ጉትጎታ በአንድ መስሪ ቤት በህዝብ ግንኙነት ሙያ ላይ ተሰማርቶ ይገኛል፡፡ ሥራ የገባውም ከፍቅረኛው

ከአሥራት ጭቅጭቅ ለመዳን አለፍ ሲል ደግሞ ለሱሱ ማስታገሻ የሚሆን ገንዘብ ያገኝ ዘንድ እንጅ የአሠሪ እና ሠራተኛ ህጉ ተመችቶት አይደለም፡፡ በእርግጥ በእናቱ በኩል ሐኪም፣ በአባቱ በኩል ደግሞ የዩኒቨረሲቲ መምህር ስለሆነ እና በአስተዳደጉ ምንም ሳይጎድልበት ስላደገ ይሆናል ይህን ያህል ወጣ ያለ አስተሳሰብ ያላበሰው፡፡ ራሚሱ በባህሪው ከቤተሰቦቹ ብቻ ሳይሆ ከሰዎች የተለየ ገፀ ባህርይ ነው፡፡ ስለሆም እያንዳንዱ ህልውናው በራሱ እና በራሱ ብቻ የተወሰነች ናት፤ በህይወቱ ውስጥ እራሱ የፈለገውን ሁሉ ከማድረግ የሚያስቆመው ምንም ነገር የለም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ለቤተሰቦቿ አንድ የሆነችው (በተለይ ለአባቷ) ጌርሳሞት በተለይም የ9ኛ ክፍል ተማሪ ከሆነች ጊዜ ጀምሮ አብዛኛዎቹን የሰፈሯን ጎረምሶች በከናፍሮቿ ውበት ያንበረከከች ውብ ገፀ ባህሪ ናት፡፡ በትምህረቷ ደግሞ ገና የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ናት፡፡ ጌርሳ የደን ልማት ባለሙያዋ እነቷ መግደላዊት አሊያም ደግሞ ሾፌሩ አባቷ አቶ ኮላሴ ከሚፈቅዱላት ውጭ የትም የማትንቀሳቀስ፣ ምንም የማትሠራ እና በተቀመጠላት ሥርዓት ውስጥ ብቻ የምትኖር ገፀ ባህሪ ናት፡፡ ከዚህ አንጻር በሐፍ ረጅም ልቦለድ ውስጥ የእነዚህን ሁለት ገጸባህርያት ህላዌ (existence) የተመለከትን እንደሆነ፣ አንዳቸው ከሌላቸው ጋር የሚቃረን ኑባሬን ሲመሩ እንታዘባለን፤ አንዳቸው በሙሉ ነጻነት፣ አንዳቸው ደግሞ በነጻነት ናፍቆት፡፡

ለነገረ ህላዌያን፣ ነጻነት ማለት የሰው ልጅ ያለምንም አይነት ማህበራዊም ሆነ መንፈሳዊ ደንብ እና ሥርዓት ጣልቃገብነት በራሱ እምነት እና ፍላጎት የትኛውንም ተግባር የመፈጸም ሂደት ነው (Daigle, 2010)፡፡ ይህን የህልውናዊነት ማዕከላዊ ጭብጥ ደግሞ በሐፍ ረጅም ልቦለድ በሁለት መንገድ ማየት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው በዚህ አይነት ነጻነት ህልውናቸውን የሚመሩ ሰዎች የሚሄዱበት መንገድ ምን ይመስላል? ነጻነታቸውስ እስከምን ድረስ ይዘልቃል? እውን ሙሉ በሙሉ ከምንም ነገር ነጻ ናቸውን? የሚሉትን መጠይቆች መሠረት ያደረገ አተያይ ሲሆን፣ የሁለተኛው ደግሞ ከዚህ በተቃራኒው አብዛኛው የህይወት መስመራቸው በሌሎች አካላት (በቤተሰቦቻቸው፣ በአካባቢያቸው፣ በጎሳቸው) አማካኝነት ቀድሞ የተቀየሰላቸው እና በዚያ ቅጥርግቢ ውስጥ በመወሰን በተበጀላቸው ጥርጊያ ብቻ እንዲሄዱ በልዩ ልዩ ደንብ እና ሥርዓቶች አማካኝነት የሚገደዱ ገፀ ሰዎችን ህላዌ የሚመለከት ይሆናል፡፡ በዚህ መሠረት በዚህ ልቦለድ ውስጥ ነጻነት እና የነጻነት እጦት ገጽ ለገጽ ተስለው እናገኛቸዋለን፡፡

ከዚህ በላይ ተደጋግሞ እንደተነሳው፣ በሐፍ ረጅም ልቦለድ ውስጥ ነጻነት ሁለት ገጽታዎች አሉት ተብሏል፣ ቀዳሚውን ሃሳብ ያየን እንደሆነ፣ በዚሁ ልቦለድ ውስጥ የምናገኘው ዋናው ገፀ ባህሪ ራሚሱ ለዚህ ዋና ማሳያ ነው፡፡ ራሚሱ ከልጅነቱ ጅምሮ ያማረውን እየበላ፣ የፈለገውን እየጠጣ፣ ያየውን እየለበሰ፣ ሲፈልግ በወጣበት የሚያድር፣ ሲያሻው ደግሞ እስከፈለገው ድረስ  አምሽቶ የሚገባ እና በታልቅ ነጻነት ውስጥ ያደገ ልጅ ነው፡፡ "…በልጅነቱ እንዲህ ሆኜ ቀባጢሶ የሚባል ነገር አላውቅም፡፡ ቤተሰቦቾ ሃብታሞች ነበሩ፡፡ የቸገረኝ ጊዜ ትዝ አይለኝም፡፡ በየሳምንቱ መጨረሻ ምሳ እበላ የነበረው ከፈረንጅ ጋር ነው…" (አዳም ረታ፣ 2010፤ 172) ታዲያ ራሚሱ መጠጥ የጀመረውም ገና በልጅነት ዕድሜው ከቤተሰቦቹ ጋር በደባልነት ይኖር በነረበት ወቅት እንደነበር ታሪኩ ይነግረናል፤ "ዛሬ 106ኛ *ሃንግኦቨሬ* ላይ ነኝ፡፡ የሰከርኩበትን ጊዜ ቆጥሬአለሁ፡፡ በየሳምንቱ እየሰከርኩ ስገባ ሁለት አመት ሆነኝ… (አዳም ረታ፣ 2010፤ 144)፡፡ እስካሁን ድረስ ምንም እንኳን አደጋ ባይደርስበትም አሁን አሁን ግን አምሽቶ እና ሰክሮ ወደቤቱ በሚገባ ስዓት አደጋ ሊደርስበት እንደሚችል መፍራት እና መጠራጠር ጀምሯል፡፡ ይህ ማለት እንደ ነገረህላዊያን እምነት ማንኛውም ነጻ ሰው በራሱ ድርጊት ምክንያት ለሚመጣበት አደጋ እራሱ ተቀዳሚ ተጋላጭ ሊሆን እንደሚችል ያውቃልና ይህንኑ ኃላፊነትም ለመቀበል እራሱን አዘጋጅቷል ማለት ነው፡፡ ይህን ጉዳይ አስመልክቶ Daigle (2010) Sartreን ጠቅሰው፣ አንድ ሰው ነጻ ከሆነ ኃላፊውም ሙሉበሙሉ እራሱ ግለሰቡ እንጂ እሱ በፈጸመው ድርጊት ሳቢያ ለሚመጣ ችግር ሁሉ ከራሱ የተሻለ ኃላፊነቱን ሊቀበል ሚችል ምንም ኃይል የለም በማለት ያብራራሉ፡፡ ራሚሱ ማድረግ ያሻውን ሁሉ ከመፈጸም አንዳችም አካል፣ ምንም ሃይል የማይገድበው፣ የፈለገውን ሁሉ ከማደድረግ ማንም የማያስቆመው በራሱ ምኞት እና ፍላጎት ብቻ የሚመራ (ራስ መር) ፍጡር ነው፡፡ የትኛውም አይነት ሃይማኖታዊም ሆነ ማህበራዊ ሥርዓት ለራሚሱ ረብ ያለው ጉዳይ አይደለም፡፡ እንዲያውም በዚህ አይነት ሂደት ውስጥ የሚራመድ ወገን ለሱ መሳለቂያው ነው፤

> […] ሌሎች ሰዎች ቤተ ክርስቲያን በመመላለሳቸው ባይመለከተኝም እኔን ይደክመኛል፡፡ የሐበሻ ሃይማኖተኞች የቀራቸው ነገር በጸሎት ሃይል ሽሮ ወጣቸውን በመልአክ ማሰራት ነው፡፡ ፈጣሪ የሚወዳቸው ከሆነ የሚፈልጉትን ሳይለምኑት አይሰጣቸውም? ፈጣሪ እንደ ምድራዊ ሹም ለምን ልምምጥ እና ደጅ ጥናት ይፈልጋል? ይሄኔ ሰዎቹ ደጀሰላም ገብተው ደጋግመው በቁስ የሚጠዘጠዙት እሱ

ያመጣውን እሱ እስከሚመልሰው የተባለውን አረፍተ ነገር ነው፡፡(አዳም ረታ፣ 2010፤155)

ሃይማኖት እና ባህል የሚባሉት ጉዳዮች ለራሚሱ ምንም ነገር ናቸው፡፡እሱ እራሱ በመሰለው እና ባመነበት መንገድ መራመድ እንጂ የትኛውንም አይነት ህገ ሃይማኖት ወይም ባህላዊ ሥርዓት አብዝቶ ይጠላል፡፡ አዎ ለነጻነቱ እንቅፋት እንደሆኑ ያምናልና እነዚህን አይነት ሁነቶች እንዲህ ያማርራል፤ "…ብደበርም ድብርቴን አንድ ሁለት እያለኩ እየቆጠርኩ አረጃታለሁ እንጂ የሃይማኖት እና የባህል አሥርቱ ቃላት ኦሪቶች ላይ ሙጭጭ አልልም፡፡ ሰባኪ ፈጣን ሲሆን፣ ተሰባኪ ንፍጣም ይደረጋልና" (አዳም ረታ፣ 2010፤ 164)፡፡ እነዚህ ጉዳዮች በህይወት ዘመኑ ሁሉ አምኖ ሊቀበላቸው የማይችሉ ባዕድ ነገሮች ናቸው፡፡ እንደ Sartre እምነት አለም የተፈጠረችው ከየትኛውም አይነት ልማደዊ እና ሃይማኖታዊ ሥርዓት ውጭ ነው፡፡ ነገር ግን ለእነዚህ ሁሉ ነገሮች መፈጠር ምክንያቱ የሰው ልጅ ነው፡፡ ሰው ደግሞ በራሱ ምንም ነው፤ ማንነቱ የሚወሰነው እራሱ በሚፈጥረው የህይወቱ መልክ ነውና፣ ራሚሱ ሌሎች ሰዎች የፈጠሯቸውን መሰል ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ቀኖናዎች ፈጽሞ አይቀበልም፡፡ የሚመራው እራሱ በፈጠረው የህላዌ መነጽር ነው፡፡ እንደ ነገረህላዌ እሳቤ አድርባይነት እና ይሉኝታ አንዳች ፖለቲካዊ ወይም ሃይማኖታዊ ሥርዓት የወለዳቸው ሁነቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም እነዚህ ጉደዮች የሰዎችን ነጻነት የሚጋፉ ልማዶች ናቸው፡፡ ስለዚህ በእነዚህ ተግባራት የተሞሉ ኑረቶች ሁሉ በነጻነት እጦት የተተበተቡ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ የሖፉ ራሚሱም ከእነዚህን መሰል አጓጉል የህላዌ ውሱንነቶች ራሱን አርቆ የሚኖር ከመሆኑም በላይ ዘወር ብሎ የሌሎችን ነጻነት አልባ ህይወት በመታዘብ ሃሳቡን እንዲህ ይተርካል፡፡ "…እዚች ምድር ላይ ከሚኖረው ስንቱ ነው ግን በልቡ የሚያስበውን ሳይፈራ ሳይቸር የሚያደርግ? ሁላችንም ቲያትረኞች ነን" (አዳም ረታ፣ 2010፤166) በማለት እራሱን ጨምሮ ይጠይቃል፡፡ ነጻነት የሌለው ሰው ደግሞ በራስ መተማመን የጎደለው መሆኑን በመግለጽ በእራሱ አንደበት የተርካል፡፡ ራሱን ከሌሎች በዙሪያው ካሉ ሰዎች ጎራ በአብሮነት እንደ ቲያትረኛ ይቁጠር እንጅ ነጻነት የሌለበት ህይወት በራስ መተማመንን እንደሚያሳጣ ጠንቅቆ ያውቃልና፤ የቅዱሳን መጣህፍት ቃላት፣ ማህበራዊ የሞራል እሴቶች፣ የአድርግ አታድርግ ሥነ ምግባራዊ አስተምህሮዎች መሳለቂያዎቹ እንጅ ቦታ የሚሰጣቸው ነገሮች አይደሉም፡፡ የጓደኛው የንጉሱ እህት እና የእሱ የቅርብ ጊዜ የወሲብ ጓደኛው የሆነችው አሥራት "…..ብሩህነት ያለፀባይ የትም አያደርስም……. ሰራ መያዝ አለብህ…… አንተን የመሰለ

ልጅ ያውም ዲግሪ ያለው መንዘላዘል የለበትም.....” ባለችው ጊዜ “ከመጽሐፍ ቅዱስ በተቀዳ አማርኛ ጠዝጥዛኝ ብቅ እያልኩ እንድጠይቃት፣ ስራም በአጭር ጊዜ ልታስይዘኝ እንደምትችል ጣቷን አቀላጥፋ አጬኻ ሞራል እና ሥነ ምግባር ትን እስኪለኝ ግታኝ፣ ለምጠጣው ቢራና ሃምበርገር ከፍላ ሄደች” (አዳም ረታ፣ 2010፤167) በማለት ይሳለቅባታል፤ የእሷን *ማህበረሰብህን መምሰል አለብህ* ውትወታ ከቁብ ሳይቆጥር እሷኑ መልሶ ይታዘባታል፡፡ ራሚሱ በየትኛውም አይነት ህግ እና ሥርዓት ስር መውደቅ ፈጽሞ አይፈልግም፤ይልቁኑ በእነዚህ ስር ያሉት ሰዎች ያስጠሉታል፡፡

ራሚሱ (አቡ) በየትኘውም የህላዌ ጉዞው ውስጥ ከማነኛውም አይነት ዘልማዳዊ እና ይትባህላዊ ድርጊት ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ነጻ ነው ማለት ይቻላል፡፡ እራሱ የመረጠውን እና ያመነበትን ተግባር ሳያመነታ ይሠራል፤ የሚመቸውን መንገድ እራሱ ይቀይሳል፤ እሱኑ በቀናው ጎዳና ይነጉዳል፡፡ የማንንም ህግ፣ የትኛውንም ሥርዓት አይፈራም፤ በምንም አይወሰንም፡፡ ይህ ገደብ የለሽ ነጻነቱ እስከ ፍቅር (የወሲብ?) ጓደኛ ምርጫው ድረስ ሳይቀር ይዘልቃል፡፡ የራሚሱ የፍቅር (የወሲብ?) ምርጫዎች አስቴር፣ ጌርሳሞት ወይም አሥራት ብቻ አይደሉም፤ አጋጣሚዎች ሁሉ ያገናኙት ሴቶችም ጭምር እንጂ፡፡ በመሆኑም በእሱ የፍቅር (የወሲብ?) ምርጫ ውስጥ ዕድሜ፣ መልክ፣ ቁመና እና መሰል የወል መስፈርቶች ዋጋ የላቸውም፤ ሴት መሆን ብቻ የራሱ በቂ መመዘኛው ነው፤ በጾታ ከእሱ ተለይቶ መገኘት፡፡ ከአሥራት ጋር ያለው ግንኙነት ደግሞ ይህን ሃሳብ ያጎላዋል፡፡

ራሚሱ እና አሥራት በወሲብ ይጎዳኙ እንጅ ሁለቱ በምንም ነገር እኩዮች አይደሉም፡፡ የሚለያዩዋቸውን ሌሎች ነገሮች ትተን እድሜያቸውን ብቻ ብንመለከት እንኳን በመካከላቸው ቢያንስ የአሥር አመት ልዩነት እንዳለ እራሱ ይተርካል፤ “... ትእዛዝ ባልሰማም፣ ከእኔ ቢያንስ አሥር ዓመት ታረጃለችና ላከብራት ብየ ተቀመጥኩ፡፡ በተጨማሪም ስካር ስላደከመኝ ያገኘሁት ቦታ በረንዳ ስር ተቀመጥኩ” (አዳም ረታ፣ 2010፤ 167)፡፡ አሥራት በአሥር አመታት ጥበልጠዋለች፡፡ ይሁን እንጅ በዚህ የእድሜ ልዩነት ሳቢያ የሚመጣውን የሌሎች ሰዎች ስላቅ እና አሽሙር ከቁብ ሳይቆጥር ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ከአሥራት ጋር የወሲብ ጊዜያትን ማሳለፉን ቀጥሎበታል፡፡ በተለይም በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በየትኛውም ባህላዊ እሴት ሁለት የፍቅር ተጓዳኞች ቢያንስ በእድሜ እኩዮች ቢሆኑ ይመረጣል፡፡ ከዚህ አለፍ ሲልም ይህ የእድሜ እኩያነት ጉዳይ

ከባህላዊ እሴትነት በተሻገረ መልኩ ህገመንግሥታዊም ነው ማለት ይቻላል፡፡ ነገር ግን የህገ መንግሥታዊውን ጉዳይ ለጊዜው እናቆየው እና ወደ አገራችን ልማዳዊ (ነባራዊ) ሁኔታ መለስ ብለን ያየን እንደሆነ፤ ቢያንስ ቢያንስ ቀደም ብዩ እንደጠቆምኩት በተመሳሳይ የእድሜ ክልል ውስጥ መገኘት አለባቸው፤ ከዚህ ውጭ ግን ወንዱ ከሴቷ በተወሰነ የእድሜ ክልል ቢበልጥ ይመረጣል፡፡ ይህ የሚሆንበት ደግሞ የራሱ የሆነ ባህላዊ አመክንዮ አለው፡፡ ይኸውም በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ጥልቁ ኃላፊነት የወንዱ በመሆኑ በእድሜ ብቻ ሳይሆን ከተቻለ በሁሉም ነገር የላቀ መሆን አለበት ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ከዚህ ባለፈ ደግሞ እድሜ እየጨመረ በሄደ ቁጥር በተለያዩ ተፈጥሯዊ ሥርዓቶች ምክንያት ሴቶች ቶሎ ለድካም የመጋለጥ እድላቸው ከፍ ያለ ነው ተብሎ ስለሚታመን እና የእነሱን ጉልበት እስከመጨረሻው ድረስ ለመጠቀም ካለ ፍላጎትም የመነጨ ይመስለኛል፡፡ የሆነው ሆኖ፣ ይህ አይነቱ ባህላዊ ሥርዓት ለራሚሱ የሚያስጨንቅ ጉዳይ አይደለምና ከላይ እንዳልኩት በአሥር አመታት ከምትበልጠው አሥራት ጋር የወሲብ ጓደኝነት ከመሰረተ ውሎ አደሯል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ፣ “መወሰን” የሚሉት ጣጣ ለራሚሱ ፈጽሞ አይመለከተውም፡፡ “…አስቴር ጊዜዋ ሲደርስ በራሷ ሰአት ወደምትፈልገው ትሄዳለች፡፡ አሥራትም እንደ እኔ በቸልታ የማያበሳጫት ሌላ ስራ የምታስይዘው ጎረምሳ ታገኝ ይሆናል፡፡ እንዲሁ እየተወዛወዝኩ እኖራታለሁ እንጅ በማንም አልወሰንም…” (አዳም ረታ፣ 2010፤ 169) ራሚሱ በፍቅር ጉዳይ የመጡለትን ሁሉ ይቀበላል፤ ከሄዱ ደግሞ ምንም ሳይመስለው ይሸኛል፡፡ ከዚያ ባለፈ ግን ተወስኖ መቀመጥ የሚሉት ብሂል ለእሱ ከተረት ተረት ያለፈ ትርጉም የለውም፡፡ በኑረቱ ውስጥ ጥሩ እና መጥፎ፣ ጽድቅ እና ኩነኔ የሚባሉትን ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ ልማዶች ፈጽሞ አያውቃቸውም ማለት ይቻላል፡፡ ህላዌው በየትኛውም አይነት ሥርዓት የተገደበ አይደለም፤ በራሱ እምነት እና ፍላጎት የተበጀ እንጂ፡፡ ይህን አይነቱን ነጻነት ፣ Daigle (2010, 44)፣ “There is no God who decides for us and imposes values on us; accordingly, we must creat our own values” በማለት ይገልጹታል፡፡ ይኸውም የሰው ልጅ የሚከተላቸውን እሴቶች ሊያዘጋጅ የሚችል ፈጣሪ (አምላክ) የሚባል ኃይል ከቶውንም የለም፡፡ ስለሆነም የሰው ልጅ እራሱ የራሱን እሴት መፍጠር አለበት የሚል ትርጓሜን ይሰጠናል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ በአፍ ረጅም ልቦለድ ውስጥ የምናገኘው ራሚሱ የራሱን አለም በራሱ የሚያዘጋጅ እና ህይዎቱን (በሙሉ ማለት ይቻላል) በራሱ መንገድ ብቻ በመምራት ከየትኛውም ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ቀኖና እራሱን ያራቀ ወይም ሙሉ ነጻነት ያለው ገፀ ሰብዕ ነው ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡ ከዚህ ባለፈ ግን በፈጣሪ ማመን ለእሱ "አይናማ እውርነት" ነው፤ ማለት ዐይን እያለው ማየት የማይችል፡፡ ከዚህ ከፍ ሲልም ከዕውቀት በእጅጉ የራቀ መሃይምነት እና ምንም አይነት የማወቅ ፍላጎት የሌለው ባለድፍን አዕምሮ መሆን ነው፡፡ የሚከተለው የራሚሱ ንግግር ይህን ሃሳብ ያደምቀዋል፤ "… መውደቅ የፈለገ በዘጠኝ እግርም ያንሸራትተዋል፡ ማለት በእግዚአብሄር ደማቅ እርግማን ስር የወደቀ…..የማወቅ ንፉግነት በአእምሮው ሽለቆ እንደ አውሬ ያደባበት በዛም የሚፈነጭበት፡፡ …" (አዳም ረታ፣ 2010፤ 176) ስለዚህ እምነት ለእሱ ይህን አይነት ትርጉም ካለው እንዴትስ ይመራበታል? ለምንስ ብሎ እያወቀ ወደአለማወቅ ይሄዳል? እራሱን ከዚህ አይነት ጭፍንነት ይሰውራል እንጂ፡፡

ነጻነት ተፈጥሮን አለመቀበል አይደለም፡፡ የራስን አለማዊ ህይወት ወይም ደግሞ ከዚህም በረቀቀ እና በጠለቀ መልኩ የእራስን ማንነት መፍጠር እንጂ፤ ከመንጋዊ አስተሳሰብ መላቀቅ፡፡ ከማንኛውም ማህበራዊ አሊያም ሃይማኖታዊ አስተምህሮ ወይም ሥርዓት በላቀ የራስን ሥርዓት በራስ መገንባት እና መከተል፤ ይህንን ተከትሎ ለሚመጣው ግብረመልስም እራስን ማዘጋጀት እንደሆነ ከአሁን በፊት በተደጋጋሚ ተነስቷል፡፡ ይህ ማለት የሰው ልጅ ወደምድር ከመጣበት ጊዜ አንስቶ የሚከተለውን የህላዌ ጉዞ የሚመለከት ነው፡፡

ለራሚሱ፣ እነዚህን መንጋዊ የሆኑ ሰብዓዊ አስተሳሰብ እና ሥርዓቶች መከተል ከተፈጥሮ ጋር ያላቸውን ጥልቅ ልዩነት በውል አለመለየት ነው፡፡ እምነት እና ሥርዓት ሰብዓዊ፣ ምድራዊ መሆናቸውን ጠንቅቆ ያውቃልና እሱም በምድር ላይ እስካለ ጊዜ ድረስ ከወል ማንነት እርቆ መኖርን መርጧል፡፡ እናም አለምን በራሱ እጅ የሚጠፈጥፍ፣ የራሱን መልክ በራሱ የሚሠራ ነጻ ግለሰብ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ይህን ነጻነቱን ደግሞ በራሱ አንደበት እንዲህ ይተርካል፤ "ይሄ አቡ ተፈጥሮን የሚቀበል ነው፡፡ እጣዬን ሳላመነታ እወስዳለሁ፡፡ ዝናብ ቢመታኝ አላማርርም፡፡ ደንቆሮ ሆኜ ብፈጠር አላማርርም፡፡ ዕውር ብሆን አላማርርም፡፡ ዝናብን አልረግምም፡፡ ደንቆሮነትን አልፈጥርም፡፡ ተፈጥሮዬ ባመጣው እና እኔ ባመጣሁት ጉድ መሃል መለየት እችላለሁ፡፡…" (አዳም ረታ፣ 2010፤ 187)

አዎ! ነጻነት መሆን የምንችለውን መሆን፣ መስራት የምንችለውን መስራት እንጅ ህገ ተፈጥሮን ሙሉ በሙሉ በጭፍኑ መቃወም አይደለም፡፡ ከዚህ በተቃራኒው ደግሞ የራሱን ሃሳብ በልበ ሙልነት የማይከተል ሰው ከራሱ የራቀ፣ ህልውናው ከሌሎች የተቀዳ እና የሌሎችን ህላዌ በማስመሰል የተጋ፣ እንደ በቀቀን የሌሎችን ህይወት የሚያስተጋባ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ይህን አይነት የህላዌ ጉዞ ደግሞ ራሚሱ እንዲህ ሲያወግዘው እንታዘባለን "…አገሩ የሰርጀሪ ነው፡፡ እራሱን መሆን የከበደው ተራነቱን የሚያንቀለጳጵስ ከርፋፋ ነው" (አዳም ረታ፣ 2010፤ 199)፡፡ ይህ አይነቱ ሥርዓት ደግሞ እንደ ነገረህላዌያን እምነት የውሸት ማንነትን (False identity) መገንባት ነው፡፡ ራሚሱ የራሱን ገደብ አልባ ነጻነት በራሱ ያወጀ፣ በአገሩ ከተለመደው መደበኛ የህላዌ ሥርዓት የወጣ እና እሱንም እስከመጨረሻው ጥግ ድረስ አጥብቆ የሚቃወም ገፀ ሰብ ነው፡፡

> እንደ ብልጣብልጦች በአፌ እያሳለጥኩ ትናንሽ ህልም እየፈለፈልኩ ለትናንሽ ግብ አልኖርም፡፡ ወደዚህ ምድር እንዲሁ ለመኖር አልመጣሁም […] እንደ ጥንት ዘመዶቼ ወይ እንደዛሬዋ እማማ በየደጀሰላሙ አልጎዘጉዝም፡፡ በቅዱስ መጽሐፍ ቸርቻሪዎች አልጠፈርም፡፡ እዛ ፔርሙዝ ውስጥ ያለው ሻይ ደም ነው ብልህ አንተ ምን አገባህ? አንቺስ?" (አዳም ረታ፣ 2010፤ *205)*

በሐፍ ረጅም ልቦለድ ውስጥ የተገለጸውን እና ሁለተኛውን የነጻነት ገጽታ ስንመለከት ደግሞ የልቦለዱን ሌላኛዋን ዋና ገፀባህሪ ጌርሳሞትን እናገኛለን፡፡ ጌርሳሞት እንደማንኛውም ሰው ከልጅነት ጊዜዋ ጀምሮ ከእድሜ እኩዮቿ ጋር እንደልቧ መጫወት፣ መቦረቅ እና መደሰት ያልቻለች ነጻነት ይሉት ነገር ህልም እነደሆነ የቀረባት፣ መሆን የሚገባት ሁሉ ቀድሞ በቤተሰቦቿ የተዘጋጀላት ከእነሱ ፈቃድ እና ፍላጎት ውጭ የትም የማትንቀሳቀስ የቁም እስረኛ ናት ማለት ይቻላል፡፡ በዚህም ምክንያት የሰፈሯን ወጣቶች ሳይቀር መቅረብ እየፈለገች በቤተሰቦቿ የተቀመጠላት ህግ እና ሥርዓት ትልቅ የግንብ አጥር ነውና ያራርቃታል፤ ጠንካራ እና ረጅም ገመድ ሆኖ ያስራታል፤ የለቀቃት መስሎ መልሶ ይስባታል፡፡ በያጋጣሚው አብረዋት የሚቆሙትን ሰዎች ሁሉ ሃይማኖት እና ጎሳ እንድትለይ በአባቷ ህግ ትገደዳለች፤ ወይም ከነአካቴው ከማንም ጋር እንዳትቆም ትከለከላለች፡፡ ከዚያ ልጅ ጋር ለምን ቆምሽ? ለምን ከማንም ጋር አብረሽ ትሄጃለሽ? መንገድ ዳርስ ምን ትሠሪያለሽ? እና በመሰል ጥያቄዎች ትነተረካለች (አዳም ረታ፣ 2010፤ 42-43 አጽንኦት ተጨምሮበታል)፡፡ በዚህ የተነሳ የምትወዳቸውን እና የሰፈሯ ልጆች የሆኑትን እነ ገለታን፣ ዘሪሁንን፣ ባካፉን እና ራሚሱን ሰላምታ ለመስጠት ትሳቀቃለች፡፡

ምክንያቱ ደግሞ አንድም የወላጆቿ ቁጣ እና ማስፈራሪያ፣ አንድም ደግሞ የአካባቢዋ ማህበረሰቦች አግቦ እና ግልምጫ በእጅጉ ያስፈሯታል፡፡

> ኩርደዳ አሳብጦ የሸሚዟን የደረት ቁልፍ ያስከፈታትን ደረቷን እየነካካች (እረስታ ነው ታዲያ?) በዓይኗ ቁጥ ታጤነዋለች፡፡ ወደእሱ እንዳትሄድ አለ አይደለ 'ፈለገችው' ተብላ 'መጠጣትዋ' ነው፡፡ […]… 'ወሬ ይደርሰኛል፣ ከዚያ ከጠንቁዋይ ልጅ ጋር (ምን ማለት ነው?) ገለታ ምናምን ከሚባል ነውዝ አይሽ እና ነገረኩ' ይላታል አባትዋ፡፡ ፀጉራማ ቡጢ ጨብጦ፡፡ … (አዳም ረታ፣ 2010፤ *50-52)*

አንድን ጎረምሳ ሞቅ አድርጎ ሰላምታ መስጠት የጨዋ ደንብ እንዳልሆነ ታውቃለችና (በማህበረሰቧውስጥ) ደፍራ ለማየት እንኳን ተቸግራለች፡፡ "ደሞ ሰላምታ ብቻ ሰጥቶ ማለፍ ክልክል ነው፡፡ አንደኛ ጨዋነት አይደለም፡፡ ደሞ አባቷ እንደነገራት ስታዲዮም ከሚያሳየው ብልግናው በስተቀር ሁለመናው ጨዋ ነው፡፡ እናም የጨዋ ልጅ ናት፡፡ ዘረ ጨዋ፡፡" (አዳም ረታ፣ 2010፤ 50) ደግሞ የአባቷ ማስፈራሪያስ? ስለዚህ እየወደደችው እና ሰላም ማለት እየፈለገች እንኳን እንዳልፈለገች መስሎ ማለፍ ቤተሰባዊ ብሎም ማህበራዊ ግዴታዋ ሆኖ እንታዘባለን፡፡ ማለትም እነዚህ ቤተሰባዊ እና ማህበራዊ ህግጋት የመናገር፣ ሃሳቧን የመግለጽ፣ እንደፈለገች የመንቀሳቀስ እና የማፍቀር ነጻነቷን ሁሉ ገፈው አራቁተዋታል፡፡ ታዲያ በምን ድፍረቷ ይህን ሁሉ ድንበር አልፋ ውስጧ የሚያዝዛትን፣ አዕምሮዋ የሚመራትን፣ ህሌናዋ የሚፈቅድላትን ህላዌ ታመቻች? እንዴትስ የራሷን የህይወት መንገድ ትቀይስ? በተለይ ደግሞ የአባቷ መርህ እና ህግጋት በህይወቷ ውስጥ አደገኛ አጥር ሆኖ አላራምድሽ ብሏታል፡፡ "አባቴ ወላጄ ብቻሳይሆን የቤታችን የፖለቲካ ጉዳይ ኃላፊ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፣ የባህል ሚኒስትር እና ያው የማይቀረው የስድብ እና የጥፊ ሚኒስትር ነው" (አዳም ረታ፣ 2010፤ 36) ለጌርሳሞት ሁሉም የህይወት እንቅስቃሴዋ በወላጅ አባቷ የተወሰነ (በተለይም እያደገች ስትመጣ) ነው፤ ስለዚህ እንድትኖር የሚፈቀድላትም ይህንኑ የተወሰነላትን ብቻ ነው፡፡

የጌርሳ የነጻነት እጦት እያደገ መጥቶ አሁን አሁን ነጻነቷን ያጣችው ዕድለቢስ በመሆኗም ይመስላት ጀምሯል፤ የተፈጠረችበትን ትውልድ፣ ተወልዳ ያደገችበትን ዘመን ታማርራለች፤ የድሮውን ሥርዓት ናፋቂ ሆናለች፤ ነጻነቷን የነጠቃት ዘመኑ፣ ወቅቱ ይመስላታል፡፡

> ታዲያ ሳይቀናኝ ቀርቶ ነው መሰለኝ የሆነ የአገሩ ፖለቲካ በተበላሸ፣ ነገር በሚያበዛ፣ ከንተሮ አፍ፣ አፍሪካዊ ሁሉ የጎሪጥ በሚተያይበት እንከፍ ዘመን ኮረደድኩ፡፡ ሲባል

*እንደምሰማው ቢ.ያንስ በዘፈን (የማንን ድምፅ ማን ያምናል?) ድሮድሮ ዐይን ተገልጦ የታየ ይወደዳል፡፡ ዛሬ አይን ተገልጦ ይወደድና እንደ አባቴ 'ጎሳው ምንድን ነው?' 'ሃይማኖቱ ምንድን ነው?' ይባላል፡፡* (አዳም ረታ፣ 2010፤ *43)*

ነጻነት ለጌርሳሞት የሰማይን ያክል ሩቅ ነው፤ አንጋጥጠው የሚያዩት ግን የማይደርሱበት አድማስ፤ የነጻነት ምኞት የተጠናወታት ልክፍት፣ የሚከተላት እርግማን ሆኖባታል፡፡ በሁለት በውል እንኳን በማይረግቡ ገመዶች በሁለት የተለያዩ አቅጣጫዎች ታስራ፣ ሥራዋ ሁሉ መካከል ላይ እንደፔንዱለም መዋለል ብቻ ሆኗል፤ ወዲህ በአባቷ ማስፈራሪያ፣ ወዲህ ደግሞ በዙሪያዋ ሰዎች አግቦ፡፡ በዚህም ሳቢያ በዙሪያዋ ያሉ ሰዎችን እና ማህበራዊ ሥርዓቱን ሁሉ መፍራት፣ መውደድን ደብቆ መያዝ (ያልወደዱ መምሰል) እና በይሉኝታ ብቻ መኖር የህይወቷ ዕጣ ፋንታዎች ሆነዋል፡፡ "ጌርሳ ጌርሳሞት በህልሟ ያየችውን፣ ነቅታም የተመኘችውን፣ ተመኝታም የወደደችውን፣ ወዳየሻተችውን፣ ውስጡ **ብልግና** አይጠፋምና አታወራውም፡፡ ማን እራሱን ትዝብት ዐይን ስር የጥላል? እግዜር የመውደድ ወጉን ለምን ከኀታችነትና ከስንፍና ጋር ሰፋው?" (አዳም ረታ፣ 2010፤ *5*9)

ለጌርሳሞት ብልግና ማለት ሃሳብን በግልጽ መናገር፣ መውደድን በነጻነት ማራመድ ነው፡፡ ይህን ነው ቤተሰቧ ብሎም ማህበረሰቧ ያስተማራት፡፡ አሁን ይህ ሥርዓት ለእሷ ሰብዓዊ ብቻም ሳይሆን ተፈጠሯዊም ጭምር ነው፤ እንዲህ እንዲሆን (መውደድ እና ፍርሃት እንዳይላቀቁ) ፈጣሪ ይሁን ብሎ ያበጀው (የፈጠረው) ይመስላት ጀምሯል፡፡ አንድም ገና ከልጅነት ዕድሜዋ ጀምሮ ከእናቷ ጋር በመመላለስ በእምነት ተቋም (ቤተክርስቲያን) ቀኖና ውስጥ ያደገች በመሆኗ፣ አንድም ደግሞ በተደጋጋሚ እንደተነሳው በልዩ ልዩ ማህብራዊ ሥርዓት ስለታጠረች ሳትወድ በግድ ስሜቷን እንድትደብቅ፣ በእነዚህ ልማዶችም ቂም እንድትቋጥር ተገድዳለች፡፡ "አተኩራ በቅሬታ እና በፀፀት ዐይን አየችው፡፡ ወንድ ልጅ መሆን ተመኘች፡፡ የምትፈልገውን ልትጠይቀው፡፡ ስለምትወደው ነገር ልታወራው፡፡ የባጥ የቆጡን፡፡ የሰማይ እና የመሬቱን፡፡ አንድ እሁድ እለትም በህልሟ እዳየችው፡፡" (አዳም ረታ፣ 2010፤ 67)

አሁን ጌርሳ በተፈጥሮ ጣልቃ መግባት ትዳዳለች፡፡ ይህን ሁሉ ነጻነት የነፈገቻት ተፈጥሮ ትመስላት ጀምራለች፡፡ እሷ የምታውቀው ፍቅርን ሳይፈራ መግለጽ፣ የመሰለውን በግልጽ መናገር በአጠቃላይ ሙሉ ስሜቱን በነጻነት ማራመድ የሚችለው ወንድ ልጅ መሆኑን

ነው፡፡ ለእንደሷ አይነቷ ሴት የፍቅር ማህደር መሆን እንጅ ስሜትን እነደአትሮንስ ገልጦ ማሳየት ከቶውንም በቀላሉ የሚቻል አይመስላትም፡፡

ጌርሳሞት ሌላው ሁሉ ቀርቶ አልባሳቶቿ እንኳን በብተሰቦቿ ምርጫ የሚወሰኑ ናቸው፡፡ ጥሩ ነው ብላ ያሰበችውን እና የመረጠችውን ልብስ ስትለብስ *አለማረብሽም እና ለውጪ* ትባላለች፤ ይህንን የአባቷን ግልምጫ ፈርታ አሮጌ ልብስ ስትቀይር ደግሞ "ደሞዟ ያልተከፈላት ገረድ መስለሽ" ሰሜን በክፉ ልታስነሺ ነው ትባላለች፡፡ *ታዲያ* የመጨረሻው አማራጪ አበቷ የሚወደውን እና የአባቷ ምርጫ የሆነውን ብቻ መልበስ ትገደዳለች (አዳም ረታ፣ 2010፤ 90)፡፡

በአጠቃላይ ጌርሳሞት መሆን ያለባትን በሙሉ የሚወስኑት እና ህይወቷንም የምትመራው ቤተሰቦቿ ባስቀመጡላት የአድርጊ/አትድርጊ መርህ እና ሥርዓት ውስጥ ሆኖ እናገኛለን፡፡ እያንዳንዱ የህይወት እንቅስቃሴዋ በቤተሰቦቿ የተወሰነላት በመሆኑ ይህንን ደንብ ተላልፋ የሆነ ድርጊት ብትፈጽም እንኳን የሚከተላት የባሰ ቁጣ እና ማስፈራሪያ፣ አለፍ ሲልም ከአቅም በላይ ተንጠራርታ የጨበጠችውን መንጠላጠያ በመበጠስ ከነበረችበት በታች እንድትወረወር የሚጋብዝ ያልተመጣጠነ አጸፋ ይሆናል፤ ከአንድም ሁለት ጊዜ የፍቅር ርዕዩዋን ያጣችውም በዚሁ ምክንያት ነው፡፡

እንግዲህ እስካሁን እንዳየነው ነጻነት በሐፍ ረጅም ልቦለድ ውስጥ በሁለት መለኩ ተገልጧል ብሎ መደምደም ይቻላል፤ ወዲህ እንደራሚሱ ወሰን በሌለው ነጻነት፣ ወዲህ ደግሞ እንደ ጌርሳሞት በለከት አልባ የነጻነት ንፍገት፡፡

## 3.2. እናነት

ለዚህ ክፍል ብቸኛው ማሳያ ይሆን ዘንድ የተመረጠው ገፀ ባህርይ ራሚሱ ነው፡፡ ራሚሱ ከዚህ ከፍ ብሎ በ "ነጻነት እና ኃላፊነት" ክፍል ውስጥ እንዳየነው የገደብ አልባ ነጻነት ባለቤት ነው፡፡ ይህ ከመጠን ያለፈ ነጻነቱ ደግሞ አድጎ እና ተወሳስቦ ከእናነት ውስጥ ይጥለዋል፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥም ይህ ጉዳይ እንደሚከተለው በስፋት ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

እናነት ከነገረህላዊ ፍላስፍና አንጻር ሲታይ ከፈጣሪ የጸዳ ማንነትን መገንባት እንደሆነ Tijen Tan (2007) Sartreን ጠቅሰው ያብራራሉ፡፡ በዚህ መሠረት በሐፍ ረጅም ልቦለድ

ውስጥ ካሉት ገፀ ባህሪያት መካከል ራሚሱ (አቡ) በዚህ እሳቤ ውስጥ ወድቆ እናስተውላለን፡፡

ከላይ ባየነው ክፍል ውስጥ በተደጋጋሚ እንደተነሳው ራሚሱ ከልጅነት እስከ እውቀት ድረስ የገደብ አልባ ነጻነት ባለቤት እንደሆነ እንታዘባለን፡፡ ይህ ወሰን የለሽ ነጻነቱ ደግሞ በስተመጨረሻ ከባዶነት ውስጥ ወስዶ ይጥለዋል፡፡ ራሚሱ በህይወቱ ውስጥ ተስፋ የሚጥልበት፣ ያግዘኛል፣ ይረዳኛል ብሎ የሚያስበው አንዳችም አምላካዊ ሃይል የለውም፡፡ ለእሱ ከሁሉም ነገር መሸሻው፣ መደበቂያው የትንባሆ፣ የመጠጥ፣ የጫት እና የወሲብ ሱሶች ናቸው፡፡ ምንም ያህል በህይወቱ ቢሰላች እና ቢማረር ከእነዚህ ነገሮች ያለፈ ተስፋ የሚጥልበት ልዕለ ተፈጥሮ ሃይል የለም፤ ፈጣሪዎቹ እነኚህ ነገሮች ናቸው፡፡ እራሱን በእነዚህ ተግባራት ለማግኘት ይኳትናል፡፡ ከእነዚህ ተግባራት ውጭ ያለው ፍጡር ሁሉ ያስጠላዋል፤ ታዲያ ይህን ጥላቻውን ደግሞ መልሶ በእነዚህ ውስጥ ይፈልጋል፡፡ “በሁሉ ነገር ይበሳጫል፡፡ ከፈጠረው እግዚአብሔር እስከ ወለደው አባቱ ድረስ ያበሳጩታል፡፡ በየመሃሉ ያለው ፍጡር እና ቁስ መአት ነው፡፡ የሚያማርረውን ሁሉ በከፊል የሚረሳው ከወዳጆቹ ጋር ብቻ ሲሆን ነው፡፡” (አዳም ረታ፣ 2010፤ *15-16*)

ወዳጆቹ የተባሉት የሰፈር አብሮ ደጎቹን እነ ገለታ፣ ዘሪሁን እና ባካፋን ነው፡፡ ይሁን እንጅ አነሱም ቢሆን ከዚህ ሃሳቡ ጨርሰው ከቶውንም አያስጥሉትም፡፡ እንዲያውም ከፍ እያሉ ሲሄዱ ሁሉም ጌርሳሞትን የየራሳቸው ለማድረግ የእርስ በእርስ ሽኩቻ ውስጥ ይገባሉ፡፡ አቡ ደግሞ ለጓደኞቹ የሚሰጠው ከሱሶቹ የተረፈውን ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ወደዚች ምድር መጣሉ ያማርረዋል፤ ያበሳጨዋል፡፡ ይህን ምሬቱን እና ብሶቱን የሚጋራው፣ ከዚህ የቁጣ መዓት ውስጥ የሚያወጣው ምንም ነገር እንደሌለ ያምናልና፤ ተስፋ የሚጥልበት ፈጣሪ እንኳን የለውም፡፡

እንደ ነገረ ህላዌያን እምነት ኦናነት ተስፋ የሚጣልበት፣ መመኪያ የሚሆን፣ ሲቸግር የሚጠየቅ፣ ሲሞላ የሚመሰገን፣ አንዳችም ሃይል እንደሌለ ማመን እና የዚችን አለም ክስተት ሁሉ በገዛ እራስ መጋፈጥ መቻል ነው (Tan, 2007)፡፡ ታዲያ ይህ አይነቱ የህላዌ ሂደት በህይወት ውስጥ ምክንያት አልባም ያደርጋል፡፡ ራሚሱም የሚመካበት ፈጣሪ የለውምና እንዴት እና ለምን እንደሚኖር አያውቅም፡፡ ደስ ያለውን ብቻም ሳይሆን ያጋጠመውን ህይወት ነው የሚገፋው፤ የመረጠውን ብቻ ሳይሆን ከፊቱ ያገኘውን ድርጊት

ነው የሚፈጽመው፡፡ አሁን አሁን ነጻነቱ አድጎ እና ተወሳስቦ፣ የህይወት መስመሩ ተጣፍቶበት ግራ ያጋባው፣ ያወዛግበው ይዟል፡፡ ይህንን ተከትሎም አንዳንዴ በህይወቱ ውስጥ ጭንቀት እና ስጋት ይጋረጥበት ጀምሯል፡፡

> አንዳንዴ ቁጭ ብዬ ሳስብ የምፈልገውን ሳላደርግ ምናልባት እተቀመጥኩበት ምናልባት እተኛሁበት ምናልባት ቢሮዬ ኩቢክል ውስጥ ተቀምጬ ሳንጋጥጥ ምናልባት የመጀመሪያዬን ቢራ ሳጠናቅቅ ቡትሌ ሳጤስ ምናልባት ገና በምርቃና መፍሰስ ስጀምር ምናልባት ሽንቴን ልሸና የሱሪ ዚፔን ስፈታ ምናልባት ሳነጥስ ምናልባት በሹካዬ ጎንጉኜ ያነሳሁት የመጀመሪያ ፓስታ ጉርሻዬ አየር ላይ እያለ ምናልባት አርፌ እተኛሁበት ወይም ዝም ብሎ አሁን ከሩብ ሰዓት በኋላ የምሞት ይመስለኛል፡፡ እግዜራችሁ የማልማት ብቻ ሳይሆን የማጥፋት ጥበበኛ ነውና፡፡ ከዚህ ፍርሃት ምን እና ማን እንደሚያድነኝ ግን አለውቅም፡፡(አዳም ረታ፣ 2010፣ *17)*

ኦናነት ከጭንቀት ጋር የተገናኘ ሲሆን፣ ይኸውም የሰው ልጅ በዓለማዊ ህይወቱ ውስጥ የሚረዳው ወይም የሚያግዘው አንዳችም ሃይል በዙሪያው እንደሌለ በሚያምንበት ወቅት የሚፈጠር ስሜት እንደሆነ Mallah (2016) ያብራራሉ፡፡ እንደ ነገረህላዌ ልሂቃን እምነት በገደብ የለሽ ነጻነት ውስጥ ያሉ ሰዎች ከእነርሱ የተሻለ እና ከራሳቸው በላይ የሆነ መሪ የሌላቸው ፍጡራን እንደሆኑ አድርገው እራሳቸውን ይቆጥራሉ፡፡ በዚህ ሳቢያ ደግሞ ተስፋ ማጣት እና ጭንቀት ውስጥ ይገባሉ፡፡

እንደ Mallah እምነት ለኦናነት የህልውናዊነት ገጽታ ዋና መከሰቻው ይህ አይነቱ ነጻነት ነውና፣ ራሚሱ ፈጣሪን እንደ አጥፊ መንፈስ፣ የጥፋት ሴራ ጠንሳሽ፣ የህላዌን ሰንሰለት ድንገት የሚበጥስ የሞት መልዓክ አድርጎ ይቆጥራል፡፡ ከዚህ ባለፈ ግን የፈጣሪን እና የህይወትን መልካም ትስስር ከቶውንም አያምንም፤ በእርሱ ህላዌ ውስጥ ፈጣሪ የሚባል እና እምነት የሚጥልበት ሠሪ መሪ አምላካዊ ሃይል የለውም፡፡ የገዛ ህላዌውን እሱው እንደሚፈጥረው ያምናልና፤ ዓለማዊ ህይወቱን በሙሉ በራሱ ምሕዋር ውስጥ ይገፋል እንጅ አለኝታ አያስፈልገውም፡፡ ታዲያ ቆም ብሎ በሚያስብ ጊዜ በህይወት ጉዞው ውስጥ መቼ እና ምን አይነት አደጋ እንደሚገጥመው አያውቅም፤ የህይወት አይቀሬ የአደጋ ዕጣ (ሞት) እንዳለ ቢያውቅም እንኳን ከዚህ ዕጣ ፋንታ ማን እንደሚያስጥለው እና በምን አይነት ሁኔታ እንደሚመጣበት ግራ ይጋባዋል፡፡ ተስፋ የሚጥልበት ልዕለ ሃይል የለውምና እራሱው ይጨነቃል፡፡ እርሱ በመረጠው ነጻነት እና ይህ ነጻነቱ በወለደው ጭንቀት መካከል ሆኖ እንደዚህ ሲያስብ የመኖር ትርጉሙ ተጣፍቶበት ባዶነቱ ትዝ ይለዋል፤ እናም ህላዌውን በኦናነት ይፋለማል፡፡

> "ለምን እንደምኖር አላውቅም፡፡ ምን እንደምፈልግ አልውቅም፡፡ በቆራጥነት የምጠጣው እና ጫት የምቅመው የመሞቻ ጊዜዬን ለማፋጠን ይመስለኛል፡፡ ለመስከር የምጠጣው መዝናናቴ መስሎህ ልትቀናብኝ የልብህ ጥርስ የገጠጠ [...] እውነት እውነት እልሃለሁ የምሰራው ስለጠፋኝ ነው፡፡" (አዳም ረታ፣ 2010፤ 170)

ከፍ ሲል እንደተጠቆመው፣ ራሚሱ ሁሉንም ነገር ትቶ ራሱን ከሱስ ጋር አላትሟል፡፡ የአለምን ውስብስብ ጣጣ በመጠጥ ለማምለጥ ይታገላል፤ ለእሱ አምላኩ፣ ተስፋው ይኸው መጠጡ ብቻ ሆኗል፡፡ የራሚሱ መጠጥ እንደ ማንኛውም ሰው የመጠጥ ናፍቆት፣ የቅንጦት፣ የተዝናኖት መጠጥ አይደለም፤ የእሱ መጠጥ ስሜት እና ጥቅም አልባ ደመነፍሳዊነት ነው፡፡ እርሱ እንደሚለው የሚሰራውን ወይም የሚፈልገውን በውል አይወቅ እንጅ ምናልባትም መጠጥ ለእርሱ ማምለጫው፣ መደበቂያው፣ ከሚጠላው ማህበራዊ ሱታፌ መሸሸጊያው አድርጎ መርጦታል፤ ከአምላኩ የተሻለ ተስፋ ጥሎበታል፤ ጊዜያዊ የጭንቀት መፈወሻ መድኃኒት ሆኖታል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ Hong W U (2013) Sartreን ዋቢ በማድረግ፣ በእርግጥ ኦና በሆኑ ሰዎች ህልውና ውስጥ አምላክ የሚባል ሃይል የለም፡፡ ስለዚህ ሰዎች ከአምላክ ጋርም ሆነ ከአምላክ ውጭ ሳይሆን አራሳቸውን ከሌላ ማንኛውም ነገር ጋር በማጣበቅ ከአምላክ ዘንድ ይገኛሉ የሚባሉ ቱሩፋቶችን እና መልካም የሚባሉ እሴቶችን ያጣሉ፤ በዚህ ሳቢያ ደግሞ ለባይታወርነት (Alienation) ይጋለጣሉ በማለት ያስረዳሉ፡፡ በዚህ መሠረት እንደ Sartre እሳቤ ከሆነ ኦናነት ከባይታወርነት ጋር የተገናኘ ብቻም ሳይሆን ለባየታወርነት አንዱ መከሰቻውም ይኸው ኦናነት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ ራሚሱ በሃሳብም ይሁን በአጠቃላይ የህይወት ፍልስፍና ከእሱ ጋር የሚራመድ ሰው ይኖራል ብሎ ስለማያምን ብቸኝነትን የህይወት ምርጫው ካደረገ ውሎ አድሯል፡፡

ቀደም ሲል እንደተነሳው እራሱን ከአምላክ ጋር ብቻ ሳይሆን ከመሰሎቹ (ከሰዎች)ም አርቆ ተክሏል፡፡ እሱ ማንንም ምንንም አይፈልግም፡፡ ምክንያቱም በዚች ምድር ላይ ከእሱ ጋር ማንም ምንም አይገጥምም፡፡ ስለሆነም ሰዎችን የሚጠጋቸው እሱ በሚፈልገው መንገድ ብቻ እንጅ እንደ እርሱ አይነት አሳቤን ስለሚያራምዱ ወይም ደግሞ የህይወት ፍልስፍናው ተጋሪ ስለሆኑ ከቶውንም አይደለም፡፡ ለምሳሌ አሥራትን ይቀርባታል፤ በሴትነቷ፣ ጌርሳን መቅረብ ይፈልግ ነበር፤ ለመቅረብም ሞክሯል (እንዳሰበው ባይሳካለትም)፤ እሷንም በሴትነቷ፣ እነ ገለታን፣ ዘሪሁን እና ባካፋን ይቀርባቸው ነበር፤ ህጻን ስለነበር፡፡ ከዚህ ባለፈ ግን የትኛውም ሰብዓዊ ፍጡር ለእሱ የሚመጥን አልሆነለትምና በመካከሉ መገኘቱን

ይጠላል፡፡ ይህን ባህሪውን በተመለከተ እንዲህ ሲተረክ እናነባለን፤ "በእሱ ፍቺ ሁለት አመታት ካምፓስ እያለ ያጋጠመው የዞረበት ሕዝብ ነው፡፡ '[…] ይሄ አገር አማሃይ ያመልካል፡፡ የአገራችን ፈጣሪ ፀጉሩን እንዳይረዝም እንዳያጥር አድረጎ የሚስተካከል አነብዳጅ ነው፡፡ ከእነዚህ ዜጎች ጋር መኖር እንደመረገም ነው' ይላል፡፡" (አዳም ረታ፣ 2010፤ *16*)

ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ ራሚሱ፣ የአገሩን አስተዳደራዊ ሥርዓት ሳይቀር አብዝቶ ይቃወማል፡፡ በሥራ ሰበብ ሊያገኛቸው ከሚችሉ አካላት አስቀድሞ እራሱን ያሸሻል፡፡ እራሱን በራሱ ፍልስፍና ብቻ አጥሮ ህይወቱን ለብቻው መኖር ይፈልጋል፡፡

> ከሆነ ከምጠላው ዩንቨርሲቲ ካልጠፉ ትምህርት በእንግሊዝኛ ቋንቋ ዲግሪዬን ወስጄ በጥበቡ ያታለልኩት ወይም የመሰጥኩት ሰው የለም፡፡ ምክንያቱም ስራ ሰርቼ አላውቅም፡፡ እንዴት? ለምን? ምን መሆንህ ነው? ቢሉኝ፤ እነዛ ቢረባም ባይረባም መጠየቅ የሚቀላቸው፣ እነዚህ በጀግና እና በፈሪ ሊመድቡኝ ምላሳቸው የተቅለበለበባቸው ወይ እነሱ ቁም ነገረኛ ለመምሰል በአፋቸው የሻፈዱ እላቸዋለሁ፡፡ እኔ የተማርኩት የማንም ፖለቲከኛ መጠቀሚያ ላለመሆን ነው፡፡(አዳም ረታ፣ 2010፤ *171)*

ስለዚህ ሥራም ቢሆን ለእርሱ የገዥ እና የተገዥ፣ የአዛዥ እና የታዛዥ መደባዊ ሥርዓት ነውና እራሱን ከዚያ መንጋ መደብለቅ አይመቸውም፡፡ ይህን መንጋዊ ሥርዓት ይፈራዋል፡፡ እጁን ከዚህ ውስጥ አስገብቶ እንደማነኛውም ሰው በመንጋ መፈረጅ ከቶውንም አይፈልግምና ይሸሸዋል፡፡ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ ይህ የራሚሱ የሥራ ሽሽት፣ አንድም በስራ አጋጣሚ ከሚያገኛቸው ሰዎች ጋር ሊኖር የሚችለውን የጋርዮሽ ሥርዓት እና ማህበራዊ መስተጋብር ፍራቻ፤ አንድም ደግሞ በአስተዳደራዊ ሥርዓቱ ውስጥ በተደጋጋሚ የሚያስተውለውን ተለምዷዊ የሆነ የማስመሰል ፖለቲካዊ የዕውርነት ተክኖ መራር ጥላቻ የወለደው ነው፡፡ የሆነው ሆኖ፣ ከየትኛውም ተለምዷዊ የህልውና ሂደት እራሱን አቅቦ መኖርን መርጧል፡፡

ራሚሱ፣ በተለይም አሁን አሁን በምድር ላይ ያሉ ሥነ ፍጥረታትን ሁሉ ጠልቶ ብቻውን ቀርቷል፡፡ ይህ አይነቱ የሰው ልጅ እና የተፈጥሮ ጅምላዊ የሆነ መራር ጥላቻው ምክንያት ምን እንደሆነ ግን ለእራሱም ግልጽ አይደለም፡፡ ይሁን እንጅ እንደ ነገረህላዌ ልሂቃን እሳቤ ይህ አይነቱ ምክንያት አልባነት እንዲሁም ጭፍን የሆነ የሥነ ፍጥረታት ጥላጫቻ እና ሽሽት ከባዶነት (ኦናነት) የሚመነጭ የተስፋ ቢስነት እና የባይታወርነት ረቂቅ ስሜት

ነው፡፡ "እና ያለ ይሉኝታ ይኸው ልበለው የማልጠላው ነገር የለም፡፡ ይሄ ጥላቻ የሚመጣው ልገልፀው ከሚከብደኝ እውስጤ ካለ ጉድጓድ ውስጥ ነው፡፡ ጉድጓዱ እንዳለ ይታወቀኛል፡፡" (አዳም ረታ፣ 2010፤ 172)

ራሚሱ ገና በልጅነት እና በጎረምሳነት እድሜው በተለይም ከጓደኞች ከእነ ገለታ፣ ባካፋ እና ዘሪሁን ጋር አብሮ እነዳልጨፈረ፣ በቀልዳቸው እንዳልሳቀ፣ በፉጨታቸው እንዳልተመሰጠ፣ በአሽሙራቸው እንዳልፎለለ፣ ብዙ ብዙ የልጅነት ጨዋታዎችን በአብሮነት እነዳላሳለፈ ዛሬ ግን ብቻውን መሆንን አብዝቶ መርጧል፤ የሰው ልጅ ለሚባል ፍጡር ሁሉ ወሰን አልባ ጥላቻ አድሮበታል፡፡ "እንግዲህ ይኼው ምክንያቱን ሳላውቅ ወይ ምክንያቱን እየገመትኩና እያማረርኩ ሰው የተባለ ፍጡር እጠላለሁ፡፡ ይሄ እንደ እኔ በሁለት እግሮቹ ቆሞ የሚሄደውን፣ በእግዜር አምሳል ተሰራሁ ብሎ ጉራ የሚቸረችረውን ማለቴ ነው፡፡" (አዳም ረታ፣ 2010፤ 172-173)

የራሚሱ ምክንያት አልባ የጥላቻ ጥፌ የሚያርፈው በሰው ልጅ ላይ ብቻ አይደለም፤ ቀደም ብየ እንደጠቆምኩት በሌሎችም ሥነፍጥረታት ሁሉ ጭምር እንጂ፡፡ ይህ ጥላቻው እና ሽሽቱ በአንድ አሊያም በተወሰኑ ነገሮች ላይ ብቻም የተገደበ አይደለም ፍጥረታትን ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ያዳርሳል፡፡

> *የማልጠላው ነገር የለም፡ የሚፈስ ወንዝ በሉት፣ የቆመ ሃይቅ፡፡ አንዴ እንኳን አልጮኽብኝም ግን ያ እዛ ጋ ያለው ጎረቤቴ ያሳደገው ውሻ ያስጠላኛል፡፡ ተራራው እና ሜዳው ደረቁ ይባል ለምለሙ ያስጠሉኛል፡፡ አረ ተራራው ምን ልሁን ብሎ አበጠ? መስኩስ ለምን ጠፍጣፋ ሆነ? የሚነፍሰው ነፋስ ያስጠላኛል፣ ምን አንቀለቀለው? ምን አንከወከወው?* [...] *ይሄን ሁሉ የምጠላውን ሰብስቦ ሊይዝ የሚችል ገደል አለ? እነዚህን ሁሉ ሰብስቦ ወደ ገደል የሚገፋልኝ ታሪክ አለ? እኔንም ደብሎ ወደዚያ ወደዚያ የሚወስድ? ከእኔ ጥላቻ የሚያመልጠው ምንድን ነው? ማነውስ? ወይስ እንደአንዳንድ ብልጣብልጥ ነን ባዮች ጥላቻዬን ሁሉ አቅፎ የሚይዝልኝ የሆነ ፍልስፍና ላበጅ?*(አዳም ረታ፣ 2010፤ *173-175)*

ራሚሱ፣ ከዚህ ሁሉ ፍጡር ከራሱም ጨምሮ እጅግ ልዩ ስፍራ ይሰጣት የነበረችውን፣ በዓለም ላይ ካሉ ፍጥረታት ሁሉ ልዩ የሆነች የእውነት ልዕለ ሰብዕ ናት ያለላትን፣ ከሰማይ በታች ያለች ልዩ ፍጡር ብሎ ያመለካትን፣ ይህን ይህን መሰል ታላቅ ከፍታ የሰጣትን እና ከሁሉ ነገር በተለየ ከወጣትነት እድሜው ጀምሮ የወደዳትን፣ የጥላቻውን ጽልመት የምታበራውን ብቸኛዋን ዓለሙን ጌርሳሞትን ሳይቀር ምትሃታዊ በነበሩት ከናፍሮቿ መበላሸት ምክንያት ጠላት፡፡ ለጌርሳ ሲሆን የጥላቻውም ምክንያት ተገለጠለት፡፡ የሆነ

ደማቅ አበባ በሰው ልጅ ላይ የበቀለ ያክል ይገረምባቸው፤ ይደነቅባቸው የነበሩ፣ እሱን እንኳን ሳይቀር ያንበረከኩ የውበት አርበኛ ከናፍሮቿ ሲቆሳሰሉ ብቸኛ ጣዖቱ እንዳልነበረች እንደ ሌላው ፍጡር ሁሉ ሸሻት፤ ሌላውን ሁሉ ባየበት ዐይኑ ዐያት፡፡ ያን መሰል ይጓጓለት የነበረ ውበቷን በገዛ እጇ ማበላሸቷን ሲታዘብ ብቸኛ የእውነት ዓለሙን ባዶ እንዳደረገችበት ጠላቱ ቆጠራት፡፡ የጥላቻው እርቀት እና ጥልቀት ማረጋገጫው ሆነች፡፡ አሁን በህይወቱ ውስጥ አንዳችም የቀረው ነገር የለም፡፡ ሁሉም ነገር ባዶ ሆኖ እሱንም ኦና አስቀርቶታል፡፡ "ጌርሳ ብረታብረቱን አስገብታ የሆነች ፋብሪካ የመሰለችው በረሷ ፈቃድ ነው፡፡ ተፈጥሮ ያለሳንክ ሰራቻት እሷ ሳንክ ሰራች፡፡ **እፏ** ውስጥ እንከን ገነባች፡፡ ከዛን ቀን በኋላ ጌርሳሞት ጌርሳ አይደለችም፡፡" (አዳም ረታ፣ 2010፤ *188)*

## 3.3. ሁኔታዊነት

ከንዑስ ገፀ ባህርያት ውስጥ የጌርሳሞት አባት አቶ ኮላሴ ባሪያው እና ከላይ በሁለቱም ክፍሎች ውስጥ የተነሳው ዋና ገፀ ባህርይ ራሚስ ለዚህ ክፍል አይነተኛ ማሳያዎች ተደርገው ተመርጠዋል፡፡ አቶ ኮላሴ ዝርያቸው ከዝንጀሮ የሆኑ ሰው ናቸው፡፡ የእርሳቸው ዝንጀሮነት ከሳይንሳዊው የሰው ዘር አመጣጥም በላይ በእውኑ ከዝንጀሮ አብራክ የወጡ ገፀ ባህርይ ናቸው፡፡ ገና ከህጻንነት (ከጨቅላነት) ዕድሜያቸው አንስቶ በአሳዳጊዎቻቸው በእነአቶ ባሪያው ስላደጉ የሰውነት ባህሪን እና ባህልን ጨምረው ወርሰዋል፡፡ በዚህም መሠረት ሚስት አግብተው፣ ልጅ ወልደው እና በሹፍርና ሥራ ተሰማርተው ህላዌያቸውን ይገፋሉ፡፡ በመጨረሻም ወደ ትውልድ ዘመዶቻቸው ይመለሳሉ፡፡ ከዚህ ባለፈ ደግሞ፣ እንደ ነገረህላዌያን እምነት ማነኛውም ሰው ምንም ያህል ነጻ ህላዌ ቢኖረው ከአካባቢው ባህል፣ ሥርዓት፣ እምነት ወዘተ ፍጹም ውጭ ሊሆን አይችልም፤ ይልቁም ከአካባቢው የተቀዳ ኑባሬ ይኖረዋል እንጂ፡፡ ለዚህ ማሳያነት ደግሞ ራሚሱ ተመርጧል፡፡ እንግዲህ እነዚህ ሁሉ ጉዳዮች በዚህ ክፍል ውስጥ ከዚህ ቀጥሎ በስፋት ቀርበዋል፡፡

ከሁሉ በፊት፣ ሁኔታዊነት ከነገረህላዌያን እሳቤ አንጻር ሲታይ በመስጠት እና በመቀበል ላይ የተመሰረተ ስብጥር ህልውናን መገንባት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይኸውም የገዛ ራስ ህላዌን እና ከሌሎች ቅድመሁኔታዎች የተቀዳ ኑረትን የሚመለከት ነው፡፡ በሕፍ ረጅም ልቦለድ ውስጥ የጌርሳሞትን አባት አቶ ኮላሴን ለዚሁ ሁነኔታዊነት አይነተኛ ናሙና ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ከሁሉ አስቀድሞ አቶ ኮላሴ ስር መሠረቱ የዝንጀሮ ዝርያ ያለው የሚባል

ብቻ ሳይሆን በቀጥታ ከዝንጀሮ የተወለደ፣ የዝንጀሮ ልጅ እና በሰዎች ፍቅር እና እንክብካቤ (በጉዲፈቻ?) ያደገ ሰውም ዝንጀሮም የሆነ ተዓምራዊ ገፀ በህሪ ነው፡፡ ኮላሴ በሖፍ ውስጥ ሰው አይደለም፤ ዝንጀሮ አይደለም፡፡ ኮላሴ ሰውም ዝንጀሮም ነው፡፡ ማለት በተፈጥሮው ዝንጀሮ ሆኖ ከዝንጀሮ የተወለደ ነገር ግን በሁኔታዎች ምክንያት ሰው የሆነ የድቅል ማንነት፣ የውህድ ባህርያት ባለቤት ለዩ ፈጡር ነው፡፡

> … ሁለቱም እግሮቹ ጥልቀት የሌለው ወንዙ ውሃ ውስጥ ያረፉ፣ **ሁለመናው ራቁቱን የሆነ**፣ በብርድ የሚንዘፈዘፍ አንድ ሞሳ ወድቆ አዩ፡፡ […] አቶ ባሪያው ልብ ገዝተው ወደ ልጁ ሲጠጉ ብዙ የጉዳት ምልክት እንደሌለበት አዩ፡ አይኖቹ ይቁለጨለጫሉ፣ ከፊቱ በስተቀር ገላው በፍዝ ቡናማ ፀጉር ተሸፍኗል፣ […] በደንብ ሊያዩት አቶ ባሪያው ወደፊቱ ሲጠጉ፣ እንዲያቅፉት አይነት በስስ ፀጉር የተሸፈኑ ክንዶቹን ወደእሳቸው ዘረጋ፡፡ አቶ ባሪያው ዙሪያ ገባቸውን ሰልለው ከውሃው ሸሸት አድርገው በጋቢያቸው ጠቀለሉትና 'ምናልባት ሰው ይኖረው ይሆን?' በማለት ወንዙ ዳር ደረቅ ጥቁር ድንጋይ ለይ እየበረዳቸው አቅፈውት ተቀመጡ፡፡ […] አቶ ባሪያው ማንም እንዳልመጣ ሲረዱ ልጁን በጋቢያቸው እንደጠቀለሉ እየተገላመጡ እያዩ ቤታቸው ገቡ፡፡(አዳም ረታ፣ 2010፤ *24)*

እንግዲህ የአቶ ኮላሴ ሰዋዊ ህልውና ከዚህ ይጀምራል፡፡ አቶ ኮላሴ ከቀድሞ ዝርያዎቹ ከዝንጀሮዎች ተለይቶ በአቶ ባሪያው እጅ ስር እንዲያድግ ያደረገውን አጋጣሚ የልቦለዱ ታሪክ እንዲህ ከትቦ ይዟል፡፡ አቶ ኮላሴ ገና በጨቅላነቱ በአንድ ገደላማ ጫካ ውስጥ እንደ ሌሎቹ ዝንጀሮዎች ሁሉ ከዛፍ ወደ ዛፍ እየዘለለ እና ቅጠሉን  እየበላ ህልውናውን የሚገፋ የዱር የእንስሳ ነበር፡፡ ታዲያ ከዕለታት በአንዱ ቀን ከአንዲት እንስት ዝንጀሮ ተጠግቶ በመገኘቱ በትልቅ ገመሬ ዝንጀሮ ተደብድቦ ቆሞበት ከነበረ ዛፍ **ስር ወደሚገኝ ዥረታም ገደል ተወርውሮ** እንዲወድቅ ተደረገ፡፡ በዚህ ጊዜ አሳዳጊው የሆኑት እና በመሃንነት ሳቢያ የልጅ ስስት እድሜያቸውን ሁሉ ያሰቃያቸው አቶ ባሪያው በዙሪያው ባሉት ሌሎች ዝንጀሮዎች ጫጫታ ምክንያት ባጋጣሚ ተጠርተው በመሄድ ከላይ በቀጥታ እንደጠቀስኩት ለሌሎች ሰዎች አንዲት ዘመዳቸው ወልዳ እንደጣለችባቸው በማስወራት **ከተጣለበት ገደል** አንስተው ወስደው ክርሥትና ካስነሱት በኋላ "አሳዳጊህ ነን ሳይሉ" እንደ ጥሩ ወላጅ ሆነው በታላቅ ፍቅር እና እንክብካቤ አሳደጉት፡፡ በኋላም አሥራ ስምንት አመቱ ላይ እነዚሁ አባቱ እና  እናቱ ቤታቸውን አውርሰው በሞት ተለዩት፡፡ እርሱም በስማቸው እየተጠራ ቤቱን አከራይቶ እና የመንጃ ፈቃዱን አውጥቶ ሰዋዊ ህለውናውን መግፋት ጀመረ፡፡

እንግዲህ ይህን የአቶ ኮላሴን የሰውነት መነሻ ታሪክ ላዕላይ ጎኑን የተመለከትን እደሆነ፣ በመጀመሪያ ደርጃ እንደየትኛውም የሰው ልጅማሰብ (ማገናዘብ) የማይችል እናከእንስሳት

ወገን የነበረ ፍጡር ነው፡፡ ይሁን እንጅ ከሰዎች ጋር ከተቀላቀለበት ጊዜ ጀምሮ ሰዋዊ ሁነቶችን መላመድ ብሎም የተለያዩ ሰዋዊ ተግባራትን መፈጸም ጀምሯል፡፡ ኮላሴን በህይወት ዘመኑ ውስጥ የእንስሳት ዘር ነህ የሚለው ማንም አልነበረም፤ ምክንያቱ ደግሞ ሙሉ ኑባሬው ሠዋዊ ነውና፡፡ ይህ ሰዋዊ ህልውናው የተቀዳው ደግሞ ካደገባቸው ቤተሰቦቹ ከእነ አቶ ባሪያው እና ምናልባትም በእነርሱ አካባቢ ካለው ማህበረሰብ ውስጥ እንጅ ሲፈጠር አብሮት የተፈጠረ ከቶውንም አይደለም፡፡ ይኸውም ከነገረህላዌ እሳቤ አንጻር ሲታይ ማንኛውም የሰው ልጅ የሚፈጠረው ወደፊት የሚኖረውን ህልውና ይዞ ሳይሆን ባዶውን ነው፤ ዓለማዊ ህልውናውን የሚፈጥረው እራሱ ግለሰቡ ወደምድር ከተቀላቀለ በኋላ ነው፡፡ ይህንኑ መንደርደሪያ ጽንሰሃሳብ ይዘን ወደታሪኩ ታህታይ (ምስጢራዊ) ጉዳይ ስናመራ ደግሞ አቶ ኮላሴ የተወረወረው ከዛፍ ወደ ገደል ብቻ አይደለም፤ የተወረወረው ሰው ካለመሆን ሰው ወደመሆን፣ ከተፈጥሮ ወደ ዓለም ህላዌ ነው፡፡ በልቦለዱ ውስጥ ከዛፍ ወደ ገደል እንደተወረወረ የተገለጸውም ይህንኑ ህልውናዊ መወርወርን ለማጠየቅ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም የዝንጀሮ ኑባሬ ሙሉ በሙሉ በዛፍ ቅርንጫፍ ላይ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን፣ በምድርም ጭምር ሆኖ ሳለ፤ የክስተቱ (Facticity) መነሻ የሚጀምረው ደግሞ ከዛፍ ቅርንጫፍ ላይ ነው፡፡ ስለሆነም ካልጠፋ መልክዓ ምድር ከላይ (ዛፍ) ወደ ታች (ገደል) እንደተጣለ ተደርጎ በመገለጹ **ዛፉ** ሰማያዊ ተፈጥሮን፣ **ገደሉ** ደግሞ ዓለምን ወይም ሥነ ፍጥረትን መወከሉን እንድንገነዘብ ያደርገናል፡፡

እንደ Sartre እምነት ከሆነ የሰውልጅ ወደ ዓለም የተወረወረ (Man is thrown to the world) ፍጡር ነው፡፡ ኮለሴ ወደ ሰብዓዊ ዓለም ባዶውን የተጣለ እና ሰብዓዊና እንስሳዊ ህልውናን አቀናጅቶ የያዘ ባለ ውህድ ህልውና ነው፡፡ "**ሁለመናው ራቁቱን የሆነ**" በሚል ከታሪኩም ላይ በግልጽ መስፈሩም ያለምክንያት አይደለም፤ ይህንኑ ባዶ ህልውና ለማስተማሰል የቀረበ እንጂ፡፡ አዎ ኮላሴ የተጣለው ራቁቱን (ባዶውን) ነበር፡፡ ሰብዓዊ ካልነበረው የዝንጀሮዎች ህላዌ ወደ አዲስ ማንነት፣ ወደ አዲስ የተቀዳ ህይወት መጥቷልና አሁን ኮለሴ ሰው እንጅ በፍጹም ዝንጀሮ አይደለም፡፡ ሰውነትን (ሰው መሆንን)ም ይዞት አልተወለደም፤ ከተወለደ በኋላ አገኘው እንጂ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ ይህ ታሪክ የሰውን ልጅ ሳይንሳዊ አመጣጥ (ሥነ ህይወታዊ ልዋጤ)ም በግልጽ ያስገነዝበናል፡፡ የሰው ልጅ ሥነ ህይወታዊ ለውጥ ደግሞ በራሱ ሁኔታዊ ነው፡፡ እንደ Hegel እምነት ማንኛውም ነጻነት ያለው ሰው እንኳን ቢሆን ህይወቱ የሚቀዳው ከአንድ የተወሰነ አውድ ውስጥ ነው፤

ኑባሬውም አውዳዊ ነውና፡፡ በሰው ልጅ ሥነ ህይወታዊ ለውጥ ውስጥ ደግሞ ማህበራዊነት አንዱ አካል ነውና፤ በማህበራዊነት ውስጥም እንደዚሁ የጋራ የሆኑ በርካታ ጉዳዮች መኖራቸው የሚያጠያይቅ አይደለም፡፡ እንደዚህ አይነቶቹ ጉዳዮች ናቸው እንግዲህ የሰው ልጆችን ሁኔታዊ የሚያሰኟቸው፡፡

ከዚህ በላይ ካየነው ታሪክ በኋላ አቶ ኮላሴ እንደማንኛውም ሰብዓዊ ፍጡር የተለያዩ ሰብዓዊ ተግባራትን ሲፈጽም እናስተውላለን፡፡ ይኸውም በሾፌርነት ሙያ ተሰማርቶ ህልውናውን ከማስቀጠልም ባለፈ፣ ሚስት አግብቶ ጌርሳሞትን የሚያክል የማራኪ ከናፍር ባለቤት የሆነች እና እንደዐይኑ የሚሳሳላት ልጅ እንደወለደ ልቦለዱ ያስነብበናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የሚወደውን መጽሔት የሚያነብ እና እንደማንኛውም ሰው ስታዲዮም ገብቶ ኳስ ጨዋታ ማየት የሚወድ እና የሚያዘወትር ገፀ ባህሪ ነው፡፡ "አባቴ ስታድዮም መሄድ፣ ብዙ ፍራፍሬ መብላት፣ ብዙ ሰላጣ ያውም ጥሬውን መቁረጠም (…) አንድ ብቸኛ ናሽናል ጂኦግራፊክ መጽሔት (…) ማንበብ እና በተለይ እንጀራ በኅመን ወጥ መብላት ይወድ ነበር፡፡" (አዳም ረታ፣ 2010፤ *28-29)፤* እንደ Heidegger ሃሳብ ከሆነ እያንድንዱ የህይወታችን እንቅስቃሴ ከሌሎች በዙሪያችን ካሉ አካላት ህልውና የተቀዳች ስትሆን፣ በአንጻሩ የሌሎች ሰዎች ህልውናም እንዲሁ ስለእኛ የሚያንጸባርቀው ነገር አለ፡፡ ኮላሴም እነዚህን ሁሉ ሁነቶች በዙሪያው ካሉት አካላት የቀሰማቸው እንደሆኑ እንረዳለን፡፡ እነዚህ ተግባራት ኮላሴ በሰብዓዊ ህልውናው ውስጥ ለብዙ ጊዜያት ይፈጽማቸው እና ይታወቅባቸው የነበሩ ጉደዮች ናቸው፡፡

ኮላሴ በሰብዓዊ ህልውናው ውስጥ የጨቅላነቱ እንስሳዊ ኑባሬ ሌሊት በህልሙ፣ ቀን ደግሞ በደመነፍሱ በተደጋጋሚ እየተመላለሰ እና እረፍት እየነሳው መጣ፡፡ ይህ ሁነት በተለይም ደግሞ በህልሙ ከመደጋገሙ የተነሳ እሱ እራሱ "የገደል ህልም" የሚል ስያሜ እንደሰጠው ታሪኩ ይነግረናል፡፡ በኋላም ይህንኑ የተለመደ ህልሙን እንዳየ በአንድ ጠዋት ከመኖሪያ ቤቱ ወጥቶ ድጋሚ ሳይመለስ ቀርቷል፡፡ በእግር በፈረስ የተደረገው የሚስቱ የመግደላዊት እና የፖሊሶቹ ፍለጋም ከሚነዳው መኪና እና ከተቀዳደዱት አልባሳቶቹ ውጭ ኮላሴን በአካል ማግኘት ከንቱ ህልም ሆኖባቸው እንደቀረ እዚሁ ታሪክ ውስጥ እናነባለን፡፡ ኮላሴ ቤቱን፣ ቤተሰቦቹን፣ ያደገበትን አካባቢ እና ሰብዓዊ አውድ ትቶ ቀድሞ የዘር ሃረጉ የተቀዳባቸው ዝንጀሮዎች ወደሚኖሩበትጫካ ተመለሷል፡፡ አሁን ደግሞ ኮላሴ ሰው ሳይሆን እንደጨቅላነቱ ተመልሶ ዝንጀሮ ሆኗል፡፡

እነግዲህ ይህ የኮላሴ አጠቃላይ ሁኔታዊ ህልውና፣ የሰው ልጅ ሁኔታ በተፈጥሮው የሁለት ውስብስብ ቅንጣቶች ማለትም የትክክለኛ ተፈጥሮ እና የተሻሻለ ወይም ደግሞ የተሰጠው (ከፈጣሪው?) እና የተቀበለው ማንነቶች ውህድ ነው የሚለውን የ(Flynn; 2006)ን ሃሳብ በድምቀት ያሳያል፡፡ እንደ Flynn እምነት አንድ ሰው በዘር፣ በማህበራዊ ማንነት፣ በቀደመ ምርጫ እና በመሳሰሉት ሁኔታዎች ውስጥ እራሱን በመዘፈቅ ቅይጥ የሆነ ህልውናን ይመሰርታልና፤ የኮላሴ ህልውናም እንዲሁ ከእነዚህ ሁሉ ሁነቶች በአንዱ አሊያም በሁሉም ሁኔታዎች ውስጥ እራሱን በመንከር ከሰውነት እና ከእንስሳነት የተዳቀለ ቅይጥ ህልውና የሚመሰርት ገፀባህሪ ሆኖ እናስተውላለን፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በሕፍ ልቦለድ ውስጥ የምናገኘው ሌላው ሁኔታዊ ገፀባህሪ ደገግሞ ራሚሱ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ራሚሱ፣ ወሰን የለሽ ነጻነት ያለው ገፀ ሰብ መሆኑን ከላይ በተደጋጋሚ አንስቻለሁ፡፡ ነገር ግን ነገረህላዌያን እንደሚሉት የትኛው በነጻነት የሚኖር ሰው ምንም ያህል ነጻነት ቢኖረው ሙሉ በሙሉ ህልውናው ከሌሎች ሰዎች የተለየ ወይም ደግሞ ከሌሎች ሰዎች የአኗኗር አሊያም የህልውና ዘይቤ ተጽዕኖ ፈጽሞ የጸዳ አይደለምና፤ ራሚሱም ከሌሎች ማህበረሰቦች የሚጋራቸው ጉዳዮች ጥቂት የሚባሉ አይደሉም፡፡ በብዙ ጉዳዮች አማካኝነት ከማህበራዊነት ፈጽሞ ማምለጥ እንደማይቻልም በእራሱ አንደበት እንዲህ ይተርካል፡፡

> የግል ልምድን ወደ ማህበራዊ ውይይት ማምጣት የናሙና ህግ ማክበር ብቻ አይደለም፡፡ አብረን እንዳለን ማሳያም ነው፡፡ በዛ በኩል በዛች በቅሎ ደረትዎን ነፍተው ቢያልፉ እልዎታለሁ ያቺ የህያ ልጅ የጠጣችው ውሃ የወንዜ ነው፡፡ የጋጠችው ከፍየሎቸ መንጋ ተጋፍታ ነው፡፡ ፋንድያዋን እሳት ለኩሸበታለሁ፡፡ ይሄ አሁን የማወራው ወሬ ደግሞ ወደዱም ጠሉም ሳሩን፣ እኔን፣ ፍየሌን፣ እስዎን፣ በቅሎዋን፣ አባቷን ፈረስን ያያያዘን ናጥራን ነው፡፡ ሙልጭ አድርገን ካልዋሸን በቀር ከዚህ ጉንጉን አናመልጥም፡፡ ግን ሞላጫ በዛ፡፡ (አዳም ረታ፣ 2010፤ 194)

ከዚህ በላይ ከተቀነጨበው የልቦለዱ ታሪክ የትኛውም ሰው ልጅ አብሮ እስከኖረ ጊዜ ድረስ ህልውናው ሰንሰለታዊ እንደሆነ በግልጽ እንረዳለን፡፡ እናም ራሚሱ ህልውናውን በነጻነት የሚመራ እና በምንም ቅድመ ሁኔታ የሚገደብ ባይሆንም ኑባሬው ከሌሎች ሰዎች ጋር በአብሮነት ነውና ከሌሎች ጋር የሚጋራው የህላዌ ልምድ እንዳለ እንታዘባለን፡፡ በየትኛውም ሰው ህላዌ ውስጥ የሚከወኑ ቋሚ ተግባራትን አብሮ ይከውናል፡፡ ለምሳሌ ሌሎች የሚመገቡት ምግቡ ነው፤ የሚጠጡት መጠጡ ነው፤ የሚኖሩበት መኖሪያው ነው፤ የሚለብሱት ልብሱ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ደግሞ እሱ የሚለ'የው በአስተሳሰቡ፣ በፍልስፍናው

ወይም ደግሞ ለህይወት በሚሰጠው ትርጓሜ ብቻ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ስለሆነም እነዚህን የሌሎች ማህበረሰቦች የህልውና ልማዶች በሚኖርበት ማህበረሰብ ሥርዓት መሠረት ይፈጽማል፤ ኑባሬውም በእነዚህ ሁነቶች መወሰኑ አይቀርም፡፡ “ግብዳ ግቢ፣ የራሴው ምኝታ ክፍል፣ እናት እና አባቴ የሚሰፍሩልኝ ቀለብ፣ አፌ ውስጥ ደሞ የቁሞ ቀር ሴት የጡት ፍንጭ እንደ አብሲት አረፋ እየፈነዳ፡፡ ጎዳናዬ ከዚህ አይወጣም፡፡” (አዳም ረታ፣ 2010፤ 204)ራሚሱ፣ ምንም እንኳን ከሌሎች በዙሪያው ካሉ ሰዎች በተለየ የራሱን ህላዌ በራሱ የፈጠረ ቢሆንም የኋላ ኋላ ግን ከእነርሱ ተጽዕኖ ሙሉ በሙሉ ሲያመልጥ አይስተዋልም፡፡ ልክ እንደሌሎቹ በዙሪያው እንዳሉ “ደደቦች” እንዳላቸው ማህበረሰቦች ሁሉ እርሱም ለሌሎች ደስታ ሲል ብቻ ማስመሰሉ ፈፅሞ አልቀረም፤ የውሸት ማንነት መገንባቱ፡፡

ራሚሱ ከአሥራት ጋር የመሰረተው የፍቅር ጓደኝነት ለእርሷ ሲል እንጅ እርሱ ወዶ እና ፈቅዶ እንደዚሁም አምኖበት የገባበት ጉዳይ ከቶውንም አይደለም፡፡ እንዲያውም በፍቅር ሰበብ መጠቀሚያ ባሪያዋ (መሳሪያዋ) ሆኗል፡፡ ታዲያ በዚህ መሠረት የሌሎችን ማስመሰል አጥብቆ የሚያማርረው ራሚሱ ራሱም አስመሳይ ሆኗል ማለት ይቻላል፡፡ ይህንን አስመሳይነት ደግሞ ምናልባትም በዙሪያው ካሉት እና ቀድሞ ሲታዘባቸው ከነበሩት ሰዎች የወረሰው ነው፡፡ “የቀረችኝ ይህቺ ካንጀቴ የማላፈቅራት ሴትዮ ናት፡፡ “[...] የቀረኝ የማላፈቅረውን የማልወደውን ማስደሰት ነው፡፡” (አዳም ረታ፣ 2010፤ *204)*

እንግዲህ ራሚሱ ምንም ያህል ነጻ ቢሆንም በህይወቱ ውስጥ በትንሹም ቢሆን አውቆም ይሁን ሳያውቅ የሌሎች ሰዎች ሱታፌ መኖሩን መገንዘብ ይቻላል፡፡ አሥራት የገቢ ምንጩ፣ የሥራ ዕድሉ ናትና ሳይወድ በግድ እሷን ማስደሰት የዘወትር ተግባሩ ሆኗል፡፡ ይህን ሳያደርግ ቢቀር ግን ያለምንም ነገር እንደሚቀር ያውቀዋልና አስመሳይነቱን እያወቀ ያስመስላል፡፡ “ሲመስለኝ ለአሥራት ምናልባት፣ ከምናልባትም በላይድብርት መፈወሻ መድሐኒቷ ነኝ፡፡ ፕሮዛክዋ ነኝ፡፡ አንዳንዴም የማስታወቂያ ሰሌዳ የሆንኩ ይመስለኛል፡፡ [...] የእሷን ዳቦ የመሸሸ ነገር ሰፍቶ የአለምን ዳቦ መሸሸ እንዳይሆንብኝ ፈራሁ፡፡ የአሥራት መሳሪያ ነኝ፡፡ እኔም አስመስላለሁ፡፡” (አዳም ረታ፣ 2010፤ *165-166)* ከዚህ አንጻር ደግሞ ይህ ገፀ ባህሪ (ራሚሱ) ነጻ ብቻ ሳይሆን ሁኔታዊም ጭምር ነው ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡

## 3.4. የርእይ መነጠቅ

በሐፍ ረጅም ልቦለድ ውስጥ ያሉ ገፀ ባህርያት ከሞላጎደል በተለያየ መጠን የርእይ መነጠቅ ሰለባዎች ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ይኸው የርእይ መነጠቅ ደግሞ በዋና ገፀ ባህርያት ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሳይሆን የልቦለዱን ንዑሳን ገፀ ባህርያት ሁሉ የሚያካልል ነው ማለት ይቻላል፡፡ በዚህ መሠረት በዚህ ክፍል ውስጥ አምስቱም ዋና ገፀ ባህርያት ማለትም፤ ጌርሳሞት፣ ገለታ፣ ዘሪሁን፣ ባካፋ እና ራሚሱ ለጭብጡ መተርጎሚያነት ተመርጠዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ከበርካታ ንዑሳን ገፀ ባህርያት መካከል ቢያንስ ከዋናዎቹ ጋር ቅርብ ዝምድና ያላቸው የጌርሳሞት እናት መግደላዊት፣ የራሚሱ እናት ወ/ሮ መቅረዝ እንዲሁም የገለታ እናት ወ/ሮ ፎርቱና እንዳስፈላጊነቱ እየተጠሩ እንዲህ ሰፊ ትንታኔ ተደርጎባቸዋል፡፡

> […] በላይኛው ከንፈሩ የላይ ከንፈሯን ሊነካት በከፊል ድፍረት ሲሳብ ተረከዞቿ መሬት ለቀቁ፡፡ ለመብረር እንደፈለገች ሁሉ ተንጠራርታ ቀረበችው፡፡ ዳቦዋ እንደ አቃቂ መፍሰስ ጀምራለች፡፡ […] በዚህ ስሙት ባህር እንዳየች ……ያ የማትዋኝበትን፡፡ ስሙቱ ምድራዊ አልነበረም፡፡ የገለታን ስም ከግስ ጋር ልትጠራው ትፈልጋለች፡፡ ቢቁነጠነጥም አፏ አንዲት ሆሄ ሳይወጣው ቃቅቶ ቀረ፡፡ […] ከመሀል ከግንቡ አጥር ወዲያ አነፍናፊ እናቷ ጠራቻት፡፡ […]ገለታ ቀና አድርጎ ወደ አፉ ሊያቀርባት ሲል ከእጁ ላይ ፊቷ እንደተነነ ሁሉ ጠፋ፡፡ […] ገለታ ቆም ብሎ ሁኔታዋን ትንሽ ታዝቦ አንገቱን እንደሰበረ ከንፈሮቹን እየላሰ ወደ ደብዛዛው ጨለማ በቀስታ ሲራመድ […] ከእሷ እየሸሸ የሚሄደውን የእግሩን እና መሳም ያልደረሰውን የትንፋሹን ዳና በሃዘን ትዝታ እያዳመጠች ያን አስቀያሚ ቀዝቃዛ የብረት በር አንኳኳች፡፡(አዳም ረታ፣ 2010፤ 75-76)

እንግዲህ የእነዚህ የሁለቱ የመዋደድ ጥመኞች፣ የከንቱ ፍቅር ናፋቂዎች ርእይ መነጠቅ የሚጀምረው ከዚህ ጀምሮ ነው፡፡ ከአራቱ ጓደኛሞች ከባካፋ፣ ከዘሪሁን፣ ከራሚሱ እና ከገለታ መካከል ጌርሳሞት፣ ገና ስታየው ልቧ በተለየ ይርድለት፣ ሰውነቷ እንደ ተዓምራዊ ኪነተኛ ይንቀጠቀጥለት፣ የስሜት ህዋሷ ሁሉ ይሳሳለት የነበረውን ገለታን፤ ስለፍቅር ማሰብ ከጀመረች ጊዜ አንስቶ ስትመኘው የነበረውን ፍቅሯን፣ በእዝነ ልቦናዋ ወይም በአይነ ህሊናዋ ከማየት እና ከመመኘት ተላቃ አሊያም ደግሞ በቃላት፣ በሐረጋት እና በዓረፍተ ነገሮች ዘርዝራ ከመንገርም በላይ በከናፍራቸው ንክኪ ልታሳየው፣ ለከት በሌለው መሳሚ የስሜቷን ጥልቀት ልታረጋግጥለት፣ የልጅነት ድንበርን መራመዷን ለመጀመሪያ ጊዜ ልትገልጥለት ጫፍ በደረሰችበት ቅጽበት በእናቷ ድንገቴ መብረቃዊ ጥሪ፣ በአባቷ ሃይለኛ የማስፈራሪያ ትውስታ አማካኝነት በሰከንዶች ሽርፍራፊ ውስጥ ከንፈሯ ከከንፈሩ ሳይደርስ፣

ሁለቱም ለመገናኘት በስስት በመሳሳብ ላይ ባሉበት አፍታ ሳይገናኙ፣ ሳይነካኩ ለዚያች ቅጽበት ብቻ ሳይሆን ለዘለዓለሙ ተፋቱ፡፡ ሁለቱም ደርሶ፣ ሆኖ ማየት የናፈቁትን ቀን፣ የቋመጡለትን የስሜት መግነጢሳዊ መዳረሻ በአይን እርግብግቦሽ ፍጥነት ለቀናት፣ ለሳምንታት፣ ለወራት፣ ለዓመታት ብቻም ሳይሆን እስከ መጨረሻዋ የእስትንፋሳቸው ጠብታ ድረስ እንዳይገናኙ ተፈረደባቸው፤ ፍርዳቸውንም ሳይወዱ በግድ እንዲቀበሉ ተገደዱ፡፡ ይህ በብዙ የስሜት መሳሳብ፣ በአድካሚ እና አስፈሪ የአቀራረብ ስልት፣ በታላቅ የስሜት ስካር የታጀበው ቴያትር መድረክ ላይ ሳይታይ እንደታሰበ ብቻ ቀረ፡፡ ይኸውም የህልም ትርኢት እንጅ የእውን አልነበረምና ለአንድ ቀን እንኳን ሳይደገም ከነአካቴው ዳግም ላይመለስ ለመጨረሻ ጊዜ ከሠመ፡፡ እንደ ነገረህላዌ ልሂቃን እምነት ይህ አይነቱ አሳዶ የያዙትን፣ ፈልጎ ያገኙትን፣ የተመኙትን፣ ያለሙትን ወዘተ ሁሉ በአንዳች ምክንያት ድንገት ከእጅ መመንተፍ፣ ካጠገብ ማጣት፣ የምኞት ከንቱ መቅረት፣ የህልም ቅዠት መሆን የሰው ልጆችን የርእይ መነጠቅ ያጎላዋል፡፡

እንደ Maxwell (2014) ሃሳብ፣ ሰዎች የህላዌ መሠረታዊ ፍላጎቶቻቸውን ለማረጋገጥ ወይም ደግሞ የተሻለ እና ውጤታማ ለማድረግ በወቅቱ ካሉበት ቦታ የተሻለ እና ውጤታማ ያደርገኛል ብለው ወዳሰቡት ቦታ በመሰደድ በቦታ እና በጊዜ ልዩነት የተለየ ርእዮትን ሰንቀው ያሳድዳሉ፤ ይፈልጋሉ፡፡ በዚሁ መሠረት ገለታም ከሚኖርበት አካባቢ አዲስ አበባ "ታቦት ማደሪያ" አገር ለቆ "መገለማመጥ፣ መጠራጠር እና መናናቅ ባለበት ቦታ መኖር አይመቸኝም" የሚለውን ብሂሉን እውን አደረገው፤ ለመጀመሪያም መጨረሻም ጊዜ ወደ ውጭ ወጣ፤ የትውልድ ሰፈሩን፣ አካባቢውን፣ አገሩን ጥሎ ተሰደደ፤ አድራሻውንም በዚያው አጠፋ፡፡ በዚህ ጊዜ የንጋት ወጋገኗን ብቻ ያሳየቻት የጌርሳሞት ጀምበር ሙሉ ብርሃኗን ለመጀመሪያ ጊዜ ነፈገቻት፤ ዙሪያዋን ጨለማ ከበባት፤ ከሚወዱት ሰው ውጭ የዓለም ከንቱነት ተገለጠላት፡፡ እናም ጌርሳሞት ከዚያች ለአፍታ አይታ ካጣችባት፣ የልቧን መሻት ከነጠቀቻት ቀን በኋላ ለብቻዋ ሆና ማልቀስን፣ ያችን የዕውን ቅዠት ተዕይንት በአዕምሮዋ ማመላለስን፣ በምናብ ወደኋላ እየተመለሱ ከንቱ የቀረ ህልምን ማንሰላሰልን፣ ህልሟን የነጠቋትን ሁነቶች ሁሉ እያሰበች መርገምን የዘወትር ሥራዋ አደረገች፤ **የቅልልቦሽ** መጫወቻነቷ እና አይቶ ማጣቷም ከዚያች ቅጽበት ጀመረ፡፡ ከገለታ ጋር በመለያየቷ ምክንያት የዋጣት ጨለማ ለዘለዓለም እንደማይነጋ እያሰበች ሁነቱን ሁሉ እንደዓለም ፍጻሜ መቁጠር ጀምራለች፡፡ "ወደ ትምህርት ቤት ወደ ገበያ ወደ ሲኒማ ወደ የትም

ስትሄድ ዛላው ህሊናዋ ውስጥ አለ ተብታባነቱም ቀጫጫነቱም የአንዳንድ እንጉርጉሮውም ወዝ፡፡ ወደ ጥልቁ ቀደ አይቶ መነፌግ ባዶ ጉድጓድ አፍጣ፣ [...] አንገቷን ሰበር አድርጋ የብር ሃብልዋ ደረቷ መሃል እንደ ደራጎን እንባ እየፈለቀ የቀሯትን ቃላቶች፡ *ሰደት ይሙት"* (አዳም ረታ፣ 2010፤ 80)

ጌርሳሞት ያጣችው የገለታን ፍቅር ብቻም አይደለም፤ ከገለታ መሄድ በኋላ ሌላ አለም እንዳለ ላሳይሽ ብሎ በቅልብልብ ምላሱ ያሳመናትን እና የገለታን በውጥን የቀረ ፍቅር ያስረሳኛል ብላ ያሰበችውን ራሚሱ (አቡ)ንም ጭምር ነው፡፡ በእርግጥ ከአቡ ጋር እዚህ ግባ የሚባል የትዝታ ጊዜ እንዳላሳለፉ ታሪኩ ራሱ ይነግረናል፡፡ ነገር ግን አግኝታው ካወራት ጊዜ ጀምሮ ደጋግማ ስለእሱ ማሰቧን ቀጥላለች፡፡ ለዚያም ነው ስልኩ ላይ ደጋግማ ስትደውል የነበረው፡፡ ታዲያ "ጣጣ ያለዘለበቱ አይመጣም" እንዲሉ ይህ ደጋግማ ለራሚሱ መደወሏ ደግሞ እስከመጨረሻው እንድታጣው ምክንያት የሚሆን ሌላ መዘዝ ገና ከጅምሩ ይዞ ብቅ አለ፡፡ ታሪኩ እንዲህ ነው፤ ከራሚሱ ጋር ስልክ ስታወራ የሰማችው እናቷ መግደላዊት ስልኳን ከእጇ ላይ መንጥቃ የራሚሱን ሰልክ ከማጥፋቷም በላይ ባለቤቷን እና የጌርሳን አባት ግስላውን አቶ ኮላሴን ከቤቱ ድረስ ልካ እንዲያስፈራራው አድርጋለች፡፡ እሱም ከቤቱ ድረስ ገብቶ እሳት በላሰ ድንፋታው አስፈራርቶ እና የማስጠንቀቂያ መልዕክት አስተላልፎ ወጥቷል፡፡ ታዲያ ጌርሳ መልሳ ለመደወል ብትፈልግ እንኳን ስልኩን ከወዴት? ራሚሱ እንዳይደውል ደግሞ ለአፍታ እነኳን የማይዘነጋው አባቷ አቶ ኮላሴ አስቀምጦት የሄደው ነጎድጓዳዊ ዛቻስ?... እንግዲህ በዚያም ይሁን በዚህ የጌርሳሞት የጎረምሳ ጥማት አሁንም ለሁለተኛ ጊዜ ከንቱ ቀርቷል፤ እንደገለታ ሁሉ ከራሚሱ ጋር ያስተሳሰረቻት ቀጭን ክር ላትቀጠል ተበጥሳለች፡፡ ሁለቱም በአንድ ጎዳና በአብሮነት ለመራመድ ቢቀጣጠሩም ከመካከላቸው ያለው ድልድይ ተሰብሮባቸው ወዲያ እና ወዲህ ማዶ ሆነው ለመተያየት እንጅ ለመገናኘት አልታደሉምና፤ በያሉበት ሆነው በሃሳብ የህልም አንጀራቸውን እንዲበሉ ተፈርዶባቸዋል፡፡

የጌርሳሞት አባት አቶ ኮላሴ ከብቸኛዋ ልጁ ጋር ቆሞ አሊያም ለጥቂት ጊዜም ቢሆን እሷን ሲያወራ ያየውን ጎረምሳ በሚችለው ሁሉ ማሳመን ይቀናዋልና፤ እንደማንኛውም ሰው ተፈጥራ ነገር ግን ህገ ተፈጥሮ የለገሰቻትን የኮረዳነት ስሜት ለማጣጣም ያልታደለችውን የልጁን የጌርሳን የፍቅር ፍላጎት በተደጋጋሚ መንጠቁን አሁንም ቀጥሎበታል፡፡ ጌርሳሞት ደግሞ ቀደም ሲል እንዳልኩት ተፈጥሮ ሳታዳላ የሰጠቻትን የኮረዳነት ፍቅር የመሻት

ስሜት ለመቅመስ ከአንድም ሁለት ጊዜ ሳይሳካላት መቅረቱ ተስፋ ሳያስቆርጣት አሁንም ለሦስተኛ ጊዜ በተለያዩ አጋጣሚዎች የሌላ ጎረምሳ ጠረን፣ የሌላ ወንድ ለስላሳ እጆች፣ የሌላ ደልዳላ እና ወንዳወንድ ገላ፣ የሌላ እኩያዋን ግብዣ እና የፍቅር መዓዛ ያለው ወሬ መፈለጓን ቀጥላበታለች፡፡ አሁንም ከበፊቱ በተሻለ የሴትነት ደንብ አምራ እና ተሽቀርቅራ ለመታየት ትጥራለች፡፡ አሁንም ዐይናፋርነቷ በሚፈቅድላት ልክ የወንድ ቁመና እና አካሄድ ማጤን፣ ማሳተዋል አብዝታለች፡፡ በዚህ መካከል የማየት እና የመታየት ዕድል የሚፈጥሩላትን ቦታዎች እና አጋጣሚዎች ሁሉ መምረጥ እንዳዘወተረች ታሪኩ ያስረዳናል፡፡ ለዚህም ነው፤ ከጓደኛዋ ከፌቨን የሥራ ቦታ (የአበባ መሸጫ ሱቅ) በረንዳ ላይ ለዕይታ በሚጋብዝ አለባበስ እና አጊያጎያጥ ተውባ መቀመጧ (አዳም ረታ፣ 2010)፡፡

የልቦለዱ ታሪክ እንደሚያወሳው፣ በዚሁ ቀን ዕለተ ሐሙስ ነበር ቀድሞ ከነገለታ ጋር ደጋግማ ታየው የነበረውን እና የሰፈሯ የታቦት ማደሪያ ልጅ የሆነውን ዘሪሁንን ያገኘችው፡፡ ዘሪሁን በተማረበት የነርስነት ሙያ ለመቀጠር ወዲያ ወዲህ እያለ ባለበት እና ሥራ ፍለጋው ባማረረው ሰዓት በፌቨን የአበባ መሸጫ ሱቅ በኩል ሲያልፍ ጌርሳሞትን አይቷት ወደተቀመጠችበት ወደ ፌቨን ሱቅ በረንዳ በማምራት ለተወሰነ ጊዜ ከጎኗ ተቀምጦ ስለውበቷ፣ ስለመገናኘት፣ ስለመገባበዝ ወዘተ ወዘተ አውርተው ሁለቱም ደግመው ሊገናኙ በስስት እና በተስፋ ተሳስበው ለጊዜው ግን ዘሪሁን የሳሳለትን ጉንጯን ስሞ፣ እሷም በመግደርደር ወግ በፈገግታ ሸኘችው፤

> ፈገግታዋ ጠቅሎ የያዘው ነገር ያለ መሰለው፡፡ የሆነ ደካማ ተስፋ፡፡ የሆነ ሁለቱም የሚጠራጠሩት እንካ፡፡ ይቺ ደካማ ፈገግታ እልባቷን አግኝቶ ቢተረትራት ከርሞ ከርሞ ከውስጧ ተግደርዳሪ እሺታ የሚወጣ፡፡ ምናልባት ቢለፋ፣ የምር ቢለፋ ያቺን እሺታ ተደግፎ እሷን እና ያቀፋትን አፎት እንደዋሸንት ሊነፋቸው ይችል ይሆናል፡፡ ትቷት ሲሄድ በሁለመናው እያሰባት ነበር፡፡ (አዳም ረታ፣ 2010፤ 97)

ጌርሳሞት እና ዘሪሁን ያለሙት ዳግም የመገናኘት ተስፋ ይቺን አጋጣሚ ማለፍ ተሳነው፤ የመገናኘት ህልማቸው በዚች ተስፋ ባዘለች ስንብታቸው ተደመደመ፡፡ ታሪኩም ይህንን አጋጣሚ እንዲህ ይነግረናል፤ ዘሪሁን ጌርሳን ተሰናብቷት እሷ ስለእሱ መልሳ-መላልሳ እያሰበች፣ እሱን ስለ እሷ እያብሰለሰለ ጥቂት እንደሄደ አቶ ኮላሴ የሆነውን ሁሉ ሲከታተሉ ቆይተው ኖሮ በሃሳብ እየናወዘ ከሚጓዘው ዘሪሁን ፊት ለፊት መጥተው ተገተሩ፡፡ የአቶ ኮላሴ እርምጃ ግን መንገድ በመዝጋት ብቻ የተገደበ አልነበረም፤ የዘሪሁንን እጅ ጨምድዶ በመያዝ አድርጎ፣ ባስፈሪ ፊታቸው ቁጣ አሳልጠ፣ በፈርጣማ ጡንቻቸው ጥፊ ታጥፎ፣ መላ

ሰውነቱ እስኪዝል ድረስ የዘሪሁንን አፍ እና ጭንቅላት "ደስ ባር" ከተቀመጠ ጠረጴዛ ጋር በኃይል እስከማጋጨትም ድረስ የዘለቀ ነበር (አዳም ረታ፣ 2010)፡፡ ታዲያ በዚህ ሁኔታ ዘሪሁን ለዚህ ሁሉ ነገር ምንጭ ወደሆነችው ጌርሳሞት ምን ቀርቶት ይመለሳል? ጌርሳሞትስ ብትሆን የአባቷን ማስጠንቀቂያ እና አስፈሪ ዱላ በየት በኩል አልፋ ከዘሪሁን ጋር ትጎዳኝ? ስለዚህ የዘሪሁን እና የጌርሳሞት ድጋሚ የመገናኘት፣ በፍቅር አየር የመንሳፈፍ፣ በመውደድ ባሕር የመዋኘት ምኞት እውነትም ምኞት ብቻ ሆኖ ቀርቷል፡፡

አሁን ጌርሳሞት ለመጨረሻ ጊዜ አንድ ዕድል ብቻ ቀርቷታል፤ ከአንድ ሁለት፣ ከሁለት ሦስት ጊዜያት አጥብቃ የሻተችውን እና አንድም ጊዜ ያልተሳካላትን የፍቅር ህይወት እውን ሊያደርግላት የሚችለው የፍቅር ተስፋዋ ከአራቱ የሰፈር ልጆች (ጓደኞቾ?) መካከል ባካፋ ብቻ ሆኗል፡፡ ሌሎቹ ሁሉም ተሻምተው ቀልበው በየሰበቡ ወዲያው እየጣሏት አልፈዋል፡፡ እርሷም እራሷ አንዱን ሸኚቶ ሌላውን በመቀበል የኮረዳነት ጠኔ ተለክፋለችና፤ ከዚያችው ከፌሽን የአበባ መሸጫ ሱቅ ደምቃ እንደተቀመጠች ለጓደኛው ሰርግ የሚሆን አበባ ለመግዛት በመጣበት አጋጣሚ ከረጅም ጊዜ ቆይታ በኋላ ከአራቱ የቀድሞ ጓደኞሞች መካከል ትምህርቱን ጨርሶ የባንክ ቤት ሠራተኛ ከሆነው ከባካፋ ጋር እንደተገናኙ የልቦለዱ ታሪክ ያትታል፡፡ በዚሁ ቀን ምሽት ላይ "ከቁንጣን በላይ" የሆነ ግብዣ፣ ከቀሚሷ ስር እስከውስጥ ሱሪዋ የሚደርስ የእጅ የፍቅር ሙዚቃ ቅኝት፣ ደስታ፣ ፍርሃት እንደገና ብዙ ብዙ ደስታ እንዲሁም በደስታ ላብ መታጠብ፣ በፍቅር ትንፋሽ መሞቅ፤ ለጥቂት ሰዓታት እነዚህ ሁሉ ነገሮች እንዳለፉ ይተርካል (አዳም ረታ፣ 2010)፡፡

ከእነዚህ ሁሉ ያልተጠበቁ ድራማዊ ትዕንቶች በኋላ ባካፋ ለሁለት ሳምንታት ያክል ቆይታ ለሥራ ጉዳይ ከአገር ሊወጣ እና ወደኬንያ ሊሄድ እንደሆነ በመግለጽ የለመደችውን የአይቶ ማጣት ዕጣዋን እንዲህ ያረዳታል፤

> [...] ባካፋ ላንጋኖ ጠልቆ እንደወጣ ሁሉ ይተነፍሳል፡፡ የትንፋሹ ላቦት እንደ ግንቦት አየር ነው፡፡ አቀፋትና፡--አትዋፊ......አትዋፊ አላት፡፡ መናገር አልቻለችም፡፡ አይኖቹ ውስጥ የምታው ፍላጎቱ ትኩረቷን በታተነው ባካፋ ልክ ገብቷል፡፡ [...] ለስራ ጉዳይ ከነገ ወዲያ ኬንያ እሄዳለሁ፡፡ ከአስራ አምስት ቀን በኋላ ስለምመለስ እደውልልሻለሁ፡፡ አቀፋት ግን መልሳ ለማቀፍ አልቸኮለችም፡፡ ጣቶቹ ወገቧን ነከሱ ለቀቁ፡፡ ድግሞ ነከሱ፡፡ ደሞ ላይና ታች ዳበሱ፡፡ ትንሽ ደሞ ሳባት ወደራሱ፡፡ የአምስት ሰከንድ ስራ ለእሱ፡፡ ስለወንድ ባታውቅም የሚሰማት ግን [...] መንገደኛ እያየ ለባካፋ መንጋለል ነው፡፡ (አዳም ረታ፣ 2010፤ 107-108)

ጌርሳሞት እንዲህ ለጊዜው በሚመስል መልኩ እየተሰናበተች እስከ መጨሻው ድረስ መሸኘትን የህይወቷ አንድ ቋሚ ገጽታ አድርጋዋለች፤ ከአንድም ሁለት ጊዜ፣ ከሁለትም ሦስት ጊዜ፣ ከሦስትም አሁን ለአራተኛ ጊዜ፡፡ ባካፋ እንዳለውም ወደ ኬንያ ተሸገረ፡፡ ሰዓታት ተቆጠሩ፤ ቀናት አለፉ፤ ሳምንት አልቆ ሌላ ሳምንት ተተካ፡፡ ነገር ግን ባካፋ ገጹ ብቻ ሳይሆን ድምጹ እንኳን ከጌርሳሞት አብዝቶ እርቋል፤ አድራሻውን ሁሉ አጥፍቶ ጠፍቷታል፤ ብቻ የውሃ ሽታ ሆኖባታል፤

> ሳምንት አልፎ ሌላ ሳምንት፡፡ ለባካፋ ስልክ ደጋግማብትደውል አይነሳም፡፡ ክለብ ሶፋ ላይ እግሮቿን አነባብራ ተቀምጣ፣ ቀዝቃዛ የበረንዳ እና የጽድ ጥላ ስር **የሎሚ ጭማቂ እየጠጣች** ለባካፋ ያላትን ጥልቅ ፍላጎት እያሰበች [...] የሚያመጣውን ጭንቀት መጨነቅ ልምድ ይጠይቃል፡፡ የቀለበችው ሁሉ ከእጇ እያፈተለከ፡፡ ምኞቷ ነው ወይስ ዘመኑ ነው ጠማማ? ይሄን የጠለቀ ስሜቷን መስመር የሚያስይዘው ባካፋ የለም፡፡ [...]ነፍሷ ሰው የሌለበት አለም ዜጋ ናት፡፡ (አዳም ረታ፣ 2010፤ 115-116)

ጌርሳሞት እንደለመደችው ሁሉ በቁም ቅዠት፣ ትርጉም (ምላሽ?) በሌለው የህልም ዓለም፣ በከንቱ ምኞት እና ተስፋ ስቃይ ውስጥ ተዘፍቃለች፡፡ ዓለም የያዘችውን እያስጣለች ጎምዛዛ ጣዕሟን (**የሎሚ ጭማቂዋን**) ትግታታለች፡፡

የልቦለዱ ታሪክ እንደሚያስረዳን፣ ባካፋ ወደጓጓለት ኬንያ ከሄደ በኋላ እንዳሰበው የተመቸው አልሆነም፤ ኪሱንም የቋመጠለትን ያክል በዶላር አልወጠረም፤ ይልቁኑ እዚያው ኬንያ ባለበት ሰዓት ባጋጠመው የምግብ መመረዝ (አለርጂ?) ምክንያት እራሱን ስቶ፣ ሰውነቱ ተዝለፍልፎ በሌሎች ሰዎች እርዳታ እራሱን ሆስፒታል ውስጥ አልጋ ላይ አገኘው እነጂ፡፡ የሆነው ሁሉ ሆኖ እሱም ከሆስፒታል ወጥቶ ወደ አገሩ አዲስ አበባ መምጣቱ ግን አልቀረም፡፡ አዲስ አበባ እንደገባ ሁሉንም ነገር ፈርጅ ፈርጅ ካስያዘ በኋላ በቀጥታ ለጌርሳ ደውሎ "ሶሲ ካፌ" ቀጥሯት እንደመጣች ነበር ሌላ የሞቀውን ህይወቱን የሚያቀዘቅዝ በረዶ የወረደበት፤ በህመም ላይ ሌላ ህመም የሆነበት (አዳም ረታ፣ 2010፤ *142-143*)፡፡

አዎ! አሁን ጌርሳሞት ለመጨረሻ ጊዜ ጉም እንደመጨበጥ፣ ከዝንብ ማር እንደመናፈቅ፣ በሰማይ ሜዳ ላይ እንደመጫወት ወዘተ ወዘተ የፍቅር ህይወቷ ከንቱ ምኞት ብቻ ሆኖባታል፡፡ ከባካፋ ብቻ ሳይሆን ከማንም ዕይታ ውስጥ የሚከቷትን ከናፍሮቿን አበላሽታቸዋለች፤ ስለዚህ አሁን ጌርሳ ሌላ ሰው ሆናለችና ከተቀጣጠሩበት ስፍራ የተገናኙት ለመጨረሻ ጊዜ ለመሰነባበት ብቻ ሆኗል፡፡ "...የመጣችው ሰዓቷን አክብራ

ቢሆንም ያልጠበቀው ነገር አጋጠመው፡፡ […] ጥርሶቿን ብሬስ ተሰርታለች፡፡ […] ብሬስ በተሰራች በሁለተኛው ቀን ከንፈሮቿ አብጠው እና ቆስለው ሕመምተኛ ሆነች፡፡ […] ጌርሳሞት ለአፍታ ሰፊ መልዕክት ሆነችበት፡፡ ሲሰነባበቱ ደግሞ እንደማያገኛት አያወቀ ነው፡፡" (አዳም ረታ፣ 2010፤ *142-143)*

የባካፋ እና የጌርሳሞት የመጨረሻ ስንብትም ከዚህ አስደንጋጭ የግንኙነት ክስተት እና ትዕይንት ጀምሮ ሆነ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ፣ ባካፋም ቢሆን በአንድ በኩል ያንን አብዝቶ የቋመጠለትን የጌርሳን ገላ (ከንፈር) እና ፍቅር ጨርሶ ባልጠበቀው መንገድ አጥቷል፤ በሌላ በኩል ደግሞ በደህናው ከሄደበት ከኬንያ ይዞት ከመጣው የምግብ መመረዝ በሽታው በተጨማሪ በአንድ ጊዜ የሌሎች በርካታ በሽታዎች ማደሪያ ሆኖ ህላዌውን በሆስፒታል ውስጥ እንዲገፋ ተገዷል፤ ጤናማነቱን ተቀምቷል (ምናልባት ይቺን ዓለምስ ሊሰናበት ይችል ይሆን?)፡፡

"-- ጌርሳሞት ሰማሽ? አለች ፌቨን

--እ? አለች ጌርሳሞት

[…]

--ባካፋ በጣም ታሞ ጥቁር አንበሳ ተኝቷል … (አዳም ረታ፣ 2010፤ 229-230)

በእርግጥ አሁን ጌርሳሞት ዓልማ ያጣችው ገለታን፣ ራሚሱ (አቡ)ን፣ ዘሪሁንን እና ባካፋን ብቻ አይደለም፤ እራሷን፣ ገላዋን፣ በተለይም ታይቶ የማይታለፈውን ጽጌረዳ **አፏን**ም ጭምር እንጂ፡፡ አሁን የምትመካበት ውበት የላትም፡፡ አበባ ከናፍሮቿ ሳያፈሩ እረግፈዋል፤ የፍቅር መግነጢስ የነበረው **አፏ** እንዳልነበረ ሆኗል፡፡ ከዚህ በኋላ ጌርሳ አይቶ ማጣት ብቻ ሳይሆን ጭራሹኑ በወጉ መታየት እንኳን አትችልም፡፡ የሁለንተናዋ ድምቀት የነበሩት ከናፍሮቿ በፊት ያደመቋትን ያክል አሁን ደብዝዘው አደብዝዘዋታል፤ ይሆናል ብላ ባልጠበቀችው ቅጽበት እንግዳ መልክ እና ቅርጽ ይዘዋል፡፡ "… ከንፈሮቿ ጥቁር፣ አባጣ፣ ከርፋፋ ሆነዋል፡፡ የበቅሎ መስለዋል፡፡" (አዳም ረታ፣ 2010፤ *143)*

እንግዲህ በአጠቃይ በአፍ ልቦለድ ውስት ጌርሳሞት በርካታ ጊዜ ነገር ግን ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ በሦስት ዋና ዋና አጋጣሚዎች ብርሃኗ ጨልሞባታል፤ በእጇ የጨበጠቻቸው የህይወት ህልሞቿ አምልጠዋታል፤ አሊያም ደግሞ ዳግም ላይገኙ ለመጨረሻ ጊዜ

ወድቀው ተሰብረውባታል፤ ማራኪ ፈገግታቸውን ለአፍታ አሳይተው ለዘለአለሙ ጋግርት ሆነውባታል፤ እልቆ ቢስ የመሰለ ህብስት አሳይተው በዚያው ቅጽበት እስከ መጨረሻው ሰውረውባታል፤ ጥቂት የህላዌ ፈውስ የሆሚሆን ሙቀት ፈጥረው ወዲያው ደግሞ ከማትቋቋመው ቁር ውስጥ ቀብረዋታል፡፡ ከእነዚህ ሦስት ዋናዋና አጋጣሚዎች መካከል የፍቅር አይቶ የማጣት ድግግሞሽ ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል፡፡ "እነዛ ሰዎች ገለታ፣ ራሚሱ፣ ባካፋ አይደሉም፡፡ በቃ አይኖች ናቸው፡፡" (አዳም ረታ፣ 2010፤ 116)

ከፍ ሲል እንደተነሳው ጌርሳሞት ለአራት ያክል ተከታታይ ጊዜያት የጓጓችላቸውን፣ አብዝታ የቋመጠችላቸውን የፍቅር ህብስቶች ለአንድ ጊዜ እንኳን ሳትቋደስላቸው በዕይታ ብቻ እንደሳሳችላቸው ቀርታለች፡፡ የወጣትነት የፍቅር ጥማቷን ለማርካት ያደረገችው ያላሰለሰ ቁፋሮዋ ከንቱ ሆኖ ከማትወጣቸው በርሃዎች ውስጥ ቀላቅሏታል፤ ጥሟን አባብሶታል፡፡ አሰሳዋ ሁሉ አየርን መዝገን ሆኖባታል፤ ከገለታ እስከ ባካፋ፣ ከዘሪሁን እስከ ራሚሱ ድረስ አጥብቃ እንዳትጨብጣቸው ሁሉም ስለታም ጎናቸውን ሰጥተው የስለታቸውን ያክል ሸርክተዋት፣ አድምተዋት አልፈዋል፡፡ በፍቅር ፍለጋ የደከመ ጎኗን በምቾት ለማሳረፍ የተጠጋቻቸው ባለ ለስላሳ ገላዎች ከእሷ ፊት ሲቀርቡ እሾህ አብቅለው በተለያየ መጠን ወግተዋታል፡፡ ጌርሳ ፍቅር ናፋቂ እንጅ ተቋዳሽ ለመሆን የታደለች ከቶውንም አይደለችም፡፡

ሌላው እና ሁለተኛው አጋጣሚ ደግሞ የውበቷን ከንቱ መቅረት የሚመለከት ነው፡፡ ጌርሳሞት ያ ሁሉን የሚያፈዝ፣ ያየውን ሁሉ በቆመበት የሚያደርቅ የከንፈር (የአፍ) ውበት በመጨረሻ እንዳልነበረ ሆኗል፡፡ "ውበት ሐሰት ነው፣ ደም ግባትም ከንቱ ነው፤" (ምሳ. 31፤30) እንዲል መጽሐፈ ምሳሌ፣ ከጥቂት ጊዜያት በኋላ በዕጌረዳነቱ የእሷን ውበት አድምቆ ሳጨርስ የጠዋት ጤዛ ሆኗል፤ ወዲያው ታይቶ ጠፍቷል፡፡ መፍካት የጀመረው አበባዋ ሙሉ መልኩን እንኳን በቅጡ ሳያሳይ ወዲያው ከስሟል፡፡

> ጌርሳሞትን … አሁን የሚያሳስባት በሽቦው ምክንያት ከንፈሮቿና ድዷ ቆስለው እንቅልፍ መነሳቷ ነው፡፡ ምርቅዙ መቁሰል ብቻም ሳይሆን ጥቂት ቦታም መምገል ጀምሯል፡፡ … መስታወት ፊት ለፊት ቆማ ገጽዋን ስታይ የምታየው ቀድሞ ያልነበረ በቦምብ የተመታ ባግዳድ የመሰለ አስቀያሚ አፏን ነው፡፡ (አዳም ረታ፣ 2010፤ *228)*

ይህ ታይቶ የጠፋው የአፏ ሁኔታ በመወደድ ፋንታ መዘባበቻ፣ በማሳመር ፋንታ እረፍት የሌለው ህመም ተክቶላት እንቅልፏን፣ ምቾቷን፣ ዘለዓለማዊ እረፍቷን አሳጥቷታል፤ ለጋነቷን፣ ወጣትነቷን፣ ትኩስነቷን ሁሉ ጠቅልሎ ነጥቋታል፤ "ጌርሳሞት መልስ ስታጣ በመሰላቸት ወደ ባዶው መንገድ ፊቷን አዞረች፡፡ ቆሻሻ አስፋልት፡ ስስ ጭቃ የለበሰ፡፡ ዝናቡ አዲስ ነው ግን መሬት ከመንካቱ ሽበት አውጥቷል፡፡ የወጣት መንገድ ነው የጀመረችው ግን በቅቷታል፡፡" (አዳም ረታ፣ 2010፤ 232)፡፡

ሦስተኛው እና የመጨረሻው አጋጣሚ፣ ወላጅ አባቷን አቶ ኮላሴን በድንገት ያጣችበትን የህይወቷን የማጣት ጉዞ የሚመለከት ነው፡፡ ጌርሳሞት የአባቷ ድንገት መጥፋት ከአፏ አሰቃቂ ህመም፣ ከፍቅር ቅልልቦሽ መጫወቻነቷ ጋር ተዳምሮ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ሆኖባታል፤ ምቾት ማጣቷን አባብሰውባታል፡፡ እርግጥ ነው ከአባቷ መጥፋት ይልቅ የአፏ ቁስለት እና ህመም የበለጠ አሳስቧታል፡፡ ይሁን እንጅ እንደ አንዳች ምትሃታዊ መንፈስ በአንድ ጠዋት ተነስቶ ወደ መሬት ይስረግ፣ ወደ ሰማይ ይትነን ብቻ ድንገት ሲሰወር የወለዳትን ልጁን አይደለም የሚያውቀውን ሰው ሁሉ ማሳሰቡ፤ ማስጨነቁ አልቀረም፡፡ የማንም ጎረምሳ እንደፈለገ እንዳይገላምጣት የሚከላከልላት የክብሯ ጥላ፣ እንደ ዐይኑ ሁሉ ይሳሳላት የነበረው አባቷ ዛሬ መንፈስ ሆኖ እንደጭስ ካጠገቧ ብን ብሎ ጠፍቷል፤ የአባትነት ፍቅሩን በውል ሳትተረጉመው እስከ መጨረሻው አጥታዋለች፡፡ ድንገቴ መሰወሩ እሷን ጨምሮ እናቷን መግደላዊትን በታላቅ ሰቀቀን ውስጥ ከቷቸዋል፡፡ ከዚህም አልፎ ለአካባቢዉ ማህበረሰቦች እና ለምርመራ ቡድን አባላት ፖሊሶችን ሁሉ ግራ የሚያጋባ እና ያልተለመደ አይነት አድራሻቢስ ሆኖ አሳስቧቸዋል፡፡ ስለሆነም ይህ የአቶ ኮላሴ ድንገት መሰወር ለልጁ ለጌርሳሞት አንዱ የህይወቷን የማጣት ጉዞ የሚያጎላ ሁነት ነው ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡

በሐፍ ልቦለድ ውስጥ ሌላኛው የርእይ መነጠቅ ሰለባ የሚሆነው ገፀ ሰብ ደግሞ ገለታ ነው፡፡ ጌርሳ የእሱን ፍቅር አይታ እንዳጣች ሁሉ እርሱም እንደጎመዠ፣ የስሜት ለሀጩ እንደተዝረበረበ ድጋሚ እንኳን ሳያገኛት ላይመለስ ከፊቷ እርቋልና፤ ከላይ እንደተነሳው ሁሉ የአፍቅሮ ማጣቱ ሰይፍ አንዱ ስለቱ የሚያገኘው እራሱንም ጭምር ነው፡፡ ገለታ ጌርሳን ለማግኘት ከሌሎች አብሮ አደግ ጓደኞቹ ተለይቶ ፈልጓል፤ ከእሷ ጋር ሲሆን ከቀድሞ ጓደኛው ከሰላማዊት ጋር ከሚሆነው በተለየ እና በተሻለ ደስታን ይፈጥርለት ስለነበር ከጌርሳ ጋር ብዙ ጊዜያትን ማሳለፍ ይመርጥ ነበር፤ ባገኛት ቁጥርም ቢሆን ለእሷ

ያለው ስስት ቀላል የሚባል እንዳልነበረ የልቦለዱ ታሪክ ምስክር ነው፡፡ ታዲያ የስሜቱን ደርዝ ሊያሳያት በጎመገቦት ቅጽበት በዛች በእናቷ ምትሃታዊ ጥሪ ምክንያት መቋረጡ የእሱንም እራስ አሳምሞታል፤ ያመነጨውን ምራቅ መልሶ አስውጦታል፤ የመለየት መብረቅ ሆኖ ጮሆ አስደንግጦታል፤ "[…] ፊቷ እጁ ውስጥ እያለ እናቷ ስትጠራት የደነገጠችው ድንጋጤ እሱም አባቷን የፈራው ፍርሃት በመሳም የሚያገኘው ደስታ እንዲቋረጥ መሆኑ የጌራ ከንፈር ውስጥ አስተማሪው የሰበከው አይነት ስሌት መኖሩን ጠረጠረ፡፡ የጎደለው ነገር ያለ መሰለው፡፡ እራሱንም አመመው" (አዳም ረታ፣ 2010፤ *76)፡፡*
ገለታ የሳሳላትን ፍቅሩን ጌርሳን በዚህ አስደንጋጭ ምክንያት አጥቷል፤ እንደ ጭጋግ ከእጁ ውስጥ ተና ጠፍታበታለች፡፡

ገለታ የተነጠቀው የጌርሳን ፍቅር ብቻም አይደለም፤ የህልውና ፍላጎቱን እና ሙሉ ህላዌውንም ጭምር እንጂ፡፡ በአገሩ ውስጥ ካለው የፖለቲካ ሁኔታ እና ወሬ ከሚወድ ማህበረሰብ ጋር መኖር ሰልችቶታል፤ የአገሩን አስተዳደራዊ ሥርዓት እና ይህን ሥርዓትም የሚከተሉ ሰዎች አስጠልተውታል፡፡ በዚህም ምክንያት ትምህርቱን እንኳን ሳይቀር አቋርጦ ከሚጠላው ማህረሰብ ለመሸሽ እግረመንገዱንም ዳጎስ ያለ ገቢ ለማፈስ ወደውጭ አገር ተሰዷል፤ "የገለታ ሽፍትነት ተደጋግሞ ከሚነገረው ተቀባይነት ካገኘውና እንደ አየር ከከበበው በማንም ወሬኛና ፖለቲኛ በሚነዛ አግኖስያ ላይ ነው" (አዳም ረታ፣ 2010፤ *66)፡፡*

የገለታ ምኞት እና ፍላጎት አውሮፓ ወይም ደግሞ አሜሪካ መሄድ ቢሆንም፤ ካሰበው ሳይደርስ ውጥኑ፣ ሃሳቡ፣ እሱነቱ ሁሉ ከመንገድ በጅምር ቀርቷል፡፡ ገለታ ደቡብ አፍሪካ ውስጥ "በኢስፒን" እና "በኦሪየንት" ኮረብታዎች መካከል በሚገኝ እና "ሎተስፓርክ" ወደሚባል ቦታ በሚሰድ መንገድ ዳር ምክንያቱ በውል ባልታወቀ እና እርሱ ከነመሆኑ እንኳን በእርግጠኛነት በማይተወቅበት ሁኔታ ይቺን ዓለም እንደተሰናብተ፤ ለዘለዓለሙ እንዳሸለበ ታሪኩ ይግረናል፤

> የልጁ ፊት ለጋ ጊም ያቆጠቆጠበት ነው፡፡ ዐይኖቹ አጠገብ ያለ ሳር የሚያዩ ይመስላሉ፡፡ በከፊል ተከፍተዋል፡፡ ቀላ ያለ ልጋግ በአፉ ቀኝ ደርዝ ፈሶ ወጥቶ አገጩ ላይ ደርቋል፡፡ […] ዛፎች ስር የልጁ ቀኝ እጅ አረፈበት ድረስ ቢጫ አባበባ ያላቸው ሱዛናዎች ይንቦገቦጋሉ፡፡ ምናልባት ለክብሩ ወይ **ለቅሌቱ** ነው" (አዳም ረታ፣ 2010፤ *212)፡፡*

ከዚህ አንጻር እንደ Maxwell ሐተታ በመጀመሪያ ደረጃ የገለታ አገር ለቆ መውጣት በራሱ ቀድሞ በአገሩ ላይ ያጣው ነገር እንዳለ ያመላክተናል፡፡ ከዚህ ባለፈ ደግሞ ከጅምሩ ከአገር ለቆ ሲወጣ የሰነቀው ምቹ አስተዳደራዊ ሥርዓት ፍለጋው እና ከምቹ ማህበረሰብ ጋር አብሮ የመኖር ምኞቱ በሞት ምክንያት ከንቱ ሆኖ እንደቀረበት እንገነዘባለን፡፡ ገለታ አብዝቶ የሻተው ተከባብሮ (ተከብሮ?) የመኖር ህልም **ቅሴት** (ውርደት) ሆኖ ያለቦታ፣ ያለሁኔታ አስቀርቶታል፤ አበባ ህይወቱን ቀምቶታል፡፡ ይህ ደግሞ ሌላው የገለታን የርእይ መነጠቅ የሚያጎላ ሁነት መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ ስለዚህ በጥቅሉ ገለታ ወዲህ በህይወት እያለ ይሳሳላት፣ ይንገበገብላት አብዝቶ ያስብላት የነበረችውን የጌርሳን ፍቅር፣ ወዲህ ደግሞ እናት አገሩን እና አገር ያስለቀቀውን ምኞቱን፣ በስተመጨረሻ ደግሞ ከዚህ ሁሉ በከፋ መልኩ ውድ ህይወቱን በተለያዩ ምክንያቶች አጥቷል፡፡

ከላይ እንደተነሳው፣ የገለታ ከአገር መውጣት ከጌርሳሞት በተጨማሪ እራሱን ገለታን እና የገለታን ቤተሰቦች በተለይም ደግሞ እናቱን ፎርቱናንም ጭምር ለዚህ አይቶ ማጣት ሰለባዎች፣ ተቋዳሾች አድርጓቸዋል፡፡ ለአንድ ቀን እንኳን ሲለያቸው የሚጨነቁት ፣ ካጠገባቸው ሲርቅ የወላድ አንጀታቸው የሚንሰፈሰፍለት የገለታ እናት ወይዘሮ ፎርቱና አድጎ የድህነት አሜካላዬን ይነቅልልኛል በሚል  እምነት በችግር ተጠብሰው ያሳደጉትን፣ ሰው ሆኖ ሰው ያድርገኛል ብለው ያሰቡትን እና ሙሉ እምነት ያሳደሩበትን የህይወት ምርኩዛቸውን፣ ባረጅ ይጦረኛል፤ ብሞት ይቀብረኛል ብለው የሚያስቡትን እና ታላቅ ተስፋ የሚጥሉበትን ብቸኛ ወንድ ልጃቸውን ገለታን ሲያጡ በከባድ የሃዘን አዘቅት ውስጥ ገብተዋል፡፡ አንድ ተስፋቸውን ተነጥቀዋል፤ ልጃቸውን እንደዐይናቸው ብሌን የሚሳሱለትን የአብራክ ክፋያቸውን፣ መሪ፣ ደጋፊ ምርኩዛቸውን አጥተዋል፡፡ ከእሸቱ ሊበሉ ዐይን ዐይን የሚያዩት እና በታላቅ ጉጉት የሚጠባበቁት የህይወት ዘመን ሰብላቸው ገለታ በአንድ ቅጽበት የስደት በረዶ ጨፍጭፎታል፤ ዳግም ላያገኙት ከፊታቸው  እስከመጨረሻው ጠፍቷል፤ እትብቱ ከተቀበረበት ከአገሩ፣ ከእናቱ ነጥሎ ድንገት ደራሽ ጎርፍ ጠራርጎ ይዞት ነጉዷል፡፡ በዚህ ምክንያት ከታላቅ የልብ ስብራት እና ከባድ ሃዘን ውስጥ እንደወደቁም ልቦለዱ ያስነብበናል፤

> […] ገና በር አንኳኩታ ከእናቱ ከፎርቱና ጋር ዐይን ለዐይን ሲገጣጠሙ ወሬው ልክ እንደሆነ ገባት፡፡ ገና ሲያዩአት ‘አይ ባፈና! አይ! አይ! አንድ ወንድ ልጄ ይጦረኛል የምለው ትቶኝ ሂደ ባፈና!’ አሉና እተቀመጡበት (…) ማልቀስ ጀመሩ፤ ተቀምጠው አልቀሩም ቆመው እየተንጎራደዱ ወገባቸውን ይዘው እንደ ሚች ሸኚ እዬዬአቸውን

> አቀለጡት፡፡ ጌርሳሞት ምን ማድረግ እንዳለባት ግራ ገብቷት አፏን ይዛ ዕንባ እየተናነቃት ትታቸው ሄደች፡፡ (አዳም ረታ፣ 2010፤ 77-78)

አሁን ፎርቱና እርሳቸው እንዳሰቡት የድህነት አቧራቸውን የሚያራግፍላቸው ብቻም ሳይሆን በጥልቅ ሃዘን ውስጥ ወድቀው የሚያነቡትን እንባ እንኳን የሚያብስላቸው ልጅ የለም፡፡ ከድህነት ጎጇቸው ለቃቅመው ለሚወዱት ታቦት ሁሉ ቢሳሉም ስለታቸው ከንቱ ሆኖ ልጃቸው ገለታ ሳይመለስ ወጥቶ ቀርቷል፤ የበላው አውሬ ከቶውንም አልጮህ ብሎ የውሃ ሽታ ሆኖባቸዋል፡፡

እንግዲህ ከላይ እንደተጠቀመው፣ በዚህ ሰፊ በተሰኘ ልቦለድ ውስጥ የተገለጹ ከዓበይት እስከ ንዑሳን ገፀ ባህርያት ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ በተለያየ መልኩ ርእያቸውን ከሞላ ጎደል የተነጠቁ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ከእነዚህ ሁሉ ገፀ ባህርያት ደግሞ የጌርሳሞት የአይቶ ማጣት የህልውና ጉዞ እና **የቅልልቦሽ መጫወቻነት** ትልቁን ስፍራ እንደሚይዝ ከዚህ በላይ በሰፊው ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ ነገር ግን ከጌርሳ በተጨማሪ ሌሎቹንም አንድ በአንድ የተመለከትን እንደሆነ ዋና ዋናዎቹ ገፀ ባህርያት ገለታ፣ ባካፋ፣ ዘሪሁን እና ራሚሱም በተለያየ መጠን አይተው አጥተዋል፤ አንዱን ጨብጠው ሌላውን ለቀዋል፤ በህይወት ዘመን ጉዟቸው ሊደርሱበት የፈለጉትን አጥተው በህይወት አዙሪት ስር በመውደቅ አጋጣሚያዊ ኑሯቸውን ገፍተዋል፤ አሊያም ደግሞ መንገዳቸው በሙሉ በእንቅፋት ተሞልቶ ካሰቡት ጫፍ ሳይደርሱ በጅምር ቀርተዋል፡፡ ቢያንስ እንኳን እነዚህ አራት አብሮ አደጎች፣ የአንድ ሰፈር ከዋክብቶች የሰፈራቸውን ደማቅ ጨረቃ ጌርሳሞትን በእጃቸው ለማስገባት ሲሉ እርስ በእርስ ከመራራቅ አንስቶ የየራሳቸውን የመማረኪያ ዘዴዎች እስከመጠቀም ብሎም በአባቷ በአቶ ኮሳሴ ግልምጫ፣ ማስፈራሪያ እና ዱላ እስከመነ'ረት ድረስ ብዙ መስዋዕትነትን ከፍለዋል፡፡ ይሁን እንጅ ይቺ የወቅቱ ደማቅ ፀሀይ አንዳቸውንም እንዳሰቡት አላሞቀችም፤ ደምቃ አላደመቀችም፡፡ ሁሉም እየጨበጡ ለቀዋታል፤ እያነሱ (እየቀለቡ) መልሰው ከነበረችበት ጥለዋታል፤ አንዳቸው ከሌላቸው ተቀባብለዋታል እንጅ ከአንዳቸውም መዳፍ ውስጥ አርፋ አልተቀመጠችም፡፡ ይህ ደግሞ ሁሉም የሚጋሩት ፈሬ አልባ ድካም፣ ስኬት አልባ ጥረት፣ ከንቱ የቀረ ምኞት ነው፡፡

ከልቦለዱ ታሪክ እንደምንረዳው፣ በመጀመሪያ ሁሉም የየራሳቸው መልክ፣ ቁመና እና መለያ ባህርያት ያሏቸው ነገር ግን አንድን ሰፈር ተጋርተው ከመኖርም ባለፈ በእድሜ እኩያነትም ይሁን በሌሎች አዛማጅ ምክንያቶች እርስ በእርስ የተሳሰሩ እና በአንድ ላይ

የተገመዱ ህብረወጣቶች ነበሩ፡፡ ይሁን እንጅ በኋላ ግን ሁሉም ጌርሳሞትን የየግላቸው ለማድረግ አጥብቀው ከመፈለጋቸው የተነሳ አስበውትም ይሁን በአጋጣሚ በአራት በአምስት ሜትር ርቀት የተተከሉ አፍላ ዛፎች ሆነዋል፡፡ ሁሉም ቅርንጫፎቻቸውን አስፍተው ጌርሳን ለማስጠለል የሚታትሩም ይመስላሉ፡፡

> የድር እና ማግ መረብ ሆነው፡ ሁለቱ የድር የቀሩት የማግ ሆነው፡፡ ፉክክርም ይመስላል፡፡ ፉክክር መጓተት ነውና መረቡን የማይመች ውጥር ያደርገዋል፡፡ [...] ምናልባት ወዳጅነታቸው ውስጥ **የተገነባው** ግን የተደበቀው ጊዜ የሚያወጣው የሕይወት ጉዞ በጨረፍታ እራሱን ሲያሳይ ሆናል፡፡ ሁሉ ነገር ተለዋዋጭ ከሆነ፡ በርሃው ካበበ፣ ያበበው ከረገፈ፣ የረገፈው ከፀደቀ እንዲህ የተሰበሰቡት ወጣቶች የማይበታተኑበት ምክንያት ኖራል? [...] ከዛ አቋቋማቸው ይሄ የተፈጥሮ ሕግ እንዳለ መጠርጠርን ይገፋፋል፡፡ (አዳም ረታ፣ 2010፤ 46-49)

ቀድሞ በነበራቸው በተቀራረበ እና ዝግ በሆነ ጥግግታቸው መካከል በተፈጥሮ የስሜት ልዋጤ ሕግ ሽፋን ተጠቅልላ ጌርሳሞት የተባለች አጥር **ተገንብታ** አራርቃ ተክላቸዋለች፡፡ ከፍ ሲል እንደተነሳው፣ እርሷም በመንገዷ ላይ እዚህም እዚያም ስታገኛቸው ከአንዱ ተነስታ ከሌላው ጥላ ስር ታርፋለች፤ ደግሞ በሚገባ ሳትጠለል ወዲያው ወደ ሌላው ትሻገራለች፡፡ ይሁን እንጅ ሁሉም በሙቀት ከሚያንገበግባት ጨረር ሙሉ በሙሉ አላሳጣሏትምና፤ በመጨረሻም የአራቱንም ጥላ ጨርሳ ምንም ከሌለበት ምድረበዳ ላይ በሐሩር ትቃጠላለች፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በልቦለዱ ውስጥ ካሉት በርካታ ንዑሳን ገፀ ባህሪያት መካከል በተለይ ከዓበይት ገፀ ባህሪያት ጋር የጠበቀ ዝምድና ያላቸውን ገፀ ሰዎች ህልውናዊ ርእይ የተመለከትን እንደሆነ፤ የጌርሳሞት እናት መግደላዊት በመጀመሪያ የልጅነት ተስፋዋን በአባት እና እናት አልባነት የተነጠቀች፣ ያለ እናት እና አባት በሌሎች ዘመዶቿ መደፈር፣ መነ'ሳት እና መጣ'ል የልጅነት ብሩህነቷን ያጣች፣ በኋላ ደግሞ ከተጣለችበት ያነሳትን እና ከሰው እኩል ያናገራትን ባሏን እና የልጅ አባቷን አቶ ኮላሴን ገና በህይወቷ አጋማሽ በድንገት የተመነተፈች ባለክንቱ ህልም ናት፤

> መግደላዊትን ያለ ኮላሴ ከሦስት ወር በለይ መኖሯ እንደጎዳት ገጽዋ ላይ ተጽፎአል፡፡ ይሙት ይኑር ፖሊስ መርምሮ ባደርስበትም [...] ጥቁር ቀሚስ ለብሳለች፡፡ ጥቁር ሻሽ አስራለች፡፡ 'ኩልዬን አልረሳሁትም' ለማለት መኪናው ተበላሽታ የቆመችበት አካባቢ ወንዝ ዳር የተገኘውን መስታወቱ የተሰባበረ የማይሰራ 'ካሲዮ' ኤሌክትሮኒክስ የእጅ ሰዓቱን በቀኝ እጇ ላይ አስራለች፡፡ (አዳም ረታ፣ 2010፤ 245)

ሌላዋ የርእይ መነጠቅ ሰለባ የሆኑት ንዑስ ገፀ ባህሪ ደግሞ የራሚሱ እናት ወይዘሮ መቅረዝ ናቸው፡፡ ወይዘሮ መቅረዝ በመጀመሪያ ደረጃ ልክ እንደ ጌርሳሞት ሁሉ በድንገት እና ለጊዜው ቀላል በመሰለ አደጋ አካላቸውን አጥተዋል፡፡ ይህን የተጎዳ አካላቸውን በህክምና ወደነበረበት ጤናማነት ለመመለስ ያላሰለሰ ጥረት ቢያደርጉም፣ ብዙ ብዙ መስዋዕትነት ቢከፍሉም ሳይሳካላቸው ቀርቶ ዘለአለማዊ በሽተኛ ሆነው አርፈዋል፤

> የአቡ እናት ወይዘሮ መቅረዝ [...] የአንገት በላይ ሃኪም ሆነው አለርት ሆስፒታል ለአስርታት ሰርተዋል፡፡ አንድ ቀን እዛው ሆስፒታል ውስጥ ሊኖሊየም ወለል ላይ የፈሰሰ ዠራራ ቫዝሊን እረግጠው ሲወድቁ የብረት ጠረጴዛ ጠርዝ አገጫቸውን ገጭቷቸው መንጋጋቸው ተሰበረ፡፡ [...] ስብራቱ ሊስተካከልላቸው ስላልቻለ ያለማቋረጥ ለሃጭ ይወርዳቸው ጀመር፡፡ [...] ማስክ ለብሶ መስራት አማሯቸው ስራ አቋርጠው ጡረታ ወጡ፡፡ (አዳም ረታ፣ 2010፤ 145)

ወይዘሮ መቅረዝ ከአካላቸውም ሌላ ለአሠርታት የደከሙለትን እና የሚወዱትን የህክምና ሙያቸውን በዚሁ በአካል ጉዳተኝነታቸው ሳቢያ ባደረባቸው ሥነ ልቦናዊ ቀውስ የህይወት ስንቅ ይሆነኛል ያሉትን ሙያቸውን ሳይወዱ በግድ (ባጋጣሚ ተገደው) አጥተውታል፡፡ ድካማቸው፣ ህልማቸው ሁሉ ከንቱ ሆኗል፤ "ከልጅነታቸው ጀምሮ ከተማሩት የሕክምና ሳይንስ ራቁ፡ ሃያ ስድስት አመታት የተማሩት እና ለሃያ ስድስት አመታት የሰሩበት ሳይንስ የተሰበረአገጫቸውን ሊያድናቸው አልቻለምና ቂም ያዙበት፡፡" (አዳም ረታ፣ 2010፤ *145)*፡፡ ከዚህ አንጻር ጠቅለል ባለ መልኩ ሲገለጽ፣ ወይዘሮ መቅረዝ ወዲህ አካላቸውን (**አፉቸውን**)፣ ጤናቸውን አጥተዋል፣ ወዲህ ደግሞ ሥራቸውን፣ እንጀራቸውን በአደጋ ሰበብ ተቀምተዋል፤ እድሜ ዘመናቸውን ለፍተው ያገኙትን፣ የህይወት ዘመን ራዕያቸው የሆነውን ሙያቸውን እና በሙያቸው ሠርተው የመብላት ርእያቸውን ተነጥቀዋል፡፡

በአጠቃላይ ከፍ ሲል እንደተጠቀመው በ ሓፍ ረጅም ልቦለድ ውስጥ ያሉ ገፀ ባህርያት፤ አንዳንዶቹ በከባድ ህመም፣ አንዳንዶቹ በሞት፣ ሌሎቹ ደግሞ በስደት እና መሰል ምክንያቶች ካለሙት ሳይደርሱ፣ የሳሱለትን ሳይቀምሱ፣ የተመኙትን ሳያሳኩ፣ የፈለጉትን ሣያገኙ ወይም ያገኙትን ሳይጠቀሙ፤ ሃሳባቸው፣ ህልማቸው፣ ምኞታቸው፣ ዕቅዳቸው እውን ሳይሆን ቅዠት ሆኖ የቀረባቸው፤ ስኬትን ጨብጠው ድንገት የለቀቁ፤ ብቅ ያለችላቸው ፀሐይ ድንገት ከመንገድ ላይ እያሉ የጠለቀችባቸው፤ በእጃቸው የያዙትን ሙዳ በቅፅበት በጭልፊት የተመነተፉ፤ በጥቅሉ የተለያዩ ርዕዮቶቻቸውን በተለያየ መጠን እና ሰበብ ያጡ ገፀ ሰዎች ናቸው ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡

## 3.5. ቀቢጸ ተስፋ

ከሁሉ በፊት፣ የህልውናዊነት ጭብጦች በግልጽም ይሁን በህቡዕ የሚዛመዱ እና የሚዋለዱ ከመሆናቸው የተነሳ አንዱ የሌላው መንስኤ ወይም አንዱ የሌላው ውጤት፣ እንዲሁም አንዱ ከሌላው ጎን የተቀረሰ ሊሆን እንደሚችል በምዕራፍ ሁለት ላይ ተነስቷል፡፡ ይህን የህልውናዊነት ጭብጦች ተዋላጅነት እና ተዛማጅነት ቴዎድሮስ ገብሬ (2001)ም ይጋሩታል፡፡ በዚህ መሠረት እንግዲህ፣ ቀቢጸ ተስፋ የሚባለው ህልውናዊ ገጽታ ከአጠቃላይ የማንነት መበጥበጥ ወይም መታወክ ጋር የተገናኘ እንሆነ የነገረህላዌ ልሂቃን ያትታሉ፡፡ እንደ ነገረ ህላዌያን እምነት ሰዎች በህይወታቸው ውስጥ ከራሳቸው ጋር የሚፈጥሩት አለመግባባት ወይም እሰጥ አገባ ከዚሁ ተስፋ መቁረጥ ላይ ያደርሳቸዋል፡፡ ይህ ከራስ ጋር የሚደረግ ግጭት ደግሞ ምንጩ ከምኞት ከንቱነት ወይም ከርእይ መነጠቅ አለፍ ሲልም ከባዶነት ስሜት ባሕር ውስጥ ሊቀዳ ይችላል፡፡

በሐፍ ልቦለድ ውስጥ የምናገኘው ራሚሱ ህልውናውን ሙሉ በርካታ ተግባራትን በነጻነት እንዳከናወነ አልቀረም፤ ይልቁንም የሚከተለው ነጻ አስተሳሰቡ ይዞበት የሚመጣውን ውጤት ሁሉ ብቸኛ ተቋዳሽ ሆነ እንጂ፡፡ ስለሆነም በስተመጨረሻ በዙሪያው ባሉ ነገሮች ሁሉ ተስፋ ቆረጧል፤ ነገር ግን አሁንም ድረስ በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ሆኖም ቢሆን ህይወቱን ይገፋል፡፡ ምናልባትም ከዚህ የተስፋ መቁረጥ አረንቋ ውስጥ የሚያወጣው የጫት እና የመጠጥ ሱሱ ብቻ ነው፡፡ ወደዚህ መደበቂያው (ሱስ) የገባውም ከሚኖርበት ዓለም ውስጥ የሚጠብቀውን በማጣቱ እንጅ መዝናናት ፈልጎ እንዳለሆነ ኦናንነት በተሰኘው ክፍል ውስጥም አንስቻለሁ፡፡

ከዚህ ባለፈ ደግሞ ራሚሱ፣ እንደ እርሱ አባባል እውቀት ሊሰብክ አስቦ "በር" የተባለ መፅሔት ከጓደኞቹ ጋር በአንድነት ያቋቁማል፡፡ ይሁን እንጅ በተለያዩ መንግስታዊ አካላት ተቃውሞ ምክንያት ሃሳቡ እንዳቀደው እውን ሳይሆን ቀርቶ በአንድነት ሊጽፉ የተሰባሰቡት ጓደኞቹ ሁሉ ወደየብትውናቸው ይበተናሉ፡፡ ታዲያ ከዚህ በኋላ የሚሰራው ጠፍቶበት፣ ሞራሉ ሁሉ ወድቆ፣ ብቻ በሁሉም ነገር ተስፋ ቆርጦ በልቦለዱ ታሪክ ውስጥ እናነባለን፡፡ በዚህ ምክንያት በተማረበት የሙያ መስክ ያገኘውን ሥራ እንዳይሰራ እንኳን በዘመኑ ያለው የአሰራር ሥርዓት ሁሉ ያስጠላዋል፤

> አስተማሪነት እንዳልገባ የተማሪ ፊት ያስጠላኛል፡፡ እንደገናስ በበርጫ ያበጠ የጎረምሳ ዐይን ልይ? በርካሽ ጂንስ የፈጠጠ ቂጢን የምታሳይ ልሰልጥን የምትል ቅባታም ባላገር ልይ? እንዴት ነው ጆኒዎች **ዲሞክራሲው** ቄንጥ የለውም እንዴ? የሕልም እንክቱ እንዲህ ይወጣል፡፡ **በደባሪ ጥበባችሁ የተገረፈው ጀርባዬ** አባጣ ጎባጣ አለው፡፡ ባለሁለት እግር ጉንዳን ነኝ ከዳቦ ፍርፋሪ ስር የተጠለልኩ፡፡ የሐሞቴ ቀረጢት በተስፋ መቁረጥ የጫት ጭማቂ ሙሉ ነው፡፡ (አዳም ረታ፣ 2010፤ 171)

ቀደም ባሉት ክፍሎች ስር ባህል፣ ሃይማኖት፣ ህግ፣ ሥርዓት የሚባሉ ጉዳዮች ለራሚሱ ምንም ናቸው ብያለሁ፡፡ በመሆኑም እነዚህ ከጎን ሆኖ የሚያያቸው እና የሚሳለቅባቸው ተግባራት ፋይዳ ቢስ ሆነው ተስፋ አሳጥተውታል፡፡ ከእነዚህ ጉደዮች ውስጥ ሆኖ የልጅነት ጊዜውን ያሳለፈበት መንገድ ብሎም በዚህ ሥርዓት ውስጥ ባሉ ሰዎች መካከል ማደጉ አሳቆታል፡፡ ስለዚህ እንደማይጠቅመው እያወቀም ቢሆን በተስፋ መቁረጥ እራሱን ወደ ሱስ ወርውሮ ጥሏል፡፡ የተማረው ትምህርት የትም እንደማያደርሰው እና ከዚህ ሥርዓት እንደማያስመልጠው ያስባልና **“ደባሪ ጥበብ”** ብሎታል፡፡

ራሚሱ የተማረው ትምህርት ለራሱ፣ ለአገሩ እና ለወገኑ የሚጠቅም እውቀት አይደለም፤ የተለመደ እና ከምንም የማያስጥል ብልሃት ሆኖ አግኝቶታል፡፡ በዚህ አይነት ልምድ ውስጥ እየኖረ በመሆኑ እና ከዚህ አይነት ልማዳዊ ህይወት መውጣት እንደማይችል ስለገባው እራሱን ለመጉዳት ወይም ደግሞ ለጊዜውም ቢሆን ለመደ'በቅ የሱስ ዋሻን ብቸኛ ምርጫው አድርጓል፡፡ በአገሩ ውስጥ ባለው ማህበራዊ እና አስተዳደራዊ ሥርዓት ጥላቻ ብቻም ሳይሆን ከሁሉ ነገር በላቀ ሲናፍቀው እና ሲጓጓለት የኖረውን እንዲሁም የዓለምን ዘበትነት ያስረሳኛል ብሎ ያሰበውን የጌርሳሞትን ፍቅር በተነፈገው ጊዜ ነው ለመጨረሻ ጊዜ የህላዌ ተስፋውን ያጣው፡፡

አሁን በሰው ልጆች ላይ ምንም አይነት ተስፋ የለውም፡፡ ጌርሳም ብትሆን እንዳሰባት ሁሉ ከሌሎቹ የተለየች ሳትሆን ከሌሎቹ ጎራ ናትና ብቸኛ ያደረጋት ተስፋው ፍጹም ከማይመቹት ተራ ተሰልፋ አስጠልታዋለች፡፡ ስለዚህ በስተመጨረሻ በሁሉም የሰው ልጆች እና በአጠቃላይ በሥነ ፍጥረታት ላይ ያለው ተስፋ ሁሉ ባዶ ሆኗል፤ “ጌርሳ ለእኔ ታላቅ ነበረች፡፡ የገባኝ ነገር እሷን ጨምሮ በደደብ መንጋ መከበቤ ነው፡፡ በብልጣብልጦች ነገ-ቢሶች መወረሬ ነው፡፡ ከእነዚህ አይነቶች ጋር አንድ መሬት ተጋርቶ ከመኖር የተነፈሱትን ከመተንፈስ ጫት እየቃምኩ አረንጓዴ ውሃ ብሸና ይሻለኛል፡፡” (አዳም ረታ፣ 2010፤ 187)፡፡

ለራሚሱ ከጌርሳሞት ውጭ ያለ የትኛውም አይነት ሥነ ፍጥረት ከንቱ መሆኑን ቀድሞውንም ያውቃል፡፡ ጌርሳ ግን ያለችው ብቸኛ ማምለኪያው ነበረች፡፡ እንደዚያ የሚያመልክበት የነበረ ውበቷ ሲሰወር ደግሞ የዓለም ውሸትነት ይበልጡኑ ተገልጦለታልና አሁን በሁሉም ነገር ላይ ያለው ጭላንጭል እምነት ሁሉ ተጨልጧል፤ "ጽላቴ መበልሸቱ አሳዘነኝ፡፡ ለመዛጉም አልጨነቅም፡፡ ለእህቴ ይሄው አልጨነቅም፡፡ ከጌርሳ ወዲያ የቀረው ሁሉ እኩል ነው፡፡ ከፍ ዝቅ የለበትም፡፡ ሰርታታዋ ታቦት ማደሪያ ሆይ ጤና እደሪ!" (አዳም ረታ፣ 2010፤ 188)፡፡ የጌርሳ ውበት መሰወር ሁለት ስለት ያለው ሰይፍ ነው፡፡ አንዱ ወገን እንህዲህ የራሚሱን የህልም ዓለም በጥሷል፤ በሌላው ጎኑ ደግሞ የራሷን የውበቷን ባለቤት የጌርሳሞትን በራስ የመተማመን እና ህልውናን ሙሉ ደምቆ የመታየት የተስፋ ገመድ አሳጥሯል፡፡

ጌርሳሞት፣ የሁሉ ነገሯ ድምቀት የነበሩትን ከናፍሮቿን ስታጣ ከሌሎች ሰዎች ጋር ለመገናኘት እንኳን ድፍረት አጥታለች፤ ከጓደኛዋ ከፌቨን ሳይቀር፡፡ እንደዚያ የሙሉ ውበቷ ነጸብራቆች እንደነበሩ ታውቃለችና አሁን ደግሞ ያልነበረ ቅርፅ እና መልካቸውን ይዛ ለመውጣት ተሸማቃለች፡፡ በእነዛ ከናፍሮቿ ላይ የነበራት እምነት ተሟጧል፡፡ አሁን ከውበቷ ተነጥላ እጣዋ በተስፋ የለሽ ሃሳብ መናወዝ ብቻ ሆኗል፡፡

> በትካዜ ወደ ሱቁ ውጭ ታያለች፡፡ ሁልጊዜ የሚከባት የተለያዩ አበቦች ጠረን አሁንም አለ፡፡ አሰፋፈሩ የተለየ ነው፡፡ በእሷ እና በዓለም መሃል ነው፡፡ አለም ፊት ለፊቷ እንደ ቪዲዮ ስዕል ከግራ ወደ ቀኝ ከቀኝ ወደ ግራ ይተረተራል፡፡ እዚህ ስትገባ ይቅበጠበጥ የነበረው የነሐሴ ደመና ወደሚሄድበት ሄዷል፡፡ (አዳም ረታ፣ 2010፤ *229)*

ጌርሳሞት በውበቷ ያጠመደቻቸውን አፍቃሪዎቿን፣ ጠያቂዎቿን፣ ናፋቂዎቿን አለፍ ሲልም ውበቷን እራሱን አጥታ ትካዜን ብቻ የሙጥኝ ብላለች፡፡ እንደዚህ አይነቱ የህልውና ገጽታ ደግሞ፣ ሰዎች በህይወት ዘመናቸው ውስጥ እርግጠኛ የሆኑባቸው ነገሮች ሲወድሙ አሊያም ሲፈራርሱ እና በነገሮች ላይ እርግጠኛነታቸውን ሲያጡ ወደ ተስፋ መቁረጥ ይገባሉ የሚለውን የTan (2007)ን ማብራሪያ ያስታውሰናል፡፡ እንደ Tan ሃሳብ የሰዎች ተስፋ ቢስነት በእለት ከእለት ህላዌያቸው ውስጥ ከሚያጋጥሟቸው ያልተጠበቁ ነገሮች ይመነጫል፡፡ ከዚህ አንጻር ጌርሳሞት፣ በውበት ላይ ሌላ ውበት፣ በመልክ ላይ ሌላ መልክ ለመጨመር እንጅ የነበረውን ቁንጅናዋን ለማጣት አልነበረም ብሬስ የተሰራችው፡፡ ነገር ግን ፈጽሞ ባልጠበቀችው ሁኔታ ውበቷን እና ጤንነቷን ተነጥቃለች፡፡ አሁን ድሮ

የነበሩትን አፍቃሪዎቿን እንኳን ብታገኛቸው አትወድም፤ አለኝ ያለችው፣ መመኪያዋ የነበረው የውበቷ ድንገት መጥፋት ተስፋዋን እና በራስ መተማመኗን ጨምሮ ይዞት ገደል ገብቷል፤ "ጌርሳሞት በሃሳቧ ነጭ ክፍል ውስጥ ነጭ አንሶላ ስር በፋሻ ታስሮ፣ ግንባሩ በፕላስተር ተሸፍኖ፣ የከሳ፣ የጠቆረ፣ በጀርባው የተዘረረ ባካፋ ይታያታል፡፡ እሱን ለመጠየቅ የምትሄድበት ምክንያት የለም፡፡ በፍቅር አፍጦ የሚያየው አፏን አበላሽታለች፡፡" (አዳም ረታ፣ 2010፤ 231)፡፡ ስለዚህ ተስፋዋ ትካዜ፣ ሃሳብ ብቻ እንጅ አሁን አንዳችም ተስፋ የላትም፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ የአቡ እናት ወይዘሮ መቅረዝ፣ የእድሜያቸውን ግማሽ ተምረው የተሰማሩበትን ዘመናዊ የህክምና ሙያ ትተው ወደ ባህላዊ የህክምና ጥበብ ፊታቸውን አዙረዋል፡፡ ወይዘሮ መቅረዝ ከአንገት በላይ እስፔሻሊስት ሆነው ለአሥርታት ቢሰሩም የዘመናዊ ህክምና የእርሳቸውን የአፍ ህመም ማዳን እንደማይችል ሲረዱ ተስፋ ቆርጠው ትተውታል፡፡ ከእርሳቸው አልፎ ለሌሎቹ ዋስትና ይሆናል ብለው ተስፋ የጣሉበት፣ ለየትኛውም በሽታ ፈውስ በመስጠት አጭር ህይወትን ሊያስቀጥሉ የተማሩት የዘመናዊ ህክምና ሙያ የእርሳቸውን ጤና መመለስ ሲሳነው የጣሉበትን እምነት እና ተስፋ በልቷልና ወደ ሌላ ጥበብ ተሻግረዋል፡፡ ከዚህም አልፎ በተስፋ መቁረጥ እራሳቸውን ጥለዋል፤ "ከጥቂት አመታት በፊት ፀጉሯን ትተኮስ ነበር፡፡ አሁን አሁን አየር የማያስገባ ስፌት የመሰለ የጉንጉን አይነት ትሰራለች፡፡ ከሳይንሳዊው አለም እርቃ አገራዊ መድሃኒተኛ መሆኗ ለእኔ ለመጀመሪያ አድናቂዋ ከብዶኛል" (አዳም ረታ፣ 2010፤ 150)፡፡

በተጨማሪም የጌርሳሞት እናት መግደላዊት የባሏን እና የጌርሳን አባት አቶ ኮላሴን በድንገት ወጥቶ መቅረት ከሞት ጋር በማያያዝ ተስፋ ቆርጣ በቤታቸው ውስጥ ታላቅ የሃዘን ድባብ እንዳጠላ እና እርሷም አልበሳቷ በሙሉ የሃዘን ልብስ መሆን እንደጀመረ ታሪኩ ያወሳል (አዳም ረታ፣ 2010፤ *245-246*)፡፡ እንደዚህ አይነቱን ተስፋ ቢስነት ደግሞ Sartre፣ ሰዎች በህይወታቸው ውስጥ ለሚወስኑት ውሳኔ ዋስትና ማጣት ወይም ስለወደፊቱ ህይወታቸው ብሩህነት እርግጠኛ አለመሆን ነው እንደሚሉት Tan (2007) ያስረዳሉ፡፡

ወይዘሮ መግደላዊት፣ እርሷ በቻለችው አቅም ከዛሬ ነገ ይመጣል በሚል ከንቱ ተስፋ መጠበቅ ከጀመረች ሦስት ወራት ተቆጥረዋል፤ ይሁን እንጅ የአቶ ኮላሴ ኮቴ ይባሱኑ እየራቀ ሲሄድ በሃሳቧ ይመጣ ጀምሯል፡፡ ተስፋ የተጣለበት የፖሊስ ምርመራም ስለኮላሴ

አዲስ ነገር ብርቅ ሆኖበታል፡፡ ስለሆነም በስተመጨረሻ በቤት ውስጥ ምንም አይነት ሙዚቃ እንዳይከፈት ብሎም ነጭ ልብስ እንዳይለበስ መከልከሏን ተያይዛዋለች፡፡ ምክንያቱ ደግሞ እንደ እርሷ እምነት አቶ ኮላሴ በህይወት የለምና ነው፤

> ይሙት ይኑር ፖሊስ መርምሮ ባይደርስበትም ተስፋ ቆርጣ ቢሞት ነው ብላ አንደኛውኑ ጥቁር ቀሚስ ለብሳለች፣ ጥቁር ሻሽ አስራለች፡፡ [...] ጌርሳሞት ከነገ ወዲያ ወደ ሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ ለመሄድ በሻንጣዋ ከምትከተው ልብስ አንድ እንኳን ጥቁር የለበትም፡፡ መግደላዊት እህል እያሰጣች ለብቻዋ ግን ሌሎች እንዲሰሙ አድርጋ ታወራለች፡ 'አሁን ይህን የቻይና ቅራቅንቦሽን ሰብስበሽ ሄድሽና' ….. 'ይገርማል …..'"እባክሽ አንቺ ልጅ ሰውም አታከብሪ ይህን ዘፈን ዝጊልኝ' 'በየትም አገር ወላጅ ይከበራል እኔ ቤት ብቻ እንጂ፣ [...]' (አዳም ረታ፣ 2010፤ 245-246)

በሌላ በኩል ደግሞ ገለታ፣ በአገሩ ውስጥ ያለው እና በየትኛውም ቦታ የተሰራጨው የምን አገባኝነት ስሜት እና ስር የሰደደ ድንቁርና ተስፋ አስቆርጦት ወደ ውጭ እንዲሰደድ ምክንያት እንደሆነው የልቦለዱ ታሪክ ያትታል፡፡ ገለታ ይህ በአገሩ ላይ የተንሰራፋ ጭፍን የሆነ የሰዎች እውቀት እና አስተሳሰብ መቼውንም ቢሆን ይቀረፋል የሚል ተስፋ አላደረበትምና ሽሽትን፣ ስደትን መርጧል፤ "ከቆመበት ትንሽ ቦታ ጀምሮ እስከዛ አድማስ ድረስሊዋጋው የማይችል ስር የሰደደ ድንቁርና እንደሰፈረ ሲገባው አፉን ለክርክር ሳይከፈት መታዘቡን ቀጠለ፡፡ ይህንን በዝምታ መከታተል ስላደከመው ከዚህ አገር መሸሽ ነበረበት፡፡ [...] ከአገር ወጣ፡፡" (አዳም ረታ፣ 2010፤ 65-66)፡፡

በተጨማሪም የገለታን መንገድ ዳር ሞቶ የመገኘት ጉዳይ እዲያጣራ የታዘዘው ደቡብ አፍሪካዊው ፖሊስ "ሰርጀንት" (መቶ አለቃ) ዴላኒ በአገሩ ደቡብ አፍሪካ ውስጥ የዴሞክራሲ፣ የሠላም፣ የብልጽግና እና የእኩልነት አዎንታዊ ልዋጤ መኖሩን በሰዎች፣ በጋዜጦች፣ በመጽሔቶች፣ በሬዲዮ፣ በቴሌቭዥን በአጠቃላይ በብዙሃን መገናኛዎች ሁሉ ሲሰማ ከእውነታ የራቀ ሆኖ በእጅጉ እንዳሰላቸው የልቦለዱ ታሪክ ያወሳል፡፡ ምክንያቱም አገሪቱን የሚያዝዛት ገንዘብ እና ወንጀል እንደሆነ አሳምሮ ያውቃልና፤ ዴላኒ በእነዚህ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ዙሪያ ከእራሱ በላይ ምንም አይነት ምስክር አያሻውም፡፡ በአገሪቱ ውስጥ የሚፈጸሙት ቁጥር ስፍር የሌላቸው ውስብስብ ወንጀሎችን ሙያው አስተዋውቆታል፡፡ በስተመጨረሻም እነዚህ በመዓልትም ሆነ በሌሊት በሥራው ላይ በተደጋጋሚ የሚያጋጥሙት በርካታ ቁጥር ያላቸው ውስብስብ ወንጀሎች ተስፋ አስቆርጠውታል፡፡ ህይወቱን ለማቆየት ብቻ ሲል ሥራውን መሥራቱን ይቀጥል እንጅ

የአገሩ የፖለቲካ ሽፋን እና እውናዊው ሁነት አልጣጣም ብሎት በህላዌው ሲሰላች እና ተስፋ ቢስ ሲሆን እንታዘባለን፤

> *የሚገባው ነገር የየቀኑ ሕይወቱ በሽብር መሞላቱ ነው፡፡* [...] *የሚበላው ቢያገኝ* ***ድንጋይ*** *እንኳን ቢሆንና ቢስማማው ስራውን ትቶ እሱን* ***እየቆረጠመ*** *በርሃ ለብቻው ለመኖር ይሰደዳል፡፡ ሞቱ ከደረሰ እንቅልፍ ሲወስደው ቢሆን ይመርጣል፡፡ አሁን እንደሚሆን ቢረዳ* ***ቢሞት ቅር አይለውም፡፡*** (አዳም ረታ፣ 2010፤ *208 አጽንኦት ተጨምሮበታል)፡፡*

*በየቀኑ የሚያጋጥመው የወንጀል መዓት በህይወቱ ውስጥ ተስፋ አስቆርጦታልና ብቸኛ የበርሃ መራር ሕይወትን፣ ሲከፋም ሞቱን አስመኝቶታል፡፡ ዴላኒ፣ በርካታ ቁጥር ያላቸውን ውስብስብ ወንጀሎች እና ወንጀለኞች በአለቆቹ ተፅዛዝ መሠረት በማሳደድ በተደጋጋሚ ከቁጥጥር ስር እንዲውሉ ቢያደርግም በስልታዊ የውሸት ጭምብል በመሸፋፈን እራሱኑ መልሰው እንደወንጀለኛ እየቆጠሩ ሚያደርሱበትን ጭቆና እና በደል ሲያስብ መሸከም ያቅተውና በሃሳብ ብቻ ይናውዛል፡፡ ይህን መሰሉን የግፈኞች ከባድ ቀንበር ለመሸከም የዴላኒ ትከሻ አቅም አነሰው፡፡*

*በመጨረሻም የወንጀለኞችን ርዕዮተዓለም ከነጭራሹ ማምከን ከቶውንም የማይታሰብ እንደሆነ በመገንዘብ ትክክለኛውን የወንጀል ማነፍነፍ ሥራውን እርግፍ አድርጎ ለመተው ተገዷል፡፡ በአገሩ ውስጥ ወንጀል ተሸጋጋሪ እና ምንም አይነት ቀኖና ሊገድበው የማይችል ተግባር መሆኑ ገብቶታል፡፡ ስለዚህ ወንጀልን የመታገል ራዕዩ መቼውንም የማይፈጸም ትንቢት ሆኖበት ባይመቸውም በዘመኑ ባህሪ ውስጥ እራሱን ደብቆ ለመኖር ወስኗል፤ የወንጀል ድርጊትን እስከ መጨረሻው ድረስ የማድረቅ ተስፋው ተሟጧል፡፡ "ሕግ ጠባቂ ቢሆንም ሕግ እራሱን አይጠብቀውም፤* [...] *አስከፊ ሆነ አልሆነ የወንጀለኞቹን ባህርይ ሁሉም ሰው በቀላሉ የሚገለብጠው እና የዘላለማዊነት ተስፋ ያለው ነው፡፡ እና ወንጀለኞችን ላጥፋ ማለት አጉል ህልም ነው፡፡ ዴላኒ መሞከር ካቆመ ሰነበተ፡፡"* (አዳም ረታ፣ 2010፤ *209)፡፡*

# ምዕራፍ አራት

## ማጠቃለያ

ይህ ጥናት፣ የነገረህላዌ ፍልስፍናን መሠረት በማድረግ በሖፍ ረጅም ልቦለድ ውስጥ የተንፀባረቁ እና ጎልተው የወጡ የህልውናዊነት ጭብጣዊ ጉዳዮችን በመለየት እና ተንትኖ በማሳየት ለምርምር የተመረጠው ልቦለድ ከነገረህላዌ ፍልስፍና ጋር ያለውን ግንኙነት ለመመርመር የተደረገ ሙከራ ነው፡፡ ይህንን ለማድረግ ያነሳሳው ዋነኛው ምክንያት ደግሞ የልቦለዱን ብሎም በልቦለዱ ናሙናነት አጠቃላዩን የአማርኛ ሥነ ጽሑፍን እና የሰው ልጅ የህልውና ፍልስፍናን ተዛምዶ ለመግለጥ መሻት ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር ደግሞ ይህ ጥናት ከላይ የተቀመጠውን ዓብይ ዓላማ ለማሳካት ማለትም በዚሁ የልቦለድ ሥራ ውስጥ የተንፀባረቁ የህልውናዊነት ጭብጦችን በመለየት እና ተንትኖ በማሳየት ከነገረህላዌ ፍልስፍና ጋር ያለውን ዝምድና ለመግለጥ፣ እራሱን የነገረህላዌ ፍልስፍናን (ንድፈሃሳብን) ለተመረጠው ልቦለድ መተርጎሚያነት ተጠቅሟል፡፡ በዚህም መሠረት በዚህ ጥናት ለምርምር በተመረጠው ሖፍ ረጅም ልቦለድ ውስጥ ተንፀባርቀዋል ተብለው የታመነባቸው አምስት ያህል የህልውናዊነት ጭብጦች ተለይተው እና በስፋት ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

በዚህ ጥናት ለትንተና በተመረጠው ሖፍ ረጅም ልቦለድ ውስጥ የሚገኙትን ከዓበይት እስከ ንዑሳን ገፀ ባህርያት እንዳስፈላጊነቱ በመውሰድ፣ ዓለማዊ ኑባሬያቸው ምን እንደሚመስል እና በህይወታቸው ውስጥ ያለፉባቸው ገናን የህላዌ ክስተቶች የትኞቹ እንደሆኑ በመፈተሽ ነው የህልውናዊነት ጭብጦቹ ተለይተው እና ተተንትነው የቀረቡት፡፡ በዚህም መሠረት በዚህ ልቦለድ ከተቀረጹት ገፀ ባህርያት መካከል አንዳንዶቹ በነጻነት የሚቦርቁ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ከዚህ በተቃራኒ የህላዌ እስትንፋሳቸው ሁሉ በሌሎች ማህበራዊ እና ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች የተሸበበባቸው የቁም እስረኞች ሆነው እናስተውላለን፡፡ ስለሆነም በዚህ ልቦለድ ውስጥ ነጻነት እና ኃላፊነት ከነጻነት እጦት ጋር ፊት ለፊት ተገልጸው ይገኛሉ፡፡ ይህ የህላዌ ሁነት ደግሞ በሁለቱ ዓበይት ገፀ ባህርያት ማለትም በራሚሱ (አቡ) እና በጌርሳሞት ላይ በስፋት የሚስተዋል ሲሆን፣ በአንደኛው ጽንፍ ራሚሱ ከምንም አይነት ማህበራዊም ሆነ ሃይማኖታዊ ሥርዓት ውጭ ሆኖ ተገልጧል፡፡ ስለሆነም እራሱ ባመነው እና ባሰበው ልክ ራሱን የሚመራ ፍፁም ነጻ ገፀ ባህሪ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

ራሚሱ በእያንዳንዱ የነጻነት ህላዌው ውስጥ የሚመጣበትን ኃላፊነትም ለመሸከም ትክሻውን ቀድሞ ያደነደነ ገፀ ባህሪ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት ራሚሱ ነፃ እና የራሱን ዓለም፣ የራሱን ማንነት፣ በጥቅሉ ራሱን በራሱ የፈጠረ ገፀ ባህሪ ነው፡፡ የትኛውንም አይነት ደንባዊ ሥርዓት ከመቃወም እና ከዚህ ሥርዓት እራሱን ከማራቅ ባለፈ ስርዓቱን ሊቀይረው ባይችልም፤ የእራሱን ህልውና ፈጥሮ በራሱ አቅጣጫ ሲጓዝ እና ከማንም ጣልቃ ነጻ የሆነ ህላዌን ግን ሲመራ እንታዘባለን፡፡ ስለዚህ ነጻ (Free) ገፀ ሰብ የሚል ትርጓሜ ተሰጥቶታል፡፡ ከዚህ በተቃራኒው ደግሞ ወዲህ በማህበረባህሉ ወግ፣ ወዲህ በሃይማኖታዊ አስተምህሮው፣ ወዲህ ደግሞ በቤተሰባዊ ደንብ እና ሥርዓቱ በሦስት በአራት ገመድ የታሰረችውን ጌርሳሞትን እናገኛለን፡፡ ከዚህ አንጻር ነጻነት ይሉት ነገር ለጌርሳሞት የሚታለም እንጅ የሚደረስበት አልሆን እንዳላት በተደጋጋሚ እናስተውላለን፡፡

ጌርሳሞት፣ ሁለንተናዊ ህይወቷን አይደለም፤ የምትለብሳቸውን አልባሳት ሁሉ የማህበረሰቧ ብሎም የቤተሰቧ ህግ አስቀምጦላታል፡፡ ከዚህ ህግ የምታመልጥበት ደግሞ አንዳችም ቀዳዳ የለም፡፡ የማምለጫ መንገዱ ሁሉ በቤተሰቦቿ ግልምጫ እና ማስፈራሪያ ብሎም በማህበረሰቡ ይሉኝታ የተዘጋ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ጌርሳሞት በተከለለላት አጥር ስር ብቻ ተወስና የምትኖር እንስት ገፀ ሰብዕ ሆናለች፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የራሚሱ ገደብ አልባ ነጻነት በህይወቱ ውስጥ መመኪያ፣ መጠለያ፣ ተስፋ መጣያ እንዲያጣ ምክንያት ሲሆነው እና ህልውናው ባዶ (ኦና) ሲሆን ተመልክተናል፡፡ ራሚሱ በየትኛውም አይነት ሃይማኖታዊም ሆነ ባህላዊ ሥርዓት የሚያምን አይደለምና በስተመጨረሻ በዙሪያው ያሉትን ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ተግባራትን፣ አለፍ ሲልም ሥነ ፍጥረታትን ሁሉ ይጠላል (ራሱንም ጨምሮ)፡፡ ስለዚህ የመጨሻ ዕጣው ትርጉም አልባ ህልውናን መምራት እና ከማንም እና ከምንም ነገር ውጭ የሆነ ኑባሬን መከተል ሆኗል፡፡ እናም ለዚህ አይነቱ ኑባሬው የህልውና ኦናነት የሚል ትርጓሜ ተሰጥቶታል፡፡

በሐፍ ልቦለድ ውስጥ የውህድ ማንነት፣ የድብልቅ ባህርያት ባለቤቱ የጌርሳሞት አባት አቶ ኮላሴ ደግሞ የሁኔታዊነትን ጽንሰ ሃሳብ የሚያጎላ ገፀ ባህሪ ነው፡፡ አቶ ኮላሴ በተፈጥሮው ዝንጀሮ ሆኖ የተወለደ በኋላ ግን በኑረቱ ሁኔታ ምክንያት ሰው የሆነ ሰውም፣ ዝንጀሮም፣

ሁለቱንም የሆነ ምትሃታዊ ተፈጥሮ ነው፡፡ ይኸውም በዚህ ጥናት ውስጥ የህልውና ሁኔታዊነት የሚል ፍቺ ይዟል፡፡

ኮላሴ በህይወት ዘመኑ ውስጥ የሰዎችንም፣ የዝንጀሮችንም ተግባራት በጥምረት ይፈጽማል፡፡ እንደሰው፣ ጋዜጣ ማንበብ እና ስቴዲዮም ገብቶ ኳስ መመልከት የሚያዘወትር፣ በመኪና ማሽከርከር የሙያ መስክ ተሰማርቶ መሰረታዊ ህላዌውን የሚመራ፣ አለፍ ሲል ደግሞ ከወየዘሮ መግደላዊት ጋር ትዳር በመመስረት ጌርሳን የመሰለች ተወዳጅ ልጅ የወለደ እና ሌላም፣ ሌላም በርካታ ሰዋዊ ተግባራቶችን እና ሁነቶችን የሚፈጽም ገፀ ባህሪ ነው፡፡ እንደ ዝንጀሮ ደግሞ አመጋገቡ ጥሬ ሰላጣ እና ጎመን ፣ ባህሪው ደግሞ ተደባዳቢ እና ብጥብጥ የሚቀናው፣ በተግባሩ ደግሞ ከዛፍ ዛፍ፣ ከገደል ገደል በቀላሉ መዝለል የሚችል ተዓምራዊ ፍጡር ነው፡፡

ከአቶ ኮላሴ ሌላ ግን ራሚሱም ፍጹም ከሆነው ነጻነቱ ጀርባ አንዳንድ ሁኔታዊ የህልውና ተግባራትን ሲፈፅም እንታዘባለን፡፡ እንደ ነገረህላዌያን እምነት ማንኛውም ሰው ምንም ያክል ነጻ ቢሆንም ከሚኖርበት ማህበረሰብ የሚቀስመው ኑረት አይጠፋምና፤ ራሚሱ በጥቂቱም ቢሆን ማስመሰልን፣ ለሰው ሲሉ መኖርን በዙሪያው ካሉ ሌሎች ማህበረሰቦች ወርሷል፡፡

በአፍ ልቦለድ ውስጥ ትልቁን እና ዋናውን ሃሳብ የሚሸፍነው ህልውናዊ ጉዳይ የርእይ መነጠቅ ነው፡፡ መጠኑ ይለያይ እንጅ ከዚህ ልቦለድ ውስጥ በዚህ የህልውና ገጽታ የማያልፍ ገፀ ባህሪ አለ ማለት አይቻልም፡፡ ይልቁንም ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ገፀ ባህርያቱ ከሞላ ጎደል ርእያቸውን በተለያዩ ምክንያቶች ያጡ ናቸው፡፡ በዚህ መሠረት ከዋና ገፀ ባህርያት ብንነሳ እንኳን፤ ገለታ፣ ባካፋ፣ ዘሪሁን እና ራሚሱ ቢያንስ ሁሉንም አንድ የሚያደርጋቸውን የጌርሳን ፍቅር በተለያዩ ወቅቶች እና ምክንያቶች አጥተዋል፤ ጌርሳሞትም የእነርሱን ፍቅር እንደዚሁ፡፡ ከዚህ ባሻገር ግን ገለታ ውጭ አገር ሄዶ በድሎት ለመኖር ያለመውን ህልም በሞት ተነጥቋል፡፡ ባካፋ ደግሞ ከኬንያ ባመጣው የምግብ መመረዝ እና ሌሎች ተደራራቢ በሽታዎች ሳቢያ ጤናውን አጥቷል፡፡ ጌርሳሞትም ብትሆን ከእነዚህ አራት አብሮ አደጎች ፍቅር በተጨማሪ የአፏን ውበት እና ጤናዋን እንዲሁም አባቷን በድንገት ተነጥቃለች፡፡

ወደ ንዑሳን ገፀ ባህርያት ስንመጣ ደግሞ የጌርሳ እናት መግደላዊት፣ ባሏን አቶ ኮላሴን በገድንገት አጥታለች፡፡ እንደዚሁም የአቡ እናት ወይዘሮ መቅረዝ እንደጌርሳሞት ሁሉ የአፏን ጤንነት ብሎም የረጅም ጊዜ የልፋት ውጤቷ የሆነውን ሥራዋን በድንገት ለቃለች፡፡ በተጨማሪም የገለታ እናት ወይዘሮ ፎርቱና፣ በልጃቸው ገለታ መጥፋት አለኝታቸውን፣ የወደፊት ምርኩዛቸውን ተነጥቀዋል፡፡

በመጨረሻም ከዚህ በላይ ርእያቸውን የተነጠቁ ገፀ ባህርያት በህይወታቸው እና በተለያዩ ሁነቶች ተስፋ ይቆርጣሉ፡፡ የያዙት ሲያመልጣቸው፣ የጨበጡት ሲወድቅ፣ በአንድ በኩል የያዙት በሌላ በኩል ሲፈስባቸው፣ እርግጠኛ የሆኑባቸው ጉዳዮች ድንገት ከአጠገባቸው ሲሰወሩባቸው፣ ተስፋ የጣሉባቸው ዕምነታቸውን ሲያጎድሉባቸው፣ የሰጧቸውን አደራ ሲበሉባቸው ወዘተ ወዘተ በህላዌያቸው ተሰላችተዋል፤ ተማረዋል፤ በስተመጨረሻም ተስፋ ቢስ ሆነዋል፡፡

ጌርሳሞት በከንፈሯ መበላሸት እና በአፏ ቁስለት ምክንያት የወደፊት ጤንነቷ ብሎም የደም ግባቷ ነገር ተስፋ የምታሳድርበት አልሆን ብሏታል፤ ተስፋዋ ተሟጧል፤ በራስ መተማመኗን ሁሉ አጥፍቶባታል፡፡ ወይዘሮ መቅረዝም እንደዚሁ የነበረው ጤናዋ እንደማይመለስ ታውቃለችና፤ ዘመናዊ የህክምና ሙያዋን ትታ ወደ ባህል መድሃኒት ቅመማ ፊቷን መልሳለች፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ራሚሱ፣ ለመተዳደሪያ ብሎም ለእውቀት እና ስልጣኔ መስበኪያ ያሰበው "በር" መጽሔት በመንግስታዊ አካላት አማካኝነት ሲታገድበት ተስፋ በመቁረጥ ከሌላ ሥራ፣ ከሰብዓዊ ፍጡር እና ከሌሎችም ሥነ ፍጥረታት ሁሉ እራሱን አርቆ የጫት ጓደኛ ብቻ አበጅቷል፡፡ ገለታንም ቢሆን ለስደት የዳረገው በአካባቢው ባለው ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ሥርዓት ተስፋ መቁረጡ ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በአገሩ የፖለቲካ ሥርዓት በእጅጉ የተማረረው እና በዚሁ ጉዳይ ተስፋ የቆረጠው ሌላው ገፀ ሰብዕ ደግሞ ደቡብ አፍሪካዊው ፖሊስ ሰርጀንት ዴላኒ ነው፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ጥናት፣ በሰፍ ረጅም ልቦለድ ውስጥ የተንጸባረቁ እና ጎልተው የወጡ ህልውናዊ ጉዳዮች ማለትም ነጻነት እና ኃላፊነት፣ ኦናነት፣ ሁኔታዊነት፣ የርእይ መነጠቅ እና ቀቢጸ ተስፋ የሚሉት የህልውናዊነት ጭብጦች ተለይተው እና በስፋት ተተንትነው ቀርበውበታል ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች


መሠለች ተሻገር፡፡ (2010)፡፡ “የሰው ልጅ ህልውና በቅበላ እና ኩርቢት ድርሰቶች፤ ነገረህልዌ ንባብ”፡፡ (የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ)፡፡ ባሕር ዳር፤ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡

ሰብለ ወልደኪዳን፡፡ (2009)፡፡ “የእኔነት ሐተታ በተመረጡ የአማርኛ ረጅም ልቦለዶች”፡፡ (የፒ.ኤች.ዲ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ)፡፡ አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ብሌን፡፡ (2007)፡፡ *የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር የሥነ ጽሑፍ መጽሔት፡፡* ቅ.8፣ ቁ.2 (ነሐሴ2007) አዲስ አበባ፤ ኤክሊፕስ ማተሚያ ድርጅት ኢ.ደማ፡፡

ቴዎድሮስ ገብሬ፡፡ (2001)፡፡ *በይነዲሲፕሊናዊ የሥነ ጽሑፍ ንባብ፡፡* አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲፕረስ፡፡

አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡፡ (1948)፡፡ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፡፡* አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡አዳም ረታ፡፡ (2010)፡፡ *አፍ፡፡* አዲስ አበባ፤ ሃሳብ አሳታሚ፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡ (2009)፡፡ *የሥነ ጽሑፍ መሰረታውያን፡፡* አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያድርጅት፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ መጽሐፍ ቅዱስ፡፡ (2000)፡፡ *መጽሐፍ ቅዱስ የብሉይ እና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት፡፡* አዲስ አበባ፤ የኢ.ተዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር፡፡

Aklilu Dessaegn. (2010). “Existentialism in the Selected Creative Works of AdamReta”.(M.A thesis).Addis Ababa; Addis Ababa University.

Azhar, I. (2013). “A Critical Study of Existentialistic View of Education and Its Relevance to Human Existebce and Progress. (PHD Thesis) Aligarh (India).Aligarh Muslim University.

Baskaya, D(B). (2011). "At the Junction of Existentialism and Skepticism''. (PHD thesis). Middle East Technical Univresity.

Blea, S. (2014). "What is Existentialism? A Revision of Contemporary Definitions".*STUDIA UBB. PHI LOSOPHIA* Vol,59 (2014). No2; PP.63-72.

Castle, G. (2007). *The Blackwell Guide To Literary Theory.* Blackwell Publishing Ltd

Chiusaroli, M. (2007). "An Existentialist Interpretation of Four Novels by Alberto Moravia".(Thesis). Peace University.

Cole B.A., M G. (1975). "Existentialism and Selected Contemporary Novels In English". (M.A Thesis). Momaster University. Hmilton, Ontario.

Daigle, C. (2010). *Jean-Paul Sartre.* London and New York: Routledge; Taylor and Francis Group.

Dreyfus, H. and Wrathall, M.(eds). (2006). *A companion to phenomonology and Existentialism.*Australia: Blackwell Publishing Ltd.

Flynn, T. (2006). *Existentialism: A Very Short Introduction.* New York: Oxford University Press.

Hornby, A S. (2006). *Oxford Advanced Learner's. Dictionary of Current English.*Seventhedition. New York: Oxford University Press.

Hua Zhang, S.H. (2017). "Existential interpretation of Isabel Archer in The PortraitOf a lady".3rd International Cnference on Economics, Social scince, Art, Education and Management Enginering (ESSAEME 2017).*Advances in Social scince, Education and Humanities research,*Vol.19.

Kearny, k. (1988). *The Wake of Imagination: Towards a Postmodern Culture.* London: Century Hutchinson Ltd.

Mallah, J.A. (2016). “Historical Roots and Basic Themes of Existential Philosophy: An Analysis”. Pune Research World ISSAN 2455-359x: *An International journal of Interdisciplinary studies,* Vol. 1, Issue. 2.

Mart, C. (2012). “Existentialism in Two Plays of Jean-Paul Sartre”.*Accedemic Journals: Journal of English and Literature;* Vol. 3(3), 50-54.

Marwood, L. (2016). “Existentialism and Postwar German Language Writing”.(PHD Thesis). London kings college.

Maxwell, U.D. (2014). “Migration, Disillusionment and Diasporic Experiences in Segun Afolabi’s Goodbye Lucille and A life Elsewhere”. *InternalJournal of English and Literature;* vol.5 (9), PP. 250-256.

Michelman, S. (2008). *Historical Dictionary of Existentialism.*United Stats of America: Scarecrow Press Ltd.

Mobini, M. and Salim Pour, M. (2016). *International Academic Journal of Humanities.*Vol.3, No. 8,2016. Pp. 81-89.

More, V. (2016). “A Philosophic Standpoint to Existence over Essence”. TheSouth Asian Acadamic Research Chironicle ISSN 2454-1109 :*Apeer Reviewed Refereed and endexed International Interdisciplinary open Access monthly e-Journal.*

Ogundipe, O. (2014). “From Utopia to Nightmare: A Ntional Dissillusionment inthe contemporary Nigerian Novel”. (PHD Thesis).University of Alberta.

Okuune, S.T and Timothy, A.E. (2007). "Despair and Disillusionment in Post-Negritude African Literature".*English Language, literature and culture*, vol.2, No.5,2007, PP.45-51.

Ranney, D. J. (1938). "What is literature? An attempt at a philosophicalDeffinition". (M.A Thesis). Loyola University.

Solomon, C. R. (1988). *Living with Nietzsche: What a Great "Immoralist" Has to Teach Us.* New York: Oxford University Press, Inc.

_________.(2005). *Existentialism* (2nd Ed). New York: Oxford University Press.

Tan, T. (2007). "Existentialism and Samuel Becket's Two plays: Endgame and Happy Day". (M.A Thesis). Middle east Technical Univrsity.

Taye Asefa and Shiferaw Bkele. (2000). "The study of Amharic Literature: an overview". *Journal of Ethiopian Studies,* vol. 33, No. 2, Special Issue Dediacated to the XIVTH international confrence of Ethiopianstudies, PP. 27-33. Institute of Ethiopian Studies.

Tsedey Wondimu. (2007). "The Case of Existence in *Fikr Eske Mekabir, KadmasBashager* and *Giracha Qacheloch*: From Existentialists Perspective".(M.A Thesis). Addis Ababa University.

Webber, J. (2009). *The Existentialism of Jean- Paul Sartre.* New York: RoutledgeTylor and Francies Group.

Wirahai, U. (2008). "The Existentialism Studies on Daniel Defoe's Robinson Crusoe's Freedom of life". Thesis The degree of Sarjana Sastra (S.S). The State Islamic University of Malang.

Wolcot, H.F. (1992). “Posturing in qualitative Research: In MDLE Compet, W.L, Millroy & J. Preissle” (eds). *The Handbook of Qualitative Researchin Education.* Sandiago: Accedemic press; pp.3-52

Woifreys, J. (2001). *Introducing Literary Theories A Guide and Glossary*. Edinburgh. Edinburgh University PressLtd.

Wu, H. (2003). “Size the Day: An Existentialist look” Accedemy publisher manufactured in Finland: *Journal of Language teaching andResearch,* vol.4, No.2, pp. 437-442).

Xiao, L. (2011). “An Aanalysis of the Disillusionment of the Americam Dream in the Great Gatsby：Based on the Perspective of Consumerisim”.*Journal of Literature and Art Studies,* vol. 7, No. 1, 63-68.

## አባሪዎች

### አባሪ- ሀ፡- የረጅም ልቦለዱ አጽመ-ታሪክ

የዚህ ጥናት ማጠንጠኛ የሆነው ሖፍ (2010) ረጅም ልቦለድ በበርካታ ደጋፊ ታሪኮች የተዋቀረ ነው፡፡ እንዳንዱን ታሪኮች አንድ በአንድ ለቅሞ በማውጣት ከዚህ ክፍል ውስጥ ማካተቱ ተገቢነት የለውምና የዋናው ታሪክ አጽም ብቻ በጥቂቱ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ የዚህ ክፍል ዓላማም ይኸው ነው፡፡

አቶ ኮለሴ፣ ገና በጨቅላነት ዕድሜው ከአንዲት ኘረረት ካለች ጥልቀት የሌላት ባህር ውስጥ ሊሞት ሲያጣጥር ባለበት ወቅት አቶ ባሪያው የተባሉ ሰው አግኝተውት ከቤታቸው ወስደው እንደልጅ አድርገው ያሳድጉታል፡፡ የ18 አመት ጎረምሳ ሲሆን አሳዳጊዎቹ አቶ ባሪያው እና ወ/ሮ ንግስት ቤታቸውን አውርሰውት ይሞታሉ፡፡ የእነርሱን መሞት ተከትሎም በሹፌርነት ሙያ ላይ ተሰማርቶ እየሠራ ባለበት ወቅት መግደላዊት የምትባል አንዲት በደን እና የዱር አራዊት ድርጅት ውስጥ የምትሠራ ሴት ለሥራ ጉዳይ ወደ ሰበታ በሄደችበት አጋጣሚ ያገኛል፡፡ በዚያው አጋጣሚም ሳትወድ በግድ ካረፈችበት ድንኳን ውስጥ ገብቶ ይደፍራታል፡፡ እርሷም ከዚያች ቀን ጀምራ እየወደደችው በመምጣቷ ከቤቱ ወስዷት አብረው መኖር ይጀምራሉ፡፡ በትዳራቸው ውስጥም አንዲት ጌርሳሞት የተባለች ዕጅግ የሚያማምሩ ክናፍር (አፍ) ያሏት ልጅ ያፈራሉ፡፡

ጌርሳሞት ኮላሴ ያያትን ሁሉ በከናፍሮቿ ውበት የምትስብ ውርግርግ ልጅ ናት፡፡ ሁልጊዜም ከቤት ስትወጣ ከሰፈራቸው ታቦት ማደሪያ አካባቢ በአንድ ላይ ተኮልኩለው የምታገኛቸው አራት ወጣቶች አሉ፡፡ የእሷ ውበት በተለይ ደግሞ ለእነዚህ አራት ወጣቶች ልዩ ክስተት ይሆንባቸዋል፡፡ ጌርሳሞት እነዚህን ወጣቶች ሁልጊዜም ከመንገዱ ላይ ስለምታገኛቸው ወደመላመዱ መጥታለች፡፡ ለሰላምታ እጇን መስጠትም ቀጥላለች፡፡ አራቱም ወጣቶች በስስት ይመለከቷታል፡፡ ሁሉም እርሷን ለማግኘት በየራሳቸው ይመኛሉ፡፡ በዚህ ውስጣዊ ፍላጎታቸው ምክንያትም መቀራረባቸው፣ ወዳጅነታቸው እየላላ ይመጣል፡፡ አቀማመጣቸውም እርሷን አግኝቶ ለማውራት በሚመች ስልት በተራራቀ ሁኔታ እንደገና ይገነባል፡፡ እርሷም ከአንዳቸው ወደሌላቸው እየተረማመደች ሰላምታዋን ታቀጥላለች፡፡ በጊዜ ሂደት ውስጥ ግን ከአራቱ መካከል አንዱን (ገለታን) በጥብቅ ሰላም

ማለት ብሎም ቆም ብሎ ማውራት ትጀምራለች፡፡ ይህ አይነቱ ግንኙነታቸው እያደገ መጥቶ ከጥልቅ ፍቅር ውስጥ ይገባሉ፡፡ ነገር ግን በስሜት ብጫ እንደተግባቡ በአንደበታቸው ገልጠው ሳያወሩ የመጨረሻውን መተሳሰባቸውን ይፋ ሊያደርጉት ሊሳሳሙ ሲቋምጡ ከቤቷ ግቢ በእናቷ ጥሪ ምክንያት ስሜታቸው ይቋረጣል፡፡ ከዚያች ቀን በኋላ በድጋሚ ሳይገናኙ ገለታ ከአገር ወጥቶ ይቀራል፡፡ በዚህ ምክንያት ጌርሳ በእጅጉ ታዝናለች፡፡

ከነዚያ በአንድላይ ይሰበሰቡ ከነበሩት እና ጌርሳሞትን ከሚወዱት አራት ወጣቶች መካከል አሁን ሦስቱ ብቻ ቀርተዋል፤ ዘሪሁን፣ ራሚሱ እና ባካፋ፡፡ ከረጅም ጊዜ ቆይታ ጌርሳሞት በኋላ ከእነዚህ ከቀሩት ሦስት ጓደኞች መካከል ከአንደኛው ከራሚሱ ጋር ትግባባለች፡፡ የስልክ አድራሻ ተለዋውጠው መደዋወልም ይጀምራሉ፡፡ ከቀናት በአንዱ ስልክ ስታወራ የሰማቻት እናቷ መግደላዊት ስልኳን ቀምታ የራሚሱን ጨምሮ የሌሎች ወንዶችን ሁሉ ስልክ ታጠፋባታለች፡፡ ይባሱኑም ለአባቷ ተናግራ ታስቆጣታለች፡፡ አባቷ አቶ ኮላሴ በሰፈሩ ውስጥ የታወቀ እና እጅግ የሚፈራ ተደባዳቢም ነውና ከራሚሱ ቤት ሄዶ እርሱን ስላጣው ለሰራተኛቸው የማስፈራሪያ መልዕክት ያስተላልፋል፡፡ ከዚያች ቀን በኋላም ራሚሱን ላታገኘው በድንገት እንደተለያዩ በዚያው ተራራቁ፡፡

ጌርሳሞት ከጓደኛዋ ከፌቨን ሱቅ ቁጭ እንዳለች በድንገት ከእነዚያ ጓደኞች አንዱ የሆነውን ዘሪሁንን ታገኘዋለች፡፡ ከዚያው ከሱቁ በረንዳ ላይ አብሯት ቁጭ ብሎ ጥቂት ካዋራት በኋላ ድጋሚ ለሻይ ቡና (ለግብዣ) እንደሚገናኙ እና በሰፈው እንደሚያወሩ ቀጠሮ ይዘው ይለያያሉ፡፡ ይሁን እንጅ ያ አስፈሪ አባቷ ሁለቱ ሲያወሩ አይቶ ኖሮ፣ ተለይቷት ጥቂት እንደተራመደ አንገቱን አንቆ ወስዶ በዱላ ይቀጠቅጠዋል፡፡ በዚህ ምክንያትም ድጋሚ ሳያገኛት ይቀራል፡፡

በዚያኑ ቀን ከዘሪሁን ጋር መለያቷን ከታክሲ ውስጥ ቁጭ ብሎ ሲጠባበቅ የቆየው ባካፋ፣ ልክ ዘሪሁን ካጠገባቸው እንደተሰወረ ጌርሳሞትን ሄዶ ያገኛታል፡፡ ባካፋ ትምህርቱን ሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ ጨርሶ የባንክ ቤት ሠራተኛ ከሆነ ጊዜ አንስቶ አይታው ስለማታውቅ እና ካገኘችው ብዙ ጊዜያት ስላለፉ በጥብቅ ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ አመሻሹን ተያይዘው ለግብዣ ወደካፌ ይሄዳሉ፡፡ በዚያው አጋጣሚ ወሲብ ቀረሽ ፍቅር ይሰራሉ፡፡ በኋላም ለ15 ቀናት ያክል ለስብሰባ ወደኬንያ እንደሚሄድ እና ሲመለስ እንደሚያገኛት፣ እስከዚያውም

እንደሚደውልላት ቃል ገብቶላት ይሰነባበታሉ፡፡ ከዚያች ቅጽበት በኋላ ቀናት ተቆጠሩ፣ ሳምንታትም አለፉ፡፡ ባካፋ አድራሻው በዚያው ጠፋ፡፡ ባካፋ በምግብ መመረዝ ታሞ ከዚያው ኬንያ ሲረዳ ቆይቶ አገሩ ቢመጣም በሚገባ ስላልተሻለው ጌርሳሞትን መግኘት አልቻለም፡፡

ከዚህ ሁሉ **ቅልልቦሽ** በኋላ ጌርሳሞት ውበቷን ለመጨመር ጥርሷን ብሬስ ትሰራለች፡፡ ነገር ግን ውበቷ እንዳሰበችው ሳሆን ለከፋ ህመም እና ስቃይ ዳረጋት፡፡ ያ ያየውን ሁሉ የሚያማልለው የጌርሳሞት **አፍ** ውበቱን፣ ለዛውን፣ ደምግባቱን አጥቷል፡፡ በዚህ መካከል በልቡ አትሚት ይኖር የነበረው ራሚሱ በድጋሚ ሲያገኛት የሚያውቀውን ውበቷን የደበቀችበት ያክል እያሰበ ዳግም ላያገኛት ተስፋ ቆርጦ እስከ መጨረሻው ይለያታል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ባካፋ ከህመሙ ድኖ ከረጅም የናፍቆት እና የህመም ጊዜ በኋላ ቢያገኛትም ይህን የአፏን መበላሸት ሲያይ ለመጨረሻ ጊዜ ተሰናበታት፡፡ ጌርሳሞት ከእነዚህ ሁሉ አንዱንም ሳትይዝ፣ በውበቷም ሳትዘልቅበት ከንቱ የሆነ ህላዌን መግፋት ዕጣዋ ሆኗል፡፡

## አባሪ- ለ፡- የረጅም ልቦለዱ ቅርጽ

የዚህ ጥናት ማዕከላዊ ማጠንጠኛ እና የደራሲ አዳም ረታ ሥራ የሆነው ሐፍ ረጅም ልቦለድ ለንባብ የበቃው በ2010 ዓ.ም ሲሆን፣ ይኸውም በጠቅላላ በ254 (ሁለት መቶ ሃምሳ አራት) ገጾች የተቀነበበ ነው፡፡ ይሁን እንጅ ይህ ለቦለድ ከገጽ251-252 ድረስ “የድርሰቱ ቅርፅ” በሚል ይዘት ስር የልቦለዱን የአጻጻፍ ስልት የሚያትት ማብራሪያን እና ከገጽ253-254 ደግሞ “ጎዳግ ማስታወሻ” በሚል ርዕሰ ጉዳይ ስር ከተለያዩ ቋንቋዎች፣ በተለያዩ አዝማናት ያገለግሉ የነበሩ የቋንቋ አጠቃቀሞች እንደዚሁም እራሱ ደራሲው (የፈጠራቸው?) አዳዲስ ቃላት ወይም የቋንቋ አጠቃቀሞች የተብራሩባቸውን ክፍሎች አካትቶ የያዘ ነው፡፡ በዚህ የ “ጎዳግ ማስታወሻ” ክፍል ስር በልቦለዱ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ነገር ግን አንባቢያንን ያደናግራሉ አሊያም ተጨማሪ ፍንጭ ይሰጣሉ ተብለው የታመነባቸው የተለያዩ ቃላት፣ ሐረጋት እና የቋንቋ አጠቃቀሞች ተለይተው ትርጓሜ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ከዚህ አንፃር ይህ ክፍል የቃላት ብያኔ ክፍል ነው ማለት የቻላል፡፡ በዚህ መሠረት ሐፍ ረጅም ልቦለድ ከድርሰት (ከልቦለድ) ሥራነት ባሻገር ወይም ከዚህ በላቀ ሁኔታ ስለ ልቦለድ አጻጻፍ ስልትም ሆነ ስለ አዳዲስ ቃላት ትርጓሜ በሌሎች የአማርኛ ለቦለዶች ዘንድ ባልተለመደ

(ባልተነካ?) መልኩ ፍንጭ እየሰጠ፣ አንድም በውስጡ አምቆ የያዘውን መልዕክት ለተደራሲያን በግልፅ በማቅረብ፣ አንድም ደግሞ ለአንባቢያንም ሆነ ለሌሎች ደራሲያን (ይህን ልቦለድ ሥራ ለሚያነቡ ሁሉ) እንደመሪ መጽሐፍ በመሆን የድርሰት አጻጻፍ ስልትን የሚጠቁም አሊያም እንደመዝገበ ቃላት ሁሉ ለአዳዲስ፣ ለተረሱ እና ላልተለመዱ ቃላት ብያኔ የሚሰጥ ተጨማሪ አጋዥ መጽሐፍም ነው ማለት ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ሐፍ ረጅም ልቦለድ የምልሰት ታሪኮች፣ ለዋናው ታሪክ ማጠናከሪያነት የገቡ ንዑሳን ታሪኮች እና እራሱ የልቦለዱ ታሪክ የሚጠራቸው አዳዲስ ሃሳቦች በግርጌ ማስታወሻ መልክ እዚህም-እዚያም በሰፊው ተብራርተው ቀርበውበታል፡፡ በመሆኑም እንደ የትኛውም አይነት የአማርኛ ልቦለድ የዋናውን ታሪክ የመጀመሪያ ጫፍ እንደያዝን በቀጥታ እያጠነጠንን ከመጨረሻው ጫፍ አንደርስም፤ ይልቁንም በየመካከሉ በተለያየ መጠን ከንዑሳን ታሪኮች ጋር ተተብትቦ እና እርስ በእርስ ተወሳስቦ እናገኘዋለን እንጂ፡፡ ታዲያ በዚህ ጊዜ ቀልባችንን ሰብሰብ፣ ንባባችንንም ገታ በማድረግ የተወሳሰበ የመሰለውን እያንዳንዱን ክር እየመዘዝን እና የዋናውን ታሪክ አካል እስኪጠቁመን ድረስ እንዳስፈላጊነቱ ወደፊት ወይም ወደኋላ ሳብ ረገብ እያደረግን መመርመር ግድ ይሆንብናል፡፡ አሊያ ግን ተቆርጦ እንደሚቀጠል ክር ሁሉ ቋጠሮው የበዛ እና ለመፍታት የሚያስቸግር አለፍ ሲልም አገልግሎት የማይሰጥ ይሆናል፡፡

ይህ ልቦለድ በተለመደ መልኩ በምዕራፍ ቅደም ተከተል የተዋቀረም አይደለም፤ ሁለት ዋናዋና "መልካ መልክ አንድ" እና "መልካመልክ ሁለት" በተሰኙ ክፍሎች የተከፈለ ሲሆን፣ በእያንዳንዱ ክፍሎች (መልካ መልኮች) ውስጥ ደግሞ ገፀ ባህርያቱን እንደዋና የምዕራፍ ማደራጃነት በመጠቀም እያንዳንዱ ገፀ ባህርያት በየተራ ዕየተጠሩ ከሚመለከታቸው ታሪክ ጋር ተዋህደው ቀርበዋል (በተለይ ደግሞ መ "መልካመልክ አንድ" ውስጥ)፡፡ በ "መልካመልክ አንድ" ውስት በርካታ ንዑሳን ገፀ ባህርያትን ጨምሮ የአምስቱም ዋና ዋና ገፀ ባህርያት ህላዌ አንድ በአንድ ተብራርቷል፡፡ በእያንዳንዱ ገፀ ባህርያት ታሪክ ውስጥም የማንም ታሪክ ጣልቃ አይገባባቸውም፤ ምናልባት ከየራሳቸው ጋር የጠበቀ ዝምድና ያለው ካልሆነ በስተቀር፡፡

**መግለጫ**

ይህ “የህልውናዊነት ጭብጦች በአዳም ረታ ሐፍ ውስጥ” የተሰኘ ጥናት ለባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል ለአማርኛ ሥነጽሑፍ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ቴሲስ ሲሆን፤ ይኸውም ከዚህ በፊት በማንኛውም ዩኒቨርሲቲ የዲግሪ ማሟያ ሆኖ ያልቀረበ መሆኑን እና ለጥናቱ በምንጭነት የተጠቀምኩባቸው መረጃዎችን በሙሉ በተገቢው መንገድ መጥቀሴን በፊርማየ አረጋግጣለሁ፡፡

**የተማሪው ስም** መንበሩ ክበር ተመስገን

**ፊርማ** -----------------------

**ቀን** -----------------------

**የካቲት፣ 2012 ዓ.ም**

**ባሕር ዳር**